ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ደርቃ ፡ የተዋበች ፡ ሃውልት ፡ መስላ ፡ ከተመለከተችው ፡ በኋላ ፡ እንባዋ ፡ ይረግፍ ፡ ጀመር ። ከዚያም ፡ ዘልላ ፡ አንገቱን ፡ በረዶ ፡ በመሰሉት ፡ ክንዶቿ ፡ አቅፋ ፡ ጮኻ ፡ ተንሰቀሰቀች ።

ልክ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከውጭ ፤ ራቅ ፡ ያለ ፡ የጫጫታና ፡ የጡሩምባ ፡ ድምጽ ፡ ተሰማ ። ለአንድሬይ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አልተሰማውም ። ለእሱ ፡ የሚሰማው ፤ የተዋቡት ፡ ክንፈሮቿና ፡ ሞቃት ፡ ትንፋሿ ፤ ጉንጩን ፡ የሚነካው ፡ እንባዋ ፤ ፊቱን ፡ ያለበሰው ፡ ሐር ፡ የመሰለው ፡ ጸጉሩዋ ፡ መዓዛ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ታታሪዋ ፡ ገረድ ፤ «ዳንን! ዳንን!» በማለት ፡ በደስታ ፡ እየጮኸች ፡ ገባችና ፤ «ወታደሮቻችን ፡ ከተማ ፡ ገብተዋል ። እህልና ፡ እንዲሁም ፡ የተማረኩ ፡ ዛፖሮዥያኖችን ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡» አለች ።

ነገር ፡ ግን ፡ የተቃቀፉት ፡ ልጂቱና ፡ ጐልማሳው ፤ የማን ፡ ወታደሮች ፡ ከተማ ፡ እንደገቡ ፤ ምንስ ፡ ይዘው ፡ እንደመጡ ፤ የተማረኩት ፡ ዛፖሮዥያውያኖችስ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፡ በፍጹም ፡ አላዳመጡም ። አንድሬይ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ በማይገኝ ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ተውጦ ፡ ጉንጩን ፡ የሚነካኩትን ፡ ጣፋጭ ፡ ከንፈሮች ፡ ይስም ፡ ጀመር ። እሷም ፡ መልሳ ፡ ትስመው ፡ ነበር ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሁለቱንም ፡ የተሰማቸው ፡ ስሜት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በሕይወቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚሰጥ ፡ ስሜት ፡ ነው ።

ኮዛኩ ፡ ከእንግዲህ ፡ ጠፋ ፡ ማለት ፡ ነው! ከኮዛክ ፡ መኳንንትነት ፡ ኮበለለ! ከእንግዲህ ፡ ዛፖሮዥዬን ፤ የአባቱን ፡ መንደሮች ፤ የአምላኩንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አያይም! ኡክሬይንም ፡ ሊጠብቋት ፡ ከታጠቁት ፡ ልጆቿ ፡ ሁሉ ፡ የላቀውን ፡ ጀግና ፡ ልጅዋን ፡ ከእንግዲህ ፡ አታየውም ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ከሸበተው ፡ ጸጕሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጭቶ ፡ እንዲህ ፡ የሚያሳፍረውን ፡ ልጁን ፡ የወለደበትን ፡ ቀን ፡ ይረግማል ።





ጩኸትና ፡ ሽብር ፡ የዛፖሮዥያንን ፡ ሠፈር ፡ መላው ። በመጀመሪያ ፡ ላይ ፡ ወታደሮቹ ፡ እንዴት ፡ አልፈው ፡ ከከተማው ፡ እንደገቡ ፡ ማንም ፡ ሊያውቅ ፡ አልቻለም ። በኋላ ፡ ግን ፡ በከተማው ፡ የስርቆሽ ፡ በር ፡ ሠፍሮ ፡ የነበረው ፡ የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ጥምብዝ ፡ ብሎ ፡ ሰክሮ ፡ ስለነበር ፡ እንዳቸውም ፡ ሳይሰሙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ደርሰው ፤ ግማሾቻቸውን ፡ ገድለው ፡ የተረፉትን ፡ ማርከው ፡ መሄዳቸው ፡ ታወቀ ። ጫጫታውን ፡ የሰሙ ፡ የጐረቤት ፡ ሰፈር ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ መሳሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ሲነሱ ፡ ወታደሮቹ ፡ ከተማውን ፡ ገብተው ፡ ኖሮ ፡ ያለ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተሯሩጠው ፡ የተከተሉትንም ፡ እንቅልፍ ፡ ያልለቀቃቸው ፡ ኮዛኮች ፡ የወታደሮቹ ፡ የደጀን ፡ ጦር ፡ ተታኩሶ ፡ መለሳቸው ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፡ ሁሉም ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ አዝዞ ፡ ሁሉም ፡ ተሰበሰቡና ፡ ባርኔጣቸውን ፡ አውልቀው ፡ ዙሪያውን ፡ በጸጥታ ፡ ሲቆሙ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የደረሰውን ፡ አያችሁ ፡ ወንድሞቼ ። ስካር ፡ ምን ፡ እንዳደረሰ ፡ ተመለከታችሁ! ጠላት ፡ እንዴት ፡ እንዳሳፈረን ፡ ይኸው ፡ አያችሁ ። ሁልጊዜ ፡ ይኸው ፡ ናችሁ! የሚሰጣችሁ ፡ ቮድካ ፡ ትንሽ ፡ በርከት ፡ ካለላችሁ ፡ ትጋቱ ፡ ትጋቱና ፡ የክርስቲያን ፡ ወታደሮች ፡ ጠላት ፡ ሱሪያችሁን ፡ መጐተት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ፊታችሁ ፡ ላይ ፡ ቢያነጥስባችሁም ፡ አትሰሙትም!»

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጥፋታቸውን ፡ በመገንዘብ ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ቆሙ ። የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መልስ ፡ ሰጠ ፤

«ቆይ ፡ እስቲ ፡ ባትኮ! ምንም ፡ እንኳን ፡ ኮሼቮይው ፡ ሲናገር ፡ ማቋረጥ ፡ ሕገ ፡ ወጥ ፡ ቢሆንም ፤ ጉዳዩ ፡ አንተ ፡ እንዳልኸው ፡ ባለመሆኑ ፡ ልናገር ፡ ይገባኛል ። ይህን ፡ የክርስ

ቲያን ፣ ጦር ፣ ስትወቅስ ፣ ትክክለኛ ፣ ፍርድ ፣ አልተከተልሀም ። በዘመቻ ፡ ላይ ፡ እያሉ ፣ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ሲዋጉ ፡ ወይም ፣ በሌላ ፡ ጠንካራ ፣ ተግባር ፣ ላይ ፣ እንደተመደቡ ፣ ሰክረው ፣ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሞት ፡ የሚገባቸው ፡ ጥፋተኞች ፣ በሆኑ ፣ ነበር ። እኛ ፡ ግን ፡ በከንቱ ፣ ተጐልተን ፡ ወይም ፡ በከተማው ፣ ዙሪያ ፡ ያለ ፣ ሥራ ፣ ስንንቀዋለል ፣ ነው ፡ የሰነበትነው ። ወይ ፣ አልጾምን ፡ ወይ ፣ ሌላ ፡ የክርስቲያን ፣ ሙያ ፣ አልሠራን ። በዚህን ፣ ጊዜ ፣ አንድ ፣ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ተጐልቶ ፣ ከመጠጣትና ፣ ከመስከር ፣ እንዴት ፣ ይወሰናል? በዚህ ፣ ምንም ፣ ኃጢአት ፣ የለበትም ። ይልቅስ ፡ አሁን ፡ ባላሰቡ ፣ ሰዎች ፣ ላይ ፣ አደጋ ፣ ጥለው ፡ ለማምለጥ ፡ እንደማይችሉ ፣ እናሳያቸው ። ከዚህ ፣ ቀደም ፡ ቀጥቅጠን ፡ ድል ፣ አድርገናቸዋል ። አሁንም ፣ ያንዳቸው ፣ ህይወት ፣ እንኳን ፣ እንዳይተርፍ ፣ አድርገን ፣ እንቀጥቅጣቸው ።»

የመንደሩ ፡ አለቃ ፣ ንግግር ፡ ኮዛኮቹን ፣ ሁሉ ፡ አስደሰታቸው ። አቀርቅሮ ፡ የነበረው ፡ ራሳቸው ፣ ቀና ፣ አለና ፣ ብዙዎቹም ፤ «ኩኩቤንኮ ፣ መልካም ፣ ተናገረ!» በማለት ፣ አደነቁ ።

ከኮሼቮይው ፣ አጠገብ ፣ ቆሞ ፣ የነበረው ፣ ታራስ ፡ ቡልባ ፤ «ታዲያስ ፡ ኮሼቮይ? ኩኩቤንኮ ፣ እውነቱን ፣ የተናገረ ፡ይመስላል ። ታዲያ ፣ ለዚህ ፣ ምን ፣ ትመለሳለህ?» አለው ።

ኮሼቮይውም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«በእውነቱ ፡ እንዲህ ፣ ያለ ፣ ልጅ ፡ የወለደ ፡ አባት ፡ የታደለ ፡ ነው! የነቀፌታ ፡ ቃል ፡ ለመሰንዘር ፣ አዋቂነት ፣ አያስፈልገውም ። ነገር ፡ ግን ፣ በችግር ፡ ላይ ፣ ያለን ፡ ሰው ፡ የበለጠ ፣ በማሳዘን ፣ ፈንታ ፣ የሚያነቃቃና ፣ የሚያደፋፍር ፣ ቃል ፣ ለመናገር ፣ ታላቅ ፣ ጥበብን ፣ ይጠይቃል ። እኔም ፣ ራሴ ፡ የሚያበረታታችሁ ፡ ቃል ፡ ለመናገር ፣ አስቤ ፣ ነበር ። ግን ፣ ኩኩቤንኮ ፡ ፈጥኖ ፡ በማሰብ ፣ ተናገረው ።»



በዚህን ፣ ጊዜ ፣ «ኮሼቮይውም ፣ መልካም ፣ ተናገረ!» የሚል ፣ የብዙ ፡ ሰው ፡ ድምጽ ፡ አስተጋባ ።

ጠና ፣ ያሉት ፣ ሽበቶ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንኳን ፣ ሳይቀሩ ፣ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፣ በዝግታ ፣ «መልካም ፡ ተናገረ ፡ » አሉ ።

ወዲያው ፡ ኮሼቮይው ፣ እንዲህ ፣ ሲል ፣ ንግግሩን ፣ ቀጠለ ፤

«አሁን ፣ አዳምጡኝ ፣ ወዳጆቼ! ሰይጣን ፣ ይያዘውና ፤ ይህን ፣ ምሽግ ፣ ለመያዝ ፤ ጀርመኖች ፣ እንደሚያደርጉት ፡ ተንጠላጥሎ ፣ ወይም ፣ ሰርስሮ ፡ መግባት ፣ የኮዛክ ፡ ሞያ ፣ አይደለም ። በግምት ፣ ለመረዳት ፣ እንደምንችለው ፣ ጠላቶቻችን ፣ወደ ፣ ከተማው ፣ ሲገቡ ፣ ብዙ ፣ ሠረገላ ፣ ስላልነበራቸው ፣ በቂ ፡ ስንቅና ፣ ጓዝ ፣ አልያዙም ፡ ማለት ፣ ነው ። በከተማው ፣ ውስጥ ፣ ያሉት ፣ ሰዎችም ፡ በጣም ፣ ስለተራቡ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ በአንድ ፣ አፍታ ፣ ነው ፣ የሚጨርሱት ። በሳር ፡ ረገድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ፡ ከቅዱሳናቸው ፣ አንዱ ፣ ከሰማይ ፡ ድርቆሽ ፡ ካልጣለላቸው ፣ በቀር ፣ ፈረሶቻቸው ፣ ምንም ፡ የሚቀምሱት ፡ የላቸውም ። ይህንኑም ፣ እግዚአብሔር ፣ ይወቅ ። ቄሶቻቸው ፡ ከመላሰኘነት ፡ በቀር ፣ ምንም ፣ ፍሬ ፡ የላቸውም ፡... የሆነው ፡ ሆኖ ፣ ጠላቶቻችን ፡ ምሽጋቸውን ፡ ትተው ፡ መውጣታቸው ፣ አይቀርም ። ስለዚህ ፡ በሶስት ፡ ተከፈሉና ፣ በሶስቱ ፡ የከተማው ፣ በሮች ፣ ተሰለፉ ። የአምስት ፣ መንደር ፡ ጦር ፡ በዋናው ፣ በር ፡ ፊት ፣ ለፊት ፤ በቀሩት ፣ በሁለቱ ፣ ደግሞ ፣ በያንዳንዳቸው ፣ የሶስት ፣ መንደር ፣ ጦር ፣ ይሰለፍ ። የዲያድኪቭና ፣ የኮርሰን ፡ መንደሮች ፣ ለደፈጣ ፡ ይዘጋጁ ። ኮሎኔል ፡ ታራስም ፡ ክፍለ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፣ ያደፍጣል ። የቲታሬቭካና ፣ የቲሞገሼቭካ ፣ መንደሮች ፣ ተጠባባቂ ፣ ጦር ፣ በመሆን ፣ ከጓዛችን ፣ በስተቀኝ ፣ ይሰለፉሉ ። የሸቸርቢኖቭና ፣ የላይኛው ፣ እስቴብሊኪቭ ፣ መንደሮችም ፣ እንዲሁ ፣ በጓዙ ፡ በስተግራ ፣ ይሰለፉሉ ። ከዚያ ፣ ከመካከላችን ፡ አነጋገር ፣ የሚ

ያውቁ ፡ ደፋሮች ፡ ወጥተው ፡ ጠላትን ፡ በንግግር ፡ ያበሳጩ!
ፖሊሾች ፡ በተፈጥሮ ፡ ቅል ፡ ራሶች ፡ ስለሆኑ ፡ ስድባችሁን ፡
አይችሉምና ፡ ዛሬውኑ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ከምሽጋቸው ፡ ሳይ
ወጡ ፡ አይቀሩም ። የሰፈር ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ ሰፈራችሁን ፡
መቆጣጠር ፡ አለባችሁ ። ሰው ፡ የጐደለበት ፡ እንዳለ ፡ ከፔ
ሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ከተረፉት ፡ ሰዎች ፡ ወስዶ ፡ ይሙላ ።
ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ተቆጣጥራችሁ ፡ አጠናቅቁ ። አእምሮውን ፡
ቀለል ፡ እንዲለው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ዳቦና ፡ አንድ ፡
መለኪያ ፡ ቮድካ ፡ ስጡ ። ብቻ ፡ የትናንቱ ፡ ምግብ ፡ ሲታሰብ ፡
የማንም ፡ ሆድ ፡ የጐደለ ፡ አይመስለኝም ። እንዲያውም ፡ እው
ነት ፡ ለመናገር ፡ እንደትናንቱ ፡ አበላላችሁ ፡ ሳትፈነዱ ፡ ማደ
ራችሁ ፡ ገርሞኛል ። ደግሞ ፡ የመጨረሻ ፡ ትእዛዜን ፡ አዳ
ምጡ ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ የመጠጥ ፡ ነጋዴ ፡ አንዲት ፡ መለ
ኪያ ፡ ቮድካ ፡ እንኳን ፡ ለአንድ ፡ ኮዛክ ፡ ሲሸጥ ፡ ቢገኝ ፡ የአ
ሳማ ፡ ጆሮ ፡ ግንባሩ ፡ ላይ ፡ በምስማር ፡ መትቼ ፡ ቁል
ቁል ፡ ነው ፡ የምሰቅለው ። አሁን ፡ ወንድሞቼ ፡ ወደየሥ
ራችሁ!»

ኮሼቮይው ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቶ ፡ ሲያበቃ ፤ ቆባቸውን ፡
እንዳወለቁ ፡ እጅ ፡ ነስተውት ፡ ወደየሠረገላቸውና ፡ ወደየ
ሰፈራቸው ፡ ተሰማሩ ። ርቀው ፡ እስኪሔዱም ፡ ድረስ ፡ ቆባ
ቸውን ፡ መልሰውን ፡ አላደረጉም ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ ዝግጅታ
ቸውን ፡ ጀመሩ ። ጐራዴያቸውንና ፡ ሰይፋቸውን ፡ አሰናዱ ።
ባሩድም ፡ ከከረጢት ፡ እያወጡ ፡ የባሩድ ፡ ቀንዳቸውን ፡ ሞሉ ።
ፈረሶቻቸውን ፡ መርጠው ፡ ሠረገላዎቻቸውንም ፡ አደራጁ ።
ታራስ ፡ ወደ ፡ ክፍለ ፡ ጦሩ ፡ ሲሄድ ፡ መንገዱን ፡ ሁሉ ፡
አንድሬይ ፡ የት ፡ እንደጠፋ ፡ ያሰላስል ፡ ነበር ። እንደሌሎቹ ፡
ከመንቃቱ ፡ በፊት ፡ ታስሮ ፡ ተማርኮ ፡ ይሆን? ግን ፡ ይህ ፡
ሊሆን ፡ አይችልም ። አንድሬይ ፡ በሕይወቱ ፡ እንዳለ ፡ የሚ
ማረክ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። ደግሞ ፡ ሞቷል ፡ እንዳይባል ፡
ከሞቱት ፡ ኮዛኮች ፡ መሃል ፡ ሬሳው ፡ አልተገኘም ። ታራስ ፡



ከጦሩ ፡ ሰፈር ፡ ሲደርስ ፡ በሃሳብ ፡ ከመዋጡ ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡
ሰው ፡ ስሙን ፡ ሲጠራው ፡ አልሰማም ፡ ነበር ።
በመጨረሻም ፡ ከእንቅልፍ ፡ እንደነቃ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፤
«ማን ፡ ነው ፡ የሚፈልገኝ?» ሲል ፡ አይሁዱ ፡ ያንኬል ፡
ከፊቱ ፡ ቆሞ ፡ አገኘ ።
አይሁዱም ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ እንዳሰበ ፡ ሁሉ ፡
እየተርበተበተ ፡ «ክቡር ፡ ኮሎኔል! ክቡር ፡ ኰሎኔል! ከተማ ፡
ደርሼ ፡ ነው ፡ የመጣሁ ፤ ክቡር ፡ ኮሎኔል!» አለ ።
ታራስ ፡ ይህ ፡ አይሁድ ፡ ከተማው ፡ ገብቶ ፡ ለመውጣት ፡
እንዴት ፡ እንደቻለ ፡ በማድነቅ ፡ እየተመለከተ ፤ «ምን ፡ ሰይ
ጣን ፡ ነው ፡ የወሰደህ?» አለው ።

«ይኸው ፡ አሁን ፡ እነግረዎታለሁ ። ይኸውልዎ ፡ በአነ
ጋግ ፡ ላይ ፡ ኮዛኮች ፡ ተኩስ ፡ ጀምረው ፡ ያን ፡ ሁሉ ፡ ጩኸ
ት ፡ ስሰማ ፡ ወዲያው ፡ ጨርቄን ፡ አንጠልጥየ ፡ ለማጥለቅ ፡
እንኳን ፡ ሳልዘገይ ፡ የተኩሱን ፡ ምክንያት ፡ ለማጣራት ፡ ሮ
ጥሁና ፡ ልክ ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ስደርስ ፡ የመጨረሻዎቹ ፡
ወታደሮች ፡ ሲገቡ ፡ አገኘሁ ። በወታደሮቹም ፡ ፊት ፡ ፊት ፡
ኮርኔት ፡ ጋሌንዶዊችን ፡ አየኋቸው ። እኒህ ፡ ሰው ፡ የማውቃ
ቸው ፡ መኳንንት ፡ ሲሆኑ ፤ በአለፉት ፡ ሶስት ፡ ዓመታት ፡ ው
ስጥ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ ብድር ፡ አለባቸው ። ስለዚ
ህ ፡ ብድሬን ፡ የምጠይቅ ፡ በመምሰል ፡ ከነሱ ፡ ጋር ፡ አብሬ ፡
ከተማ ፡ ገባሁ ።»
«እንዴት? ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ገብተህ ፡ ደግሞ ፡ ብድር ፡
ለማስከፈል ፡ ፈለግህ? እሱም ፡ እዚያው ፡ እንደውሻ ፡ እንድ
ትሰቀል ፡ ሳያደርግ ፡ ቀረ?» አለው ፡ ቡልባ ።
«እንዴታ! ሊሰቅሉኝማ ፡ ፈለጉ ። አሽከሮቻቸውም ፡
ወዲያው ፡ ገመዱን ፡ አንገቴ ፡ ላይ ፡ አግብተውት ፡ ነበር ።
ግን ፡ ጌትዮውን ፡ ነፍሴን ፡ እንዲያተርፏት ፡ በመለመን ፡ ያለ
ባቸውን ፡ ብድር ፡ እስከፈለጉት ፡ ጊዜ ፡ እንዲያቆዩት ፤ ደግሞ ፡
ሌሎቹ ፡ መኳንንት ፡ ያለባቸውን ፡ ብድር ፡ ካስከፈሉኝ ፡ ተጨ

ማሪ ፡ ገንዘብ ፡ እሰጥዎታለሁ ፡ ብዬ ፡ ለመንኳቸው ። ክቡር ፡ ኮርኔቱ ፣ ብዙ ፡ መንደሮች ፣ አራት ፡ ቤተ ፡ መንግሥቶች ፡ እንዲሁም ፡ እስከ ፡ እሽክሎቭ ፡ የሚደርስ ፡ ሰፊ ፡ መሬት ፡ ይኑራቸው ፡ እንጂ ፡ በገንዘብ ፡ ረገድ ፡ ከአንድ ፡ ኮዛክ ፡ አይሻሉም ። አንድ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ እንኳን ፡ በኪሳቸው ፡ አይገኝም! አሁንም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የብሬስሎቭ ፡ አይሁዶች ፡ ባይሰጧቸው ፡ ኖሮ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ለመዝመቻ ፡ እንኳን ፡ ምንም ፡ ባላገኙ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ ከምክር ፡ ቤቱ ፡ ስብሰባ ፡ ቀሩት ፡...»

«ታዲያ ፡ ከተማ ፡ ሄደህ ፡ ምን ፡ አደረግህ? ከኛ ፡ ሰዎች ፡ ያየኸው ፡ አለ?»

«አዎ ፡ በደንብ ፡ አይቻለሁ! ብዙ ፡ የኛ ፡ ሰዎች ፡ እዚያ ፡ አሉ ። ኢሳክ ፣ ራሁም ፣ ሳሙኤል ፣ ሃይቫሎህ ፡ ደግሞ ፡ ወለድ ፡ እግድ ፡ ያዡ ፡ አይሁድ ፡...»

«ውሾቹን ፡ እዚያው ፡ ሰይጣን ፡ ይውሰዳቸው! ስለአይሁድ ፡ ዘሮችህ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ግድ ፡ አለኝ! እኔ ፡ የጠየቅሁህ ፡ ስለኛ ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ነው!» አለና ፡ ታራስ ፡ በቁጣ ፡ ጮኸበት ።

«አይ ፣ እኔ ፡ የኛን ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ አላየሁም ። ጌታዬ ፡ አንድሬይን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ያየኋቸው ።»

«አንድሬይን ፡ አየኸው! በልኮ ፡ ንገረኝ ፡ አንተ ፡ አይሁድ ፣ የት ፡ ነው ፡ ያየኸው? በእስር ፡ ቤት? በጓድጓድ ፡ ውስጥ? ተዋርዶና ፡ ታሥሮ ፡ ነው?»

«ጌታዬ ፡ አንድሬይን ፡ ለማሰር ፡ ማን ፡ ይደፍራል! አሁን ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ታላቅ ፡ መኳንንት ፡ ሆነዋል ። ኧረግ ፡ በእግዚአብሔር ፣ ላውቃቸው ፡ እንኳን ፡ አልቻልሁም! ትከሻቸው ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፣ ደረታቸው ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፣ ጥሩራቸው ፡ ወርቅ ፡ የጦር ፡ ትጥቃቸው ፡ ሁሉ ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ ነው ። ልክ ፡ እንደመስከረም ፡ ጸሐይ ፡ በወርቅ ፡ ያንጸባርቃሉ ። ደግሞ ፡ ወየወዱ ፡ ምርጥ ፡ ፈረሳቸውን ፡ ሰጥተዋቸዋል ። ፈረሱ ፡ ብቻ ፡ ሁለት ፡ መቶ ፡ ቼርቮኔጽ ፡ የሚያወጣ ፡ ነው!»



ቡልባ ፡ ግራ ፡ ገባው ።

«ለምንድን ፡ ነው ፡ ይህን ፡ የባዕድ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ የለበሰው?»

«የበለጠ ፡ ስለሚያምር ፡ ነዋ ። ደግሞ ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላሉ ። ሌሎችም ፡ አብረዋቸው ፡ ወዲያ ፡ ወዲህ ፡ ይላሉ ። እሳቸው ፡ ያስተምሯቸዋል ፣ እነሱም ፡ ያስተምሯቸዋል ። ልክ ፡ ሃብታም ፡ የፖሊሽ ፡ መኰንን ፡ ሆነዋል!»

«ይህን ፡ እንዲያደርግ ፡ ማን ፡ አስገደደው?»

«እኔ ፡ ማንም ፡ አስገደዳቸው ፡ አላልሁም ። በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ወደነሱ ፡ መሔዳቸውን ፡ ጌታዬ ፡ አያውቁም ፡ እንዴ?»

«ማን ፡ ነው ፡ በፈቃዱ ፡ የሔደው?»

«ጌታዬ ፡ አንድሬይ ፡ ናቸዋ!»

«ወዴት ፡ ነው ፡ የሔደው?»

«ወደነሱ ፡ ወገን ፡ ነዋ ። አሁን ፡ በቃ ፡ በፍጹም ፡ የነሱ ፡ ሰው ፡ ሆነዋል ።»

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንት ፡ የአሳማ ፡ ጆሮ!»

«እንዴት ፡ ልዋሽ ፡ እችላለሁ! ውሸት ፡ የምናገረው ፡ እኔ ፡ ሞኝ ፡ ነኝ ፡ እንዴ! በነፍሴ ፡ ቆርጬ ፡ እዋሻለሁ ፡ ይመስለዎታል! ለአንድ ፡ ጌታ ፡ ውሸት ፡ የሚናገር ፡ አይሁድ ፡ እንደውሻ ፡ መስቀሉን ፡ አጣሁት ፡ እንዴ!»

«እንግዲህ ፡ አንተ ፡ እንደምትለው ፡ ኃይማኖትና ፡ አገሩን ፡ ሸጧል ፡ ማለት ፡ ነው?»

«እኔ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ሸጠዋል ፡ አላልሁም ። እኔ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ መሔዳቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የተናገርሁት ። »

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንት ፡ የተረገምህ ፡ አይሁድ! በክርስቲያኖች ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ ተሠርቶ ፡ አያውቅም! ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንት ፡ ልክስክስ ፡ ውሻ!»

«እንዲያው ፣ ዋሽቼ ፡ እንደሆን ፡ በቤቴ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ሳር ፡ ይብቀልበት! እውነት ፡ ዋሽቼ ፡ እንደሆን ፣ በአባቴ ፣

በእናቴ ፤ በአማቴ ፤ በአባቴ ፡ አባት ፤ በእናቴም ፡ አባት ፡ መቃብሮች ፡ ላይ ፡ አላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ምራቁን ፡ ይትፋበት! እንዲያውም ፡ ጌታዬ ፡ ከፈቀዱ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ የሔዱ በትንም ፡ ምክንያት ፡ እንግረዎታለሁ ።»

«ለምን ፡ ሔደ?»

«ወየወዱ ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አለቻቸው ፡… አቤት ፡ አምላኬ! እንዴት ፡ ቆንጆ ፡ ናት!»

እዚህ ፡ ላይ ፡ አይሁዱ ፡ እጆቹን ፡ በመዘርጋት ፤ ዓይኖቹን ፡ በማፍጠጥ ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የሚጣፍጥ ፡ ነገር ፡ እንዲቀምስ ፡ ሁሉ ፡ አፉን ፡ በማጣጣም ፡ ስለውበቷ ፡ ለመግለጽ ፡ ሞከረ ።

«በልኮ ፤ ታዲያስ ፡ ምን ፡ ሆነ?» አለው ፡ ቡልባ ።

«በቃ ፤ ለእሷ ፡ ሲሉ ፡ ወደነሱ ፡ ወገን ፡ ሔዱ ። አንድ ፡ ሰው ፡ ፍቅር ፡ ከያዘው ፡ ውኃ ፡ እንደተነከረ ፡ የጫማ ፡ ቆዳ ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደፈለጉት ፡ ይተጣጠፋል ።»

ቡልባ ፡ በሃሳብ ፡ ተዋጠ ። የሴት ፡ ኃይሏ ፡ ታላቅ ፡ መሆኑና ፡ ብዙ ፡ ኃይለኛ ፡ ሰዎችንም ፡ አሸንፋ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ እንደመራች ፡ ትዝ ፡ አለው ። አንድሬይም ፡ በተፈጥሮው ፡ በሴት ፡ ውበት ፡ በቶሎ ፡ የሚማረክ ፡ መሆኑንም ፡ አስታወሰ ። ይህን ፡ ሲያሰላስል ፡ ከቆመበት ፡ መሬት ፡ የተተከለ ፡ ይመስል ፡ ሳይንቀሳቀስ ፡ ብዙ ፡ ቆየ ።

አይሁዱም ፤ «ይስሙኝ ፡ ጌታዬ ፤ ሁሉንም ፡ ልንገርዎ ፡» አለና ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ፤

«ወዲያው ፡ ጩኸቱን ፡ እንደሰማሁና ፡ ወታደሮቹ ፡ የከተማውን ፡ በር ፡ ሲገቡ ፡ ሳይ ፤ ድንገት ፡ ያስፈልገኝ ፡ ይሆናል ፡ ብዬ ፡ አንድ ፡ የሉል ፡ ጌጥ ፡ ያዝሁና ፡ ሮጥሁ ። መቼም ፡ በከተማው ፡ ወይዛዝርት ፡ አሉና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የሚበሉት ፡ ባይኖራቸው ፡ ሉሉን ፡ እንደሚገዙኝ ፡ አውቅ ፡ ነበር ። ታዲያ ፡ የኮርኔቱ ፡ አሽከሮች ፡ ወዲያው ፡ እንደለቀቁኝ ፤ ሉሉን ፡ ለመሸጥ ፡ ወደ ፡ ወየወዱ ፡ ግቢ ፡ ሮጥሁኝና ፡ እዚያው ፡ ያገኘ



ኋት ፡ አንዲት ፡ ታታር ፡ ሁሉንም ፡ ነገር ፡ ነገረችኝ ። ‘ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ሲሸሹ ፡ ሠርግ ፡ ይደረጋል ። ጌታዬ ፡ አንድሬይ ፡ ዛፖሮዥያኖቹን ፡ ለማባረር ፡ ቃል ፡ ገብተዋል ፡’ አለችኝ ።»

«ታዲያ ፡ ያን ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ ፡ እዚያው ፡ አልገደልኸውም?» አለና ፡ ቡልባ ፡ ጮኸ ።

«ለምን ፡ ይገደላሉ? በገዛ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ነው ፡ የሄዱት ። ምን ፡ ጥፋት ፡ አጠፉ? እዚያ ፡ የሚሻላቸው ፡ ሆኖ ፡ አገኙትና ፡ ሄዱ ።»

«ታዲያ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተያያችሁ?»

«እንዴታ! አየኋቸው ፡ እንጂ! አቤት ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ባለግርማ ፡ ጀግና ! ከሁሉም ፡ የላቁ ፡ ባለግርማ ፡ ሞገሥ! ደግሞ ፡ ወዲያው ፡ አወቁኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርካቸው ። ቀረብ ፡ ስላቸውም ፡ እንዲህ ፡ አሉኝ ፡…»

«ምን ፡ አለህ?»

«መጀመሪያ ፡ በጣታቸው ፡ ጠሩኝና ፡ ‘ያንኬል!’ አሉኝ ። እኔም ፤ ‘ጌታዬ ፡ አንድሬይ!’ አልኋቸው ። ‘ያንኬል ፤ ለአባቴ ፡ ንገረው ፤ ለወንድሜ ፡ ንገረው ፤ ለኮዛኮች ፡ ንገራቸው ፤ ለዛፖሮዥያን ፡ ሁሉ ፤ ለሁሉም ፡ ንገር ። ከእንግዲህ ፡ አባቴ ፡ አባቴ ፡ አይደለም ፤ ወንድሜ ፡ ወንድሜ ፡ አይደለም ፤ ጓደኞቼም ፡ ጓደኞቼ ፡ አይደሉም ። ሁሉንም ፡ እወጋቸዋለሁ! ከያንዳንዳቸው ፡ ጋር ፡ እዋጋለሁ!’ አሉኝ ።»

«ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ከሃዲ ፡ ይሁዳ! ውሸትህን ፡ ነው ፡ አንተ ፡ ውሻ! ክርስቶስን ፡ የሰቀልኸው ፡ አንተው ፡ ነህ! አንት ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተረገምህ ፡ ሰው! እገድልሃለሁ ፡ አንት ፡ ሰይጣን! በል ፡ ከፊቴ ፡ ጥፋ ፡ ወይ ፡ እዚህ ፡ ቆመህ ፡ሙት!» አለና ፡ ቡልባ ፡ በቁጣ ፡ ጮኸ ፡ ጐራዴውን ፡ መዘዘ ።

የደነገጠው ፡ አይሁድም ፡ ወዲያው ፡ ሩጫ ፡ ጀምሮ ፡ ቀጫጭን ፡ እግሮቹ ፡ የቻሉትን ፡ ያህል ፡ ይበር ፡ ጀመር ። ምንም ፡

እንኳን ፡ ታራስ ፡ ቁጣውን ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ለመወጣት ፡
ስላልፈለገ ፡ ባይከተለውም  አይሁዱ ፡ ተገላምጦ ፡ እንኳን ፡
ሳያይ ፡ የኮዛኮቹን ፡ ሰፈር ፡ አቋርጦ ፡ በመስኩም ፡ ብዙ ፡ አ
ገር ፡ ድረስ ፡ ሮጠ ።

ቡልባ ፡ አሁን ፡ ሲያስታውስ ፤ ባለፈው ፡ ሌሊት ፡ አን
ድሬይን ፡ ከአንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ በሰፈሩ ፡ መሃል ፡ ሲጓዝ ፡
እንዳየው ፡ ትዝ ፡ አለውና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ አሁንም ፡ ቢ
ሆን ፡ የገዛ ፡ ልጁ ፡ ሃይማኖቱንና ፡ ነፍሱን ፡ ሸጦ ፡ እንዲህ ፡
ካለ ፡ ውርደት ፡ ይደርሳል ፡ ብሎ ፡ ባያምንም ፡ የሸበተውን ፡
ራሱን ፡ በትካዜ ፡ አቀረቀረ ።

በመጨረሻ ፡ ጦሩን ፡ ወደ ፡ ደፈጣ ፡ መራና ፡ እሱም ፡
አብሮ ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ብቻ ፡ ኮዛኮች ፡ ሳያቃጥሉት ፡ በተ
ረፈው ፡ ጫካ ፡ ውስጥ ፡ ተሰወረ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፈ
ረሰኞችና ፡ እግረኞች ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ወደ ፡ ሶስቱ ፡ የከተ
ማው ፡ በሮች ፡ በሚወስዱት ፡ መንገዶች ፡ ተጉዞው ፡ ቀርበ
ዋል ። አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ተከታትለው ፡ የየመንደሩ ፡ የጦር ፡
ክፍሎች ፡ ይጓዙ ፡ ጀመር ። ኡማን ፤ ፖፖቪች ፤ ካኔቭ ፤ እስ
ቴብሊኪቭ ፤ ኔዛማይ ፤ ጉርጉዝ ፤ ቲታሬቭካ ፤ ቲሞዜቭካ ፤
የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ብቻ ፡ የለም ፡ እንጂ ፡ ሁሉም ፡ ተሰ
ልፈዋል ። የፔሬያስላቭ ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ ቮድካቸውን ፡
ከልክ ፡ በላይ ፡ ጠጥተው ፡ በዚሁ ፡ በመጠጣቸው ፡ መልካም ፡
እድላቸውን ፡ አጥፍተውታል ። አንዳንዶቹ ፡ ከታሠሩ ፡ በ
ኋላ ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ እንዳሉ ፡ ሲነቁ ፤ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡
እዚያው ፡ እንደተኙ ፡ በሞት ፡ ሳይነቁ ፡ ቀርተዋል ። አለ
ቃቸው ፡ ሀሊብ ፡ ራሱ ፡ ሱሪ ፡ እንኳን ፡ ሳያጠልቅ ፡ ሃሪቁን ፡
በጠላት ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፡ የነቃው ።

በከተማው ፡ ውስጥ ፡ የጠላት ፡ ንቅናቄ ፡ ይሰማ ፡ ጀመር ።
ሁሉም ፡ ከምሽጉ ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈው ፡ ለኮዛኮች ፡ ግሩም ፡
የሆነ ፡ ትርኢት ፡ ሆነው ፡ ታዩ ። የፖሊሽ ፡ መኳንንት ፡ አንዱ ፡
ከአንዱ ፡ የበለጠ ፡ ያማረ ፡ እየሆኑ ፡ በምሽጉ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።



እንደበረዶ ፡ በነጣ ፡ ላባ ፡ ያጌጡት ፡ የነሃስ ፡ ጥሩሮቻቸው ፡
እንደ ፡ ብዙ ፡ ጸሐዮች ፡ ያበሩ ፡ ጀመር ። አንዳንዶቹ ፡ ደግሞ ፡
ከጫፋቸው ፡ ወደ ፡ ጐን ፡ የታጠፉ ፡ ቀለማቸው ፡ ቀላ ፡ ያሉ ፡
ወይም ፡ ሰመያዊ ፡ ቀላል ፡ ቆቦች ፡ አድርገው ፡ በወርቀዘ
ቦ ፡ ወይም ፡ በጥልፍ ፡ ያጌጠ ፡ ኮት ፡ ለብሰዋል ። ብዙዎቹ ፡
ከፍ ፡ ያለ ፡ ዋጋ ፡ በወጣበት ፡ ጌጥ ፡ ያጌጡ ፡ ጐራዴዎችና ፡
ጠበንጃዎች ፡ ይዘዋል ። ሌላም ፡ ብዙ ፡ ጌጣጌጥና ፡ የወግ ፡
እቃ ፡ በትጥቃቸው ፡ ይታያል ። የቡድዣክ ፡ ኮሎኔል ፡ ባለ
ወርቀዘቦ ፡ ቀይ ፡ ቆብ ፡ አድርጐ ፡ ከሁሉም ፡ ግንባር ፡ ተጀ
ንኖ ፡ ቆሟል ። ኮሎኔሉ ፡ ግዙፍ ፡ ሰው ፡ ነበር ። በአካባቢው ፡
ካሉት ፡ ሁሉ ፡ በቁመትም ፡ ሆነ ፡ በውፍረት ፡ የበለጠ ፡ ሲሆን ፡
ለክብሩ ፡ የሚገባውና ፡ ውድ ፡ የሆነው ፡ ኮቱ ፡ በጭንቅ ፡ የያ
ዘው ፡ ይመስላል ። በሌሎቹ ፡ በሮች ፡ አንፃር ፡ ደግሞ ፡ ሌላ ፡
ኮሎኔል ፡ ቆሟል ። ይህኛው ፡ ኮሎኔል ፡ በሰውነቱ ፡ ትንሽና ፡
ድርቅ ፡ ያለ ፡ ሲሆን ፡ ጓሳ ፡ ከሚመስሉት ፡ ቅንድቦቹ ፡ ሥር ፡
ያሉት ፡ ጥቃቅን ፡ ዓይኖቹ ፡ በንቃት ፡ ይቁለጨለጫሉ ። ወዲ
ያና ፡ ወዲህ ፡ በቅልጥፍና ፡ እየዞረ ፡ በደረቅ ፡ እጁ ፡ በማመል
ከት ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰጥ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በአካል ፡ አነስተኛ ፡
ቢሆንም ፡ በጦር ፡ ስልት ፡ ተሰጥኦ ፡ እንዳለው ፡ ግልጽ ፡ ነ
በር ። ከእሱ ፡ ብዙም ፡ ሳይርቅ ፤ አንድ ፡ ረጅምና ፡ ለግላጋ ፡
ኮርኔት ፡ ቆሟል ። ኮርኔቱ ፡ ችፍግ ፡ ያለ ፡ ጺም ፡ ሲኖረው ፡
ጠንካራ ፡ መጠጥና ፡ ፈንጠዝያ ፡ ለመውደዱ ፡ ምልክት ፡ የ
ሆነ ፡ ደም ፡ የመሰለ ፡ ቅላት ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ ይታያል ። ከሱ
ም ፡ ጀርባ ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ፡ ይታያሉ ። እነዚህ ፡ መኳን
ንት ፡ በገንዘባቸው ፡ ወይም ፡ ከንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ባገኙት ፡
ገንዘብ ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ከዘር ፡ ዘር ፡ በወረደላቸው ፡ በአባ
ቶቻቸው ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ እቃ ፡ ለአይሁዶች ፡
በመሸጥ ፡ ባገኙት ፡ ገንዘብ ፡ የታጠቁ ፡ ነበሩ ። በዚያ ፡ የነበ
ሩት ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ከየስፍራው ፡ የተጠራቀሙ ፡ ናቸው ።
አንዳንዶቹ ፡ ለመጠጥ ፡ መግዣ ፡ እንኳን ፡ የማይሆን ፡ ገን

ዘብ ፡ የላቸውም ። ሆኖም ፡ ሁሉም ፡ ለጦርነት ፡ ለብሰውና ፡ ታጥቀው ፡ ተዘጋጅተዋል ።

የኮዛኮች ፡ ጦር ፡ ከምሽጉ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በጸጥታ ፡ ቆሞአል ። በልብሳቸው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ የወርቅ ፡ ምልክት ፡ አይታይም ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ ብቻ ፡ በአንዳንዶቹ ፡ ኰራዶዎች ፡ እጀታና ፡ በጠመንጃቸው ፡ ላይ ፡ የጌጥ ፡ ሥራ ፡ ሲያብለጨልጭ ፡ ይታያል ። ኮዛኮች ፡ በጌጥ ፡ ያሸበረቀ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ አይወዱም ። የጨርቅ ፡ ልብሶቻቸውም ፡ ሆኑ ፡ የብረት ፡ ልብሶቻቸው ፡ ጌጥ ፡ የሌላቸው ፡ ልሙጥ ፡ ናቸው ። ጫፍ ፡ ጫፋቸው ፡ ቀይ ፡ የሆኑት ፡ የበግ ፡ ቆዳ ፡ ቆቦቻቸው ፡ ሜዳውን ፡ አልብሰውት ፡ ይታያሉ ።

ከዛፖሮዥያኖቹ ፡ ሰልፍ ፡ መካከል ፡ ሁለት ፡ ኮዛኮች ፡ በፈረስ ፡ እንደተቀመጡ ፡ ለየት ፡ ብለው ፡ ወጡ ። እኒህ ፡ ኮዛኮች ፡ አንዱ ፡ ወጣት ፡ አንደኛው ፡ ደግሞ ፡ ጠና ፡ ያለ ፡ ሲሆኑ ፡ ሁለቱም ፡ በአነጋገር ፡ ቅልጥፍናቸው ፡ የታወቁ ፡ በጦር ፡ ሞያም ፡ የማይነቀፉ ፡ አህሪም ፡ ናሽና ፡ ሚኪታ ፡ ጐሎኮፕቴንኮ ፡ የሚባሉ ፡ ነበሩ ። ከነዚህ ፡ ከሁለቱም ፡ ኋላ ፡ ዴሚድ ፡ ፖፖቪች ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ተከትሏቸዋል ። ፖፖቪች ፡ በሴቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ ሲሆን ፡ በአድሪአኖፖል ፡ የተዋጋና ፡ በሕይወቱ ፡ ብዙ ፡ የጦር ፡ ፈተና ፡ የደረሰበት ፡ ሰው ፡ ነበር ። ተማርኮ ፡ በእሳት ፡ ሊቃጠል ፡ ሲል ፡ ጸጉሩና ፡ ጢሙ ፡ ከተንጫረረ ፡ በኋላ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ሴቹ ፡ መጥቶ ፡ አሁን ፡ ጸጉሩም ፡ ጢሙም ፡ አድጐለታል ። እሱም ፡ እንደቀሩት ፡ እንደሁለቱ ፡ ሰዎች ፡ በአንደበቱ ፡ ተመርጦ ፡ ነው ፡ አሁን ፡ ተከትሏቸው ፡ የሄደው ። ወዲያው ፡ እነዚህ ፡ የተመረጡት ፡ ኮዛኮች ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለማበሳጨት ፡ ዘለፋቸውን ፡ ጀመሩ ።

«አሃ! የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ቀይ ፡ ኮት ፡ ልብሶአል ፡ ግን ፡ ውስጣቸው ፡ ቢታይ ፡ ሃሞታቸው ፡ ነጭ ፡ ነው!»

ከምሽጉ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ወፍራሙ ፡ ኮሎኔልም ፤ «ቆይ ፡ አሳያችኋለሁ! ሁላችሁንም ፡ በሰንሰለት ፡ ነው ፡ እማስራችሁ ፡



ጠመንጃዎቻችሁንና ፡ ፈረሶቻችሁን ፡ አስረክቡ ፡ እናንት ፡ ገባሮች! ጓደኞቻችሁን ፡ እንዴት ፡ እንደአሰርኋቸው ፡ አላያችሁም?» አለና ፡ ወደ ፡ ተከታዮቹ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ «እስቲ ፡ እንዲያዩአቸው ፡ ኮዛኮቹን ፡ እዚህ ፡ አቅርቧቸው!» አለ ።

ኮዛኮቹ ፡ በገመድ ፡ እንደታሰሩ ፡ መጥተው ፡ ምሽጉ ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ። የመንደር ፡ አለቃቸው ፡ ህሊብ ፡ ሱሪ ፡ እንኳን ፡ ሳይኖረው ፡ ራቁቱን ፡ ከፊታቸው ፡ ቆሞአል ። ከእንቅልፉ ፡ ሳይነቃ ፡ እንደውሻ ፡ ተይዞ ፡ በመታሰሩና ፡ እንዲሁም ፡ ራቁቱን ፡ ሆኖ ፡ በወገኖቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በመታየቱ ፡ አፍሮ ፡ አንገቱን ፡ አቀረቀረ ። ጸጉሩ ፡ ሌሊቱን ፡ ሸብቶ ፡ አድሮአል ።

«አይዞህ ፡ ህሊብ! እናድንሃለን!» አሉና ፡ ከታች ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ ጮኹ ።

ቦሮዳትይ ፡ የተባለው ፡ የመንደር ፡ አለቃ ፡ «አይዞህ ፡ ጓዴ! ራቁትህን ፡ መማረከህ ፡ የአንተ ፡ ጥፋት ፡ አይደለም ። በማንም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚደርስ ፡ የአጋጣሚ ፡ ነገር ፡ ነው ። ይልቁንም ፡ አንድ ፡ ልብስ ፡ እንኳን ፡ ሳያለብሱህ ፡ ለማፌዣ ፡ ስለአመጡህ ፡ ሊያፍሩ ፡ የሚገባቸው ፡ እነሱ ፡ ነበሩ ፡» በማለት ፡ ጓደኛውን ፡ አጽናናው ።

ጐሎኮፕቴንኮ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ እየተመለከተ ፡ «እንቅልፍ ፡ ከወሰዳቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ጐበዝ ፡ ወታደሮች ፡ ናችሁ!» አለ ።

ከላይ ፡ ያሉትም ፡ «ቆዩ ፡ ቁንጮአችሁን ፡ ነው ፡ የምንቆርጥላችሁ ፡» እያሉ ፡ ጮኹ ።

«እስቲ ፡ ሲያደርጉት ፡ እናያለን!» አለ ፡ ፖፖቪች ፡ ወዲያው ፡ በኮርቻው ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ግን ፡ እኮ ፡ አይሆንም ፡ አይባልም ፤ ምናልባት ፡ ፖሊሾቹ ፡ የሚሉት ፡ እውነት ፡ ይሆናል ። እዚያ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ቅርጫት ፡ ሆድ ፡ መሪነት ፡ በእውነትም ፡ ደህና ፡ ሊከላከሉ ፡ ይችላሉ ።»

ኮዛኮቹም ፡ ፖፖቪች ፡ አንድ ፡ ቀልድ ፡ እንዳዘጋጀ ፡ ተገንዝበው ፤ «እንዴት ፡ ነው ፡ ደህና ፡ ሊከላከሉ ፡ የሚችሉት?» ብለው ፡ ጠየቁት ።

ፖፖቪችም ፡ «ምክንያቱም ፡ ቀፈታሙ ፡ ኮሎኔል ፡ መሪ ፡ ከሆነ ፡ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ከኋላው ፡ ተከልሎ ፡ እኛ ፡ የምንወረውረው ፡ ጦር ፡ ከሱ ፡ ቦርጭ ፡ አልፎ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ ሊያገኝ ፡ ስለማይችል ፡ ነው ፡» ሲል ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ሳቁ ። ብዙዎቹም ፡ የፖፖቪችን ፡ አንደበት ፡ በማድነቅ ፡ ንግግር ፡ ጀምረው ፡ ነበር ። ግን ፡ የጀመሩትን ፡ ንግግር ፡ ለመጨረስ ፡ እንኳን ፡ ጊዜ ፡ አላገኙም ።

ፖሊሾቹ ፡ ይህንን ፡ ዘለፋ ፡ ለመታገስ ፡ ስላልቻሉ ፡ ኮሎኔሉ ፡ ለውጊያ ፡ ምልክት ፡ ሲሰጥ ፡ የኮዛኮቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ ስለአየ ፤ «ዘወር ፡ በሉ ፡ ከምሽጉ ፡ ሥር ፡ ዘወር ፡ በሉ!» ብሎ ፡ ጮኸ ።

ኮዛኮቹ ፡ ከምሽጉ ፡ ሥር ፡ መለስ ፡ ከማለታቸው ፡ ፖሊሾቹ ፡ ከላይ ፡ ሆነው ፡ ተኩስ ፡ ያዘንቡባቸው ፡ ጀመር ። በምሽጉ ፡ ላይ ፡ ጥድፊያ ፡ ሆነ ፤ ሽበቶው ፡ ወየወዳ ፡ ራሳቸው ፡ በፈረስ ፡ ሆነው ፡ ብቅ ፡ አሉ ። የግንቡ ፡ በሮች ፡ ተከፍተው ፤ ብዙ ፡ ጌጥ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶች ፡ የለበሰ ፡ ወታደሮች ፡ እየጎረፉ ፡ ወጡ ። የልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ ወታደሮች ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ በያዘ ፡ የጦር ፡ ሰልፍ ፡ እየተከታተሉ ፡ ሲወጡ ፡ በመጨረሻም ፡ እንደየግል ፡ ፍላጎታቸው ፡ የለበሱና ፡ የታጠቁት ፡ ከፍተኛ ፡ መኳንንት ፡ መጡ ። መኳንንቱ ፡ ከተራው ፡ ወታደራቸው ፡ ጋር ፡ መደባለቅን ፡ አይፈቅዱም ፡ ነበር ። የሚያዙት ፡ የጦር ፡ ክፍል ፡ የሌላቸው ፡ መኳንንትም ፡ ከገባሮቻቸውና ፡ ከቤት ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ጋር ፡ ተሰለፉ ። ከመኳንንቱ ፡ ጀርባ ፡ እንደገና ፡ ሌላ ፡ የወታደሮች ፡ ሰልፍ ፡ ተከትሎአል ። ከዚያ ፡ ኮርኔቱ ፡ ቀጠለ ። ከሱም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ የወታደሮች ፡ ሰልፍ ፤ ከዚያም ፡ ወፍራሙ ፡ ኮሎኔል ፡ ሲያልፍ ፡ ትንሹ ፡ ኮሎኔል ፡ የደጀኑን ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ከኋላ ፡ ተከትሎአል ።



የኮዛኮቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ እየጮኸ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰጥ ፡ ጀመር ። «እንዳይደራጁ ፡ ጊዜ ፡ አትስጡአቸው! የሁሉም ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ አንድነት ፡ ሆናችሁ ፡ ተዋጉ! ሌሎቹን ፡ በሮች ፡ ተውአቸው! የትታሬቭ ፡ መንደር ፡ ቀኝ ፡ አዝማቹን ፡ ውጋ! የዲያድኪቭ ፡ መንደር ፡ ግራ ፡ አዝማቹን ፡ ውጋ! ኩኩቤንኮና ፡ ፓሊቮዳ ፡ ከኋላቸው ፡ ጥመዱ ! ሰልፋቸውን ፡ አበላሹ! በታትኗቸው!»

ኮዛኮቹ ፡ ከሁሉም ፡ ወገን ፡ በመውጋት ፡ የፖሊሾቹን ፡ ሰልፍ ፡ በታትነው ፡ ከመሃላቸው ፡ ተቀላቀሉ ። ለጠላታቸው ፡ የጥይት ፡ መተኮሻ ፡ ጊዜ ፡ እንኳን ፡ አልሰጡትም ፤ ጦርና ፡ ጐራዴ ፡ ሥራውን ፡ ጀመረ ። ከጠላት ፡ ጋር ፡ ተደባልቀው ፡ ስለነበር ፡ እያንዳንዱ ፡ ኮዛክ ፡ ሞያውን ፡ ለማሳየት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሆነለት ። ዴሚድ ፡ ፖፖቪች ፡ ሶስት ፡ ተራ ፡ ወታደሮች ፡ ገድሎ ፡ እንዲሁም ፡ ሁለት ፡ ከፍተኛ ፡ መኳንንት ፡ ከፈረሳቸው ፡ ሲጥል ፤ «ጥሩ ፡ ፈረሶች! ሁልጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ፈረሶች ፡ ስመኝ ፡ ነበር!» አለና ፡ ፈረሶቹን ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ ነድቶ ፡ እዚያ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ እንዲጠብቁለት ፡ ተናገረ ። ይህን ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ተመልሶ ፡ ከፈረሳቸው ፡ የጣላቸው ፡ መኳንንት ፡ ዘንድ ፡ ሔዶ ፡ አንዱን ፡ ወዲያው ፡ ገደለው ። አንደኛውን ፡ ደግሞ ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያለውን ፡ ጐራዴውንና ፡ ከኪሱ ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ወርቅ ፡ ከገፈፈው ፡ በኋላ ፤ አንገቱን ፡ በገመድ ፡ ጠልፎ ፡ የገመዱን ፡ ጫፍ ፡ ከኮርቻው ፡ ጋር ፡ አሰረና ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ እየጐተተ ፡ ወሰደው ።

ኮቢታ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ጥሩ ፡ ወጣት ፡ ኮዛክ ፡ ከአንድ ፡ የፖሊሽ ፡ ጐበዝ ፡ ጦረኛ ፡ ጋር ፡ ተጋጥመው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲዋጉ ፡ ቆዩ ። ወዲያው ፡ ኮዛኩ ፡ በፖሊሹ ፡ ላይ ፡ አየለበትና ፡ ጥሎ ፡ በሰላ ፡ የቱርክ ፡ ጮቤው ፡ ደረቱን ፡ ወጋው ። ግን ፡ ኮዛኩም ፡ አልቀረለትም ፡ ወዲያው ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ጆሮ ፡ ግንዱን ፡ ብሎ ፡ ጣለው ። ተኳሹም ፡ ከሁሉም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጨዋና ፡ ከሁሉም ፡ ያማረ ፡ መኮንን ፡ ነበር ። በታላቅ ፡ ግር

ማ ፡ በሃመር ፡ ፈረሱ ፡ ሆኖ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ እየተወረ
ወረ ፡ ብዙ ፡ ልዑላዊ ፡ ሞያ ፡ ፈጸመ ። ሁለቱን ፡ ኮዛኮች ፡ በጐ
ራዴ ፡ ሰነጠቃቸው ። ፌዮዶር ፡ ኮርዥ ፡ የተባለውን ፡ ጥሩ ፡
ኮዛክ ፡ መጀመሪያ ፡ ፈረሱን ፡ በጥይት ፡ ጥሎ ፡ በኋላ ፡ እሱን ፡
በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገደለው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የብዙዎችን ፡ አን
ገትና ፡ ክንድ ፡ የቆራረጠው ፡ ይህ ፡ መኮንን ፡ አሁን ፡ ኮዛ
ኩን ፡ ኮቢታን ፡ ጀሮ ፡ ግንዱን ፡ በጥይት ፡ መትቶ ፡ ገደለው ።
የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡
አይቶ ፡ ስለነበር ፡ «ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ነው ፡ ጉልበቴን ፡
መፈተን ፡ ያለብኝ!» ብሎ ፡ ጮኸ ። ወዲያው ፡ ፈረሱን ፡ ኮ
ለኮለና ፡ ከኋላው ፡ ጋልቦ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ሲ
ጮኽ ፡ በአቅራቢያው ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አንቀጠ
ቀጣቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የፖሊሹ ፡ መኮንን ፡ ዞሮ ፡ ጠላ
ቱን ፡ ለመግጠም ፡ ሲል ፡ ፈረሱ ፡ በጩኸቱ ፡ ደንብሮ ፡ ስለ
አስቸገረው ፡ ገና ፡ ከመዞሩ ፡ የኩኩቤንኮ ፡ ጥይት ፡ ትከሻውን ፡
መታና ፡ ከፈረሱ ፡ አውርዶ ፡ ጣለው ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ቢሆን ፡
ልቡ ፡ ሳይሸነፍ ፡ ጠላቱን ፡ ለመምታት ፡ ሞክሮ ፡ ነበር ። ግን ፡
ክንዱ ፡ ዝሎ ፡ ጐራዴውን ፡ ማንሳት ፡ እንኳን ፡ አልቻለም ።
በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ ሰይፉን ፡ አወጣና ፡ በተከፈተው ፡
በጠላቱ ፡ አፍ ፡ ጨመረው ። ሰይፉም ፡ የዚያን ፡ መኮንን ፡ እ
ንደ ፡ ስኳር ፡ የነጡ ፡ ሁለት ፡ ጥርሶች ፡ ሰብሮ ፤ ምላሱን ፡ ለሁ
ለት ፡ ሰንጥቆ ፤ አንገቱን ፡ አነካከተና ፡ አልፎ ፡ መሬት ፡ ውስ
ጥ ፡ ተሰካ ። መኮንኑን ፡ ከቀዝቃዛው ፡ መሬት ፡ ጋር ፡ ለዘለ
ዓለም ፡ ሰፋው ። በወንዝ ፡ ዳር ፡ እንደበቀለ ፡ ጽጌረዳ ፡ የቀ
ላው ፡ ልዑላዊ ፡ ደሙ ፡ እንደ ፡ ምንጭ ፡ እየገነፈለ ፡ በወር
ቀዘቦ ፡ የተዘመዘመውን ፡ ቢጫ ፡ ኮቱን ፡ በከለው ። ኩኩቤ
ንኮ ፡ የገደለውን ፡ መኮንን ፡ ትቶ ፡ ወደሌላ ፡ ዞረና ፡ ከው
ጊያው ፡ ተደባለቀ ።
የኡማን ፡ መንደር ፡ አለቃ ፡ ቦሮዳትይ ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡
ስለነበር ፤ «ይህን ፡ ያህል ፡ ሃብት ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡ ገድሎ ፡



ለምን ፡ ሳይማርከው ፡ ሄደ! እኔ ፡ ራሴ ፡ ሰባት ፡ መኳንንት ፡
በእጄ ፡ ገድያለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ በአንዳቸውም ፡ ላይ ፡ እንዲ
ሀ ፡ ያለ ፡ የከበረ ፡ ትጥቅ ፡ አላየሁም ፡» አለና ፡ ወደ ፡ ኩኩ
ቤንኮ ፡ ግዳይ ፡ ሄደ ።
ቦሮዳትይ ፡ በስስት ፡ ተታለለና ፡ የከበረውን ፡ የጦር ፡ ትጥ
ቅ ፡ ለመፍታት ፡ ጐንበስ ፡ አለ ። ወዲያው ፡ አንድ ፡ በአል
ማዝ ፡ ያጌጠ ፡ የቱርክ ፡ ጩቤ ፡ ከሬሳው ፡ ላይ ፡ አንስቶ ፤
እንዲሁም ፡ ወርቅ ፡ የያዘ ፡ ከረጢት ፡ ከቀበቶው ፡ ፈታ ፤
ከዚያም ፡ ያማረ ፡ መሃረብ ፤ ብዙ ፡ ብር ፤ እንዲሁም ፡ ለፍ
ቅር ፡ መታሰቢያ ፡ የተሰጠ ፡ የሴት ፡ ጸጉር ፡ ቁራጭ ፡ የያዘ ፡
ቦርሳ ፡ ሲያወልቅ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከፈረሱ ፡ አውርዶ ፡ በጐ
ራዴ ፡ መትቶ ፡ የተወውን ፡ አፍንጫ ፡ ቀይ ፡ ኮርኔት ፡ ከኋ
ላው ፡ ሲመጣበት ፡ አላየውም ። ኮርኔቱ ፡ ጐራዴውን ፡ ባለ ፡
ኃይሉ ፡ አንስቶ ፡ በአጐነበሰው ፡ በቦሮዳትይ ፡ አንገት ፡ ላይ ፡
አሳረፈው ። የኮዛኩ ፡ ስስት ፡ ምንም ፡ አልጠቀመውም ፤ አን
ገቱ ፡ ተቀንጥሶ ፡ ተወረወረ ፤ ቀሪ ፡ አካሉም ፡ ያለ ፡ ጭን
ቅላት ፡ ሲወድቅ ፡ ያካባቢውን ፡ ምድር ፡ በደም ፡ አቀላው ።
የኮዛክ ፡ ነፍሱም ፡ በራ ፡ ሔደች ። ኮርኔቱ ፡ የኮዛኩን ፡ አን
ገት ፡ በቁንጮው ፡ አንጠልጥሎ ፡ ኮርቻው ፡ ላይ ፡ ሊያስረ
ው ፡ ሲል ፡ ክፉ ፡ ደም ፡ መላሽ ፡ ከተፍ ፡ አለበት ።
ንስር ፡ አሞራ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ አንዣብቦ ፡ በሚያድ
ነው ፡ አውሬ ፡ ላይ ፡ ድንገት ፡ ትክል ፡ እንደሚልበት ፡ ሁሉ ፡
የታራስ ፡ ቡልባ ፡ ልጅ ፡ የእስታፕ ፡ ገመድ ፡ ሸምቀቆ ፡ በኮ
ርኔቱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አንዣበበና ፡ በአንገቱ ፡ ጥልቅ ፡ አለ ። ሸ
ምቀቆው ፡ በጉሮሮው ፡ ላይ ፡ እየጠበቀ ፡ ሲሔድ ፡ የኮርኔቱ ፡
ፊት ፡ ጠወለገ ፤ ሽጉጡን ፡ አውጥቶ ፡ ለመተኮስ ፡ ቢሞክር ፡
እጁ ፡ ሊያነጣጥርለት ፡ ስለአልቻለ ፡ ጥይቱ ፡ ባከኖ ፡ ቀረ ።
ከዚያ ፡ ኮርኔቱ ፡ ለምርኮኛ ፡ ማሠሪያ ፡ በኮርቻው ፡ ላይ ፡
ይዞት ፡ የነበረውን ፡ ገመድ ፡ እስታፕ ፡ ፈታና ፡ ኮርኔቱን ፡
እጅና ፡ እግሩን ፡ አስሮ ፡ የገመዱንም ፡ ጫፍ ፡ ከራሱ ፡ ኮርቻ ፡

ጋር ፡ አሰረና ፡ የኡማን ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ለአለቃቸው ፡ የመጨረሻ ፡ ክብር ፡ የሚደረገውን ፡ በቀል ፡ እንዲመለከቱ ፡ እየተጣራ ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ ይጐትተው ፡ ጀመር ።

የኡማን ፡ ኮዛኮች ፡ አለቃቸው ፡ መሞቱን ፡ እንደሰሙ ፡ ውጊያውን ፡ ትተው ፡ ሬሳውን ፡ ለማግኘት ፡ ሮጡና ፡ ወዲያው ፡ ሳይዘገዩም ፡ ለአለቅነት ፡ ማንን ፡ እንደሚመርጡ ፡ ይመካከሩ ፡ ጀመር ። በመጨረሻ ፡ ሁሉም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ ተስማሙ ። «ለምን ፡ በከንቱ ፡ እንከራከራለን? ከወጣቱ ፡ ከኦስታፕ ፡ ቡልባ ፡ የተሻለ ፡ አለቃ ፡ አናገኝም ፤ እርግጥ ፡ ነው ፡ በእድሜ ፡ ከሁላችን ፡ ያነሰ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ የሽማግሌ ፡ አእምሮ ፡ ነው ፡ የያዘው ፡» ተባባሉና ፡ እስታፕን ፡ ለመምረጥ ፡ ወሰኑ ።

ኦስታፕም ፡ በልጅነቱ ፡ ምክንያት ፡ ሥልጣኑን ፡ አልቀበልም ፡ ሳይል ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መግደርደር ፡ አስፈላጊ ፡ አለመሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ባርኔጣውን ፡ አውልቆ ፡ ስለተሰጠው ፡ ክብር ፡ ኮዛክ ፡ ጓደኞቹን ፡ አመስግኖ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ውጊያው ፡ መራቸውና ፡ አለቅነት ፡ የመረጡት ፡ በከንቱ ፡ አለመሆኑን ፡ በሞያ ፡ ገለጸላቸው ።

ፖሊሾቹ ፡ ውጊያው ፡ ከወዲያ ፡ ወገን ፡ ሲያይልባቸው ፡ ጊዜ ፡ እንደገና ፡ ተደራጅተው ፡ ለመዋጋት ፡ ወደኋላ ፡ በሩጫ ፡ ሸሹ ። ትንሹ ፡ ኮሎኔል ፡ በተጠባባቂነት ፡ ለብቻ ፡ የቆየውን ፡ የደጅን ፡ ጦር ፡ ለውጊያ ፡ ሲያዝዝ ፡ ጦሩም ፡ ወዲያው ፡ ተኩስ ፡ ከፈተና ፡ በኮዛኮቹ ፡ ላይ ፡ ጥይት ፡ አወረደባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ጥይቱ ፡ ዓይናቸው ፡ ፈጥጦ ፡ ውጊያውን ፡ የሚያስተውሉትን ፡ የኮዛክ ፡ በሬዎች ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ ሰው ፡ አልነካም ። በሬዎቹ ፡ በፍርሃት ፡ እየጮኹ ፡ ወደ ፡ ኮዛኮች ፡ ሰፈር ፡ ዞረው ፡ ሠረገላዎችን ፡ እየሰባበሩና ፡ ብዙም ፡ ሰው ፡ በእግራቸው ፡ እየረጋገጡ ፡ ፈረጠጡ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፡ ክፍለ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ ካደፈጠበት ፡ ቦታ ፡ ወጣና ፡ የበሬዎቹን ፡ መንገድ ፡ ዘጋባቸው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የደነበሩት ፡ በሬ



ዎች ፡ የታራስ ፡ ሰዎች ፡ ስላስደነገጧቸው ፡ ወደ ፡ ፖሊሾች ፡ ጦር ፡ ዞረው ፡ ፈረሰኞችን ፡ እየጣሉ ፡ እየረጋገጡ ፡ በታተኗቸው ።

ዛፖሮዥያኖቹም ፡ «ጐሽ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ በሬዎቻችን! በዘመቻ ፡ ላይ ፡ አገለገላችሁን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ረዳችሁ!» ብለው ፡ ጮኸው ፡ ጠላታቸውን ፡ በኃይል ፡ ይጣደፉ ፡ ጀመር ።

ከጠላት ፡ ጦር ፡ ብዙዎቹ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ሞቱ ። ብዙ ፡ ኮዛኮችም ፡ ሞያቸውን ፡ አሳዩ ። ፖሊሾቹ ፡ እንዳልሆነላቸው ፡ ስለተገነዘቡ ፡ የከተማው ፡ በር ፡ እንዲከፈት ፡ አስደረጉና ፡ አቧራ ፡ የለበሱት ፡ የደከሙ ፡ ፈረሰኞች ፡ እንደበግ ፡ ተግተልትለው ፡ ገቡ ። አንዳንድ ፡ ኮዛኮች ፡ በማባረር ፡ ተከትሏቸው ፡ ነበር ። አስታፕ ፡ ግን ፡ «ከግንቡ ፡ ራቁ! ጥሩ ፡ አይደለም ፡ አትቅረቡ ፤ ወንድሞቼ !» ብሎ ፡ በመጮኽ ፡ የኡማንን ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ አስቀራቸው ። እውነትም ፡ ደህና ፡ ታይቶት ፡ ኖሮአል ። በግንቡ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ተኩስ ፡ ስለከፈቱባቸው ፡ ግንቡን ፡ የቀረቡት ፡ ኮዛኮች ፡ ብዙ ፡ ጉዳት ፡ ደረሰባቸው ። ወዲያው ፡ ኮሼቮዩ ፡ ጋልቦ ፡ መጣና ፤ «እንዲህ ፡ ነው ፡ አለቃ ፡ ማለት ፡ ገና ፡ አዲስ ፡ ከመሾሙ ፡ መንደሩን ፡ ልክ ፡ እንደነባር ፡ ሆኖ ፡ ይመራል!» በማለት ፡ ኦስታፕን ፡ አመሰገነው ። ሽማግሌው ፡ ቡልባ ፡ ይህ ፡ የተባለው ፡ አለቃ ፡ ማን ፡ እንደሆን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ ኦስታፕ ፡ በኡማን ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ተመለከተ ። «ይኸውላችሁ ፡ ወንድ ፡ ማለት!» አለና ፡ ታራስ ፡ በአድናቆት ፡ ልጁን ፡ ከተመለከተው ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ ተደስቶ ፡ ልጁን ፡ ስለመረጡለት ፡ የኡማንን ፡ ኮዛኮች ፡ አመሰገናቸው ።

ኮዛኮቹ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ለመመለስ ፡ ሲያስቡ ፡ ፖሊሾቹ ፡ በከተማው ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ እንደገና ፡ ብቅ ፡ አሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የቀድሞው ፡ ጌጥ ፡ ሁሉ ፡ ተበላሽቷል ።

ብዙ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶች ፡ በደም ፡ ተበክለዋል ፤ የሚያምሩትን ፡ የነሃስ ፡ ጥሩሮችም ፡ አቧራ ፡ ሸፍኖአቸዋል ።

ከግንቡ ፡ ሥር ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፤ «ታድያስ ፡ እንደ ፎከራችሁት ፡ አሰራችሁን ፡ እንዴ?» እያሉ ፡ ጮኹ ። ወፍራሙ ፡ ኮሎኔልም ፡ በእጁ ፡ የያዘውን ፡ ገመድ ፡ እያወዛወዘ ፡ የቀድሞ ፡ ዛቻውን ፡ በመድገም ፡ «ቆይ ፡ አሳያችኋለሁ!» ብሎ ፡ በቁጣ ፡ ጮኸ ። በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ያሉት ፡ አቧራ ፡ የለበሱና ፡ የደከሙ ፡ ጠረኞች ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ መዛታቸውን ፡ ቀጠሉ ። አንዳንድ ፡ ንዴተኞችም ፡ ስድብ ፡ ይለዋወጡ ፡ ነበር ።

በመጨረሻ ፡ ሁሉም ፡ ረጋ ፡ አሉ ። አንዳንዶቹ ፡ በውጊያ ፡ ደክመው ፡ ለማረፍ ፡ ጋደም ፡ ሲሉ ፡ ሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ቁስላቸው ፡ ላይ ፡ አፈር ፡ እየነሰነሱ ፡ ከጠላት ፡ ሬሳ ፡ በሚቀዱት ፡ ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ጨርቅ ፡ ይጠቀልሉ ፡ ጀመር ። አንዳንድ ፡ በፍጹም ፡ ያልደከሙ ፡ ግን ፡ የሞቱትን ፡ ቀብር ፡ ያዘጋጁ ፡ ጀመር ። ጉድጓዱ ፡ በጐራዴና ፡ በእንካሴ ፡ እየተቆፈረ ፡ አፈሩንም ፡ በቆባቸውና ፡ በኮታቸው ፡ እያወጡ ፡ የወደቁት ፡ ኮዛኮች ፡ ሬሳ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ተጋድሞ ፡ ጩካኞች ፡ አሞሮች ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ እንዳያነቁሩት ፡ አፈር ፡ ለበሰ ። የፖሊሾች ፡ ሬሳ ፡ ግን ፡ ተሰብስቦ ፡ በደንባሪ ፡ ፈረሶች ፡ ጭራ ፡ ላይ ፡ ከታሰረ ፡ በኋላ ፡ ፈረሶቹን ፡ አስደንብረው ፡ በሜዳው ፡ ለቀቋቸው ። ፈረሶቹም ፡ በአቧራ ፡ የተለወሱትን ፡ የፖሊሾቹን ፡ ሬሳዎች ፡ እየጐተቱ ፡ በዳገት ፤ በቁልቁለት ፤ በጉድጓድና ፡ በወንዞችም ፡ አልፈው ፡ እየጋለቡ ፡ ጠፉ ።

ከዚያ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ወደ ፡ እራት ፡ ተሰማሩ ። ሌሊቱንም ፡ በውጊያው ፡ ላይ ፡ ስለደረሰባቸው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሲወያዩ ፡ ቆዩ ። የያንዳንዳቸው ፡ የጦር ፡ ሞያ ፡ ሲነሳና ፡ ሲወራ ፡ ብዙ ፡ አመሹ ። ታራስም ፡ አንድሬይ ፡ ከጠላት ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ስላለመኖሩ ፡ ጉዳይ ፡ ሲያሰላስል ፡ አመሸ ። ያ ፡ ይሁዳ ፡ በገዛ ፡ ወገኖቹ ፡ ላይ ፡ ለመሰለፍ ፡ አፍሮ ፡ ቀርቶ ፡ ይሆን ፡ ወይስ ፡



አንድሬይ ፡ እንዲሁ ፡ ተማርኮ ፡ ተወስዶ ፡ አይሁዱ ፡ ያንኪል ፡ ዋሽቶ ፡ ይሆን? ግን ፡ ወዲያው ፡ የአንድሬይ ፡ ልብ ፡ በአንድ ፡ ሴት ፡ ቃል ፡ ቶሎ ፡ እንደሚወላውል ፡ አስታውሶ ፡ ታራስ ፡ በኃዘን ፡ ተዋጠ ። ወጥመድ ፡ ባገባችው ፡ ፖሊሽ ፡ ሴት ፡ ላይም ፡ በቀሉን ፡ ለመወጣት ፡ ማለ ። ቢሆንለት ፡ ይህን ፡ መሃላውን ፡ ከመፈጸም ፡ የሚመለስ ፡ አይደለም ። ቢያገኛት ፡ ውበትዋንም ፡ ባልተመለከተ ፡ ነበር ። የተዋበውን ፡ ጸጉርዋን ፡ አስሮ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ እንዲያዩዋት ፡ ሜዳ ፡ ለሜዳ ፡ እንደሚጐትታት ፡ አይጠረጠርም ። በተራራ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ንጹህ ፡ በረዶ ፡ የነጡት ፡ ጡቶችዋና ፡ ትከሻዋ ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ሲንገላቱ ፡ በደምና ፡ በአቧራ ፡ በተለወሱ ፡ ነበር ። ያን ፡ የተዋበ ፡ ለጋ ፡ አካልዋን ፡ ቆራርጦ ፡ በጣለው ፡ ነበር ። ግን ፡ ቡልባ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነገ ፡ ምን ፡ እንዳሰበ ፡ ሊያውቅ ፡ አይችልም ። በመጨረሻ ፡ እናወዘውና ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው ።

ኮዛኮቹ ፡ አሁንም ፡ ያወጋሉ ። ንቁዎቹ ፡ ዘበኞችም ፡ ሌሊቱን ፡ ሙሉ ፡ ለዘብ ፡ ጥበቃ ፡ በነደዱት ፡ ደመራዎች ፡ አጠገብ ፡ ቆመው ፡ በትጋት ፡ ይጠብቃሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ስምንት ።

ገና ፡ ጀንበር ፡ ከፍ ፡ ሳትል ፡ ዛፖሮገርያኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ለምክር ፡ ተሰበሰቡ ። ኮዛኮቹ ፡ ሴቹን ፡ ለቀው ፡ በዘመቱበት ፡ ታታሮች ፡ መጥተው ፡ ሰፈሩን ፡ ዘርፈው ፡ የተከማቸውን ፡ ሃብት ፡ ሁሉ ፡ በዝብዘው ፡ በዚያ ፡ የነበሩትን ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ገድለውና ፡ ማርከው ፡ የከብትና ፡ የፈረሶችን ፡ መንጋም ፡ እየነዱ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፔሬኮፕ ፡ ሔደዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ተሰማ ። ማክሲም ፡ ጐሎዱኻ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ብቻ ፡ ከመንገድ ፡ ሚርዛውን ፡ ገድሎ ፡ ከታታሮች ፡ አምልጦ ፡ የታታር ፡ ልብስ ፡ ለብሶና ፡ በታታር ፡ ፈረስ ፡ እየጋለበ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡

ተከሉልና ፡ ሁለት ፡ ሌሊት ፡ ተጉዞ ፡ ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ዱብኖ ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ መሰፈራቸውን ፡ ስለሰማ ፡ ከሰፈራቸው ፡ ደረሰ ። እንደደረሰም ፡ የሆነውን ፡ ጉዳት ፡ ከመናገር ፡ በቀር ፡ አመጣጡ ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ ኮዛኮቹ ፡ እንደተለመደው ፡ አለመጠን ፡ ጠጥተው ፡ በስካር ፡ እንዳሉ ፡ ተይዘው ፡ እንደሆነ ፤ ታታሮቹም ፡ የተደበቀውን ፡ የጦር ፡ ሰራዊቱን ፡ ሃብት ፡ እንዴት ፡ እንዳገኙት ፡ ለማስረዳት ፡ አልቻለም ። በድካም ፡ ጉልበቱ ፡ ዝሎ ፡ ሰውነቱ ፡ ሁሉ ፡ አብጦ ፡ ፊቱም ፡ በነፋስ ፡ ተጠብሶና ፡ ተላልጦ ፡ ስለነበር ፡ ወዲያው ፡ እንደደረሰ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰደው ።

እንዲህ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ዘራፊዎቹን ፡ ተከታትሎ ፡ መያዝ ፡ በኮዛኮቹ ፡ ዘንድ ፡ የተለመደ ፡ ነበር ። አለዚያ ፡ ግን ፡ እስረኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ በእስያ ፡ ማይነር ፤ በስማርነና ፡ ወይም ፡ በክሬት ፡ ደሴት ፡ ወደሚገኙት ፡ የባርያ ፡ ገበያዎች ፡ ይላካሉ ። አሁን ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ ለምክር ፡ የተሰበሰቡት ፡ ለዚሁ ፡ ነው ። በአሁኑ ፡ ስብሰባ ፡ የመጡት ፡ ከአለቆቻቸው ፡ ትእዛዝ ፡ ለመቀበል ፡ ሳይሆን ፡ በእኩልነት ፡ እርስ ፡ በእርሳቸው ፡ ለመመካከር ፡ ስለሆነ ፡ ሁሉም ፡ ቆባቸውን ፡ ሳያወልቁ ፡ ቆሙ ።

«ሽማግሌዎች ፡ በመጀመርያ ፡ ምክራቸውን ፡ ይስጡ!» እያሉ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሲጮሁ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ «ኮሼቮይ ፡ ምክርህን ፡ ስጠን!» ይሉ ፡ ጀመር ።

ኮሼቮዩም ፡ ቆቡን ፡ አውልቆ ፡ እንደ ፡ አለቃቸው ፡ ሳይሆን ፡ እንደ ፡ ጓደኛቸው ፡ ሆኖ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ስለሰጡት ፡ ክብር ፡ በትህትና ፡ ካመሰገናቸው ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ከኔ ፡ ይበልጥ ፡ አዋቂዎችና ፡ የበሰሉ ፡ ሰዎች ፡ በመካከላችን ፡ ይገኛሉ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ የመናገሩን ፡ ክብር ፡ ለኔ ፡ ከሰጣችሁኝ ፡ ምክሬ ፡ ይህ ፡ ነው ። የታታሮችን ፡ ነገር ፡ ሁላችሁም ፡ ስለምታውቁት ፡ አሁን ፡ ምንም ፡ ጊዜ ፡ ሳናባክን ፡ ብንከተላቸው ፡ ይሻላል ። ታታ



ሮች ፡ እኛን ፡ አይጠብቁንም ፤ የዘረፉትን ፡ ሃብት ፡ ሁሉ ፡ ወዲያው ፡ በታትነው ፡ ያጠፉትና ፡ ምልክት ፡ እንኳን ፡ አናገኝም ። ፖሊሾቹ ፡ አሁን ፡ ኮዛኮች ፡ ማን ፡ እንደሆንን ፡ ተገንዝበውታል ፤ በሃይማኖታችን ፡ ላይ ፡ የተፈጸመውን ፡ በደል ፡ በተቻለን ፡ ተበቅለነዋል ። ይህ ፡ የተራበ ፡ ከተማም ፡ ምንም ፡ የሚጠቅመን ፡ አይደለም ፡ ስለዚህ ፡ የኔ ፡ ምክር ፡ ዘራፊዎቹን ፡ ተከትለን ፡ እንድንሔድ ፡ ነው ።»

«እንሒድ !» እያሉ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጮሁ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ቃላት ፡ ታራስ ፡ ቡልባን ፡ አላስደሰቱትም ። ሽበት ፡ ጣል ፡ ጣል ፡ ያደረገባቸውን ፡ ቅንድቦቹ ፡ ኮስትሮ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«የለም ፡ ምክርህን ፡ ጥሩ ፡ ምክር ፡ አይደለም ፤ እንዲህ ፡ ልትል ፡ አይገባም ፤ እንደሚመስለኝ ፡ ተማርከው ፡ እዚሁ ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ ያሉትን ፡ ጓደኞቻችንን ፡ ረስተሃቸዋል ። ተቀዳሚውንና ፡ የተቀደሰውን ፡ የጓደኝነት ፡ ሕግ ፡ ጥሰን ፡ ኮዛክ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ የኡክሬይን ፡ ሩሲያውያን ፡ መኳንንት ፡ ላይ ፡ እንደደረሰው ፡ ሁሉ ፡ በቁማቸው ፡ ተሰቃይተውና ፡ ተቆራርጠው ፡ እንዲቀሩ ፡ የፈለግህ ፡ ትመስላለህ ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ሰዎች ፡ እንባላለን ፡ እስቲ ፡ ልጠይቅህ? ጓደኛው ፡ በባዕድ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ወድቆ ፡ እንዲቀር ፡ ትቶ ፡ የሚሔድ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ኮዛክ ፡ ነው? የኮዛክነት ፡ ክብራችሁን ፡ መጠበቅ ፡ ከተዋችሁና ፡ መስደብን ፡ ከፈለጋችሁ ፡ እኔን ፡ ይቅርታ ፡ አድርጉልኝ ፡ እኔ ፡ ብቻዬንም ፡ ቢሆን ፡ እዚሁ ፡ እቀራለሁ!»

ዛፖሮዥያኖቹ ፡ ሁሉ ፡ ሃሳባቸው ፡ ወለወለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኮሼቮዩ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ጀግናው ፡ ኮሎኔል ፡ ሆይ ፤ በታታሮች ፡ እጅም ፡ ጓደኞቻችን ፡ መኖራቸውንና ፡ እኛ ፡ ካልደረስንላቸው ፡ ለእድሜ ፡ ልክ ፡ ባርነት ፡ ለከሃዲዎች ፡ እንደሚሸጡ ፡ ይህም ፡ ከ

8—401

ማናቸውም ፡ ከፉ ፡ ሞት ፡ የባሰ ፡ እድል ፡ መሆኑን ፡ ረስተ
ሽው ፡ ይሆን? በክርስቲያን ፡ ደማችን ፡ ያፈራነውን ፡ ሃብት ፡
ዘርፈው ፡ መውሰዳቸውን ፡ ረስተሽዋልን?»

ኮዛኮቹ ፡ የሁለቱን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ንግግር ፡ እያሰላሰሉ ፡
የሚናገሩት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ሁሉም ፡ በስማቸውና ፡ በክብ
ራቸው ፡ እንከን ፡ እንዲደርስበት ፡ አልፈለጉም ። ከዚያ ፡ በዛ
ፖሮዥያን ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውስጥ ፡ የሁሉ ፡ ታላቅ ፡ የሆ
ነው ፡ ካሲያን ፡ ቦቭዲዩግ ፡ ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ቀረበ ። ይህ ፡
ሰው ፡ በኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ የተከበረና ፡ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ኮሼ
ቮይ ፡ ሆኖ ፡ የተመረጠ ፡ ነው ። በጦር ፡ ሜዳም ፡ እንደ ፡ ማና
ቸውም ፡ ጐበዝ ፡ ኮዛክ ፡ በጊዜው ፡ ብዙ ፡ ሞያ ፡ ሠርቶአል ።
አሁን ፡ ግን ፡ ስለአረጀ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ተካፋይነቱን ፡ ትቶ ፡
ምክርም ፡ መስጠት ፡ ስለማይፈልግ ፡ በኮዛኮቹ ፡ መሃል ፡ ተጋ
ድሞ ፡ ስለጦርነትና ፡ ስለጀብዱ ፡ ሲወራ ፡ ማዳመጥ ፡ እንጂ ፡
ምንም ፡ አይናገርም ። ከዚህ ፡ ቀደም ፡ በተደረጉት ፡ ዘመቻ
ዎች ፡ ከሰፈር ፡ አልወጣም ፡ ነበር ። በአሁኑ ፡ ዘመቻ ፡ ግን ፡
ሽማግሌው ፡ ኮዛክ ፡ ወኔው ፡ አላስችል ፡ ስላለው ፡ «የሆነው ፡
ይሁን ፡ እንጂ ፡ አብሬአችሁ ፡ እሄዳለሁ ፡ ለኮዛክነት ፡ ክብር ፡
ገና ፡ ሳላገለግል ፡ አልቀርም!» ብሎ ፡ መጣ ።

አሁን ፡ ምክር ፡ ለመስጠት ፡ ሲነሳ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ ጸጥ ፡
አሉ ፤ ሲናገር ፡ ከሰሙት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አልፎአል ። ቦቭዲ
ዩግ ፡ ምን ፡ እንደሚል ፡ ለመስማት ፡ ሁሉም ፡ ጓጉ ።

እሱም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ንግግሩን ፡ ጀመረ ፤

«ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፡ ሆይ ፤ ምክሬን ፡ የምሰጥበት ፡
ጊዜው ፡ እነሆ ፡ ደረሰ ። ልጆቼ ፡ ሆይ ፤ የሽማግሌ ፡ ቃሌን ፡
አዳምጡኝ ። የኮሼቮዩ ፡ ንግግር ፡ በእውነትም ፡ የአዋቂ ፡ ንግ
ግር ፡ ነው ። የጦር ፡ ሠራዊቱንና ፡ ሃብቱንም ፡ የመጠበቅ ፡ ግ
ዴታ ፡ ያለበት ፡ የኮዛኮች ፡ መሪ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ የተ
ናገረው ፡ ተገቢ ፡ ነው ። ይህ ፡ ነው ፡ የመጀመሪያ ፡ ንግግሬ ፤
ሁለተኛው ፡ ንግግሬ ፡ ደግሞ ፡ የሚከተለው ፡ ነው ። ኮሎኔ



ል ፡ ታራስ ፡ የተናገረው ፡ ቃልም ፡ ታላቅ ፡ እውነትን ፡ የተመ
ረኰዘ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ ረጅም ፡ እድሜ ፡ ይስጠው ።
ለኡክሬይንም ፡ እንደሱ ፡ ያሉ ፡ ኮሎኔሎች ፡ አያሳጣት! የኮ
ዛኮች ፡ ተቀዳሚ ፡ ተግባርና ፡ ክብር ፡ ለጓደኞቻቸው ፡ ታማኝ ፡
ሆነው ፡ መገኘት ፡ ነው ። በዚህ ፡ በረጅሙ ፡ እድሜዬ ፡ ውስ
ጥ ፡ አንድ ፡ ኮዛክ ፡ ጓደኛውን ፡ ሲከዳ ፡ ሰምቼ ፡ አላውቅም ።
እዚህ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮችና ፡ ከሴቹም ፡ የተማረኩት ፡ ሁሉም ፡
ጓደኞቻችን ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ሆነ ፡ በዚያ ፡ የቁጥራቸው ፡
ማነስ ፡ ወይም ፡ መብዛት ፡ ልዩነት ፡ አያመጣም ። ሁሉም ፡
ጓደኞቻችንና ፡ ሁሉም ፡ የምንወዳቸው ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡
ምክሬ ፡ ይህ ፡ ነው ። በታታሮች ፡ እጅ ፡ ያሉት ፡ እስረኞች ፡
ይበልጡብናል ፡ የሚሉ ፡ ታታሮቹን ፡ ይከተሉ ፤ በፖሊሾ
ቹ ፡ እጅ ፡ ያሉት ፡ እስረኞች ፡ ይበልጡብናል ፡ የሚሉም ፡ እዚ
ሁ ፡ ይቅሩ ። ታታሮቹን ፡ ተከትለው ፡ የሚዘምቱትን ፡ ኮሼ
ቮዩ ፡ ይምራ ። የሚቀሩት ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ኮሼቮይ ፡
ይምረጡ ። ደግሞ ፡ የሽማግሌ ፡ ምክሬን ፡ ብታዳምጡኝ ፡
ለቀሪዎቹ ፡ ኮሼቮይ ፡ ለመሆን ፡ ከታራስ ፡ ቡልባ ፡ የተሻለ ፡
ማንም ፡ ሰው ፡ አይገኝም ። በጉብዝና ፡ ማናችንም ፡ ብንሆን ፡
እሱን ፡ አናክልም!»

ቦቭዲዩግ ፡ ይህን ፡ ተናገረና ፡ ዝም ፡ አለ ። ኮዛኮቹም ፡
ከዚህ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛክ ፡ በቀረበው ፡ ምክር ፡ ተደሰቱ ። ሁሉ
ም ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየወረወሩ ፡
«ተባረክ ፡ ባትኮ! ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ ብለህ ፡ ኖረህ ፡ በመጨ
ረሻ ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ተናገርክ! ለኮዛክነት ፡ ክብር ፡ ገና ፡ አገ
ለግላለሁ ፡ በማለት ፡ የሰጠኸው ፡ ቃል ፡ በከንቱ ፡ አልቀረ
ም!» እያሉ ፡ ጮሁ ።

«ታዲያ ፡ ሁላችሁም ፡ በዚህ ፡ ተስማምታችኋል?» ሲል ፡
ኮሼቮዩ ፡ ጠየቀ ።

ኮዛኮቹም ፡ «አዎ ፡ ተስማምተናል!» ብለው ፡ ጮሁ ።

«እንግዲያው ፡ ሸንጐው ፡ ተፈጸመ ፡ ማለት ፡ ነው?»

«አዎ ፡ ተፈጸመ ።»

«እንግዲያው ፡ ልጆቼ ፡ ትእዛዜን ፡ አዳምጡ!» አለና ፡ ኮሼቮዩ ፡ ቆቡን ፡ አድርጎ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ቆመ ። ዛፖሮዥያኖቹም ፡ አንድ ፡ መሪ ፡ ሲናገር ፡ እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ መሬት ፡ መሬት ፡ እያዩ ፡ ቆሙ ። ኮሼቮዩ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«አሁን ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፡ ተከፋፈሉ! ለመሔድ ፡ የምትፈልጉ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፤ ለመቅረት ፡ የምትፈልጉ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ተለዩ! የአንድ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ አብዛኛው ፡ የመንደሩ ፡ ጦር ፡ ወደሔደበት ፡ ይደባለቃል ። ቀሪው ፡ አነስተኛው ፡ የዚያ ፡ መንደር ፡ ጦርም ፡ ከሌላ ፡ መንደር ፡ ጋር ፡ ይደባለቃል ።»

ወዲያው ፡ እንደታዘዙት ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ተከፍለው ፡ ቆሙ ። እንደ ፡ አጋጣሚ ፡ ሆኖ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ በቁጥር ፡ ምንም ፡ አልተበላለጡም ። ለመቅረት ፡ የፈለጉት ፡ አብዛኛው ፡ ኔዛማይ ፡ መንደር ፡ የኡማንና ፡ የካኔቭ ፡ መንደሮች ፡ በሙሉ ፡ እንዲሁም ፡ ከፖፖቪች ፡ ከስቴብሊኮቭና ፡ ከቲሞሼቭካ ፡ መንደሮች ፡ አብዛኞቹ ፡ ናቸው ። የቀሩት ፡ ታታሮቹን ፡ ተከትሎ ፡ ለመዝመት ፡ መረጡ ። በሁለቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ጀግናና ፡ ብርቱ ፡ ኮዛኮች ፡ ነበሩ ። ታታሮቹን ፡ ተከትሎ ፡ ለመሔድ ፡ ከመረጡት ፡ ውስጥ ፡ ቼሬቫቲ ፡ ፖኮቲፖሌ ፡ ሌሚሽ ፡ እንዲሁም ፡ ኹማ ፡ ፕሮኮፖቪች ፡ ይገኙ ፡ ነበር ። ዴሚድ ፡ ፖፖቪችም ፡ በአንድ ፡ ሥፍራ ፡ ብዙ ፡ ለመቆየት ፡ የማይችል ፡ ቅብጥብጥ ፡ ኮዛክ ፡ ስለነበር ፡ ከነሱው ፡ ጋር ፡ ለመሄድ ፡ ተነስቶአል ። ከፖሊሾች ፡ ጋር ፡ ጦርነቱን ፡ አይቶ አልና ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከታታሮች ፡ ጋር ፡ ለመሞካከር ፡ ፈለገ ። ሌሎች ፡ ብዙ ፡ ጀግናና ፡ ባለዝና ፡ ኮዛኮችም ፡ እንዲሁም ፡ ከአለቆች ፡ መካከል ፡ ኖስትዩጋን ፡ ፖክሪሽካ ፤ ኔቬሊችኪ ፡ ከታታሮች ፡ ጋር ፡ ገጥመው ፡ ጉራዴና ፡ ጡንቻቸውን ፡ ለመሞከር ፡ ፈቅደው ፡ ተነሱ ። ከሚቀሩት ፡ ኮዛኮች ፡ መካከልም ፡



ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ ነበሩ ። የጦር ፡ አለቆች ፡ የሆኑ ፡ ዴሚትሮቬች ፤ ኩኩቤንኮ ፤ ቬርቲኽቪስት ፤ ባላባን ፤ አስታፕ ፡ ቡልባና ፡ ሌሎችም ፡ ባለዝና ፡ ኮዛኮች ፡ እነ ፡ ቮቭቱዜንኮ ፤ ቼሬቪቼንኮ ፤ እስቴፋን ፡ ጉስካ ፤ ኦኽሪም ፡ ጉስካ ፤ ሚኮላ ፡ ጉስቲይ ፤ ዛዶሮዥኒይ ፤ ሜቴሊትሳ ፤ ኢቫን ፡ ዛክሩቲጉባ ፤ ሞሲይ ፡ ሺሎ ፤ ዴክቲያሬንኮ ፤ ሲዶሬንኮ ፤ ፒሳሬንኮ ፤ ሁለተኛው ፡ ፒሳሬንኮ ፤ ደግሞ ፡ ሌላው ፡ ሶስተኛ ፡ ፒሳሬንኮ ፤ ሌሎችም ፡ ጥሩ ፡ ጥሩ ፡ ኮዛኮች ፡ እዚያው ፡ ቀርተው ፡ ከፖሊሾች ፡ ጋር ፡ ለመዋጋት ፡ ቆረጡ ። ሁሉም ፡ በብዙ ፡ ሥፍራ ፡ የተጓዙና ፡ የዘመቱ ፡ ናቸው ። በአናቶሊያ ፡ ወደቦች ፤ በክራይሚአ ፡ ጨሬና ፡ መስኮች ፤ ከድኔፕር ፡ ከሚቀላቀሉት ፡ ትንሽና ፡ ትልቅ ፡ ወንዞችም ፤ ያልተጓዙበትና ፡ ያልደረሱበት ፡ ሥፍራ ፡ አልነበረም ። ሞልዳቪያን ፤ ዋላኪያንና ፡ የቱርክንም ፡ አገር ፡ ጐብኝተዋል ። በኮዛክ ፡ ጀልባዎቻቸው ፡ በጥቁር ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ እየተጓዙ ፡ ሃምሳ ፡ ጀልባ ፡ ሆነው ፡ ብዙ ፡ የከበሩና ፡ ታላላቅ ፡ መርከቦችን ፡ እየወጉ ፡ ብዙ ፡ የቱርክ ፡ መርከቦች ፡ አስምጠዋል ። በጊዜያቸው ፤ ብዙ ፤ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ባሩድ ፡ የተኮሱ ፡ ናቸው ። ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ ደጋግመው ፤ ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የሐርና ፡ የከፈይ ፡ ጨርቆችን ፡ ለእግራቸው ፡ ገንባሌ ፡ ቀድደዋል ። ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜም ፡ ደጋግመው ፡ በቀበቷቸው ፡ የተንጠለጠሉትን ፡ ከረጢቶች ፡ በወርቅ ፡ ሞልተው ፡ ነበር ። በመጠጥና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ያጠፉትም ፡ ገንዘብ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተብሎ ፡ ሊታወቅ ፡ ያዳግታል ። በሌላ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ እነሱ ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ የሚያባክኑት ፡ ሃብት ፡ ለዕድሜ ፡ ልክ ፡ መተዳደሪያ ፡ በበቃ ፡ ነበር ። እነሱ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ እየጋበዙ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ እንዲደሰት ፡ ዛፋኝ ፡ ሙዚቀኞች ፡ እየቀጠሩ ፡ በዕውነተኛው ፡ የኮዛክ ፡ ባሕል ፡ አባከኑት ። አሁንም ፡ እንኳን ፡ አንዳንዶቹ ፡ ምንም ፡ ቅርስ ፡ የላቸውም ። ድንገት ፡ በሌለንበት ፡ ወራሪ ፡ የመጣ ፡ እንደሆን ፡ በማለት ፡ በድኔፐር ፡ ደሴቶች ፡ በቄጠ

ማ ፡ መካከል ፡ የቀበሩዋቸውን ፡ የብር ፡ ጽዋዎች ፤ የወርቅ ፡ ድሪና ፡ አልቦዎች ፡ ታታሮቹ ፡ ለማግኘት ፡ ያዳግታቸዋል ። ራሳቸው ፡ ኮዛኮቹ ፡ እንኳን ፡ ሃብታቸውን ፡ የቀበሩበትን ፡ ሥፍራ ፡ መዘንጋት ፡ ጀምረዋል ። ለታማኝ ፡ ጓደኞቻቸውና ፡ ለክርስቲያንነት ፡ ሃይማኖት ፡ ሲሉ ፡ እዚህ ፡ ቀርተው ፡ ፖሊሾቹን ፡ ለመበቀል ፡ የቆረጡት ፡ ኮዛኮች ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ።

ሽማግሌው ፡ ኮዛክ ፡ ቦቭዲዩግም ፡ አብሯቸው ፡ ለመቅረት ፡ ወስኖ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ታታሮቹን ፡ ለማባረር ፡ ዕድሜዬ ፡ አይፈቅድልኝም ። ስለዚህ ፡ ዕውነተኛ ፡ የኮዛክ ፡ ሞት ፡ ለመሞት ፡ የምችልበት ፡ ሥፍራ ፡ እዚህ ፡ ነው ። የመሞቻዬ ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ለተቀደሰው ፡ ለክርስትና ፡ ሃይማኖት ፡ ስዋጋ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ እንድሞት ፡ ዘወትር ፡ ለአምላክ ፡ ስፀልይ ፡ ነበር ። ይኸው ፡ ፀሎቴ ፡ ሠመረልኝ ። ለአንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ኮዛክ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የክብር ፡ ሞት ፡ በየትም ፡ አይገኝም ።»

ሁሉም ፡ በየመንደር ፡ የጦር ፡ ክፍላቸው ፡ ተከፋፍለው ፡ በሁለት ፡ መሥመር ፡ ከተሰለፉ ፡ በኋላ ፡ ኮሼቮይው ፤ በመካከላቸው ፡ እየሄደ ፤ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፤ ሁሉም ፡ ወገን ፡ ተደስቷልን?» አላቸው ።

ኮዛኮቹም ፤ «ሁላችንም ፡ ተደስተናል ፤ ባትኮ!» ብለው ፡ ጮኹ ።

«በሉ ፡ እንግዲያው ፡ ተሳሳሙና ፡ ተሰነባበቱ ። ከእንግዲህ ፡ መገናኘታችሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚያውቀው ። በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ መሪያችሁን ፡ አዳምጡ ፤ የኮዛክነት ፡ ክብራችሁ ፡ የሚጠይቀውን ፡ ተግባር ፡ ሁሉ ፡ በሚገባ ፡ ፈጽሙ ።»

ከዚያ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ በአንድ ፡ ተሳሳሙ ። መጀመሪያ ፡ አለቆቹ ፡ ጉንጭ ፡ ለጉንጭ ፡ ተሳስመው ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡ መጨባበጥ ፡ ጀመሩ ። ሁለት ፡ አለቆች ፡ እጅ ፡ ለእጅ ፡



ተጨባብጠው ፡ ሲቆሙ ፤ ሁለቱም ፡ በየበኩላቸው ፤ «እንደገና ፡ እንገናኝ ፡ ይሆን ፡ ወንድሜ ፡ መኳንንት?» ብሎ ፡ ለመጠየቅ ፡ ሳይፈልጉ ፡ አልቀሩም ። ግን ፡ ይህ ፡ በሸበቶ ፡ ራሳቸው ፡ ውስጥ ፡ በሃሳብ ፡ ይጉላላ ፡ እንጂ ፡ አንዳቸውም ፡ ገልፀው ፡ አልተናገሩትም ። በአለቆቹ ፡ ዙሪያ ፡ ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ሁሉ ፡ ይሰነባበቱ ፡ ነበር ። ሁሉም ፡ በየበኩላቸው ፡ ያለባቸውን ፡ ከባድ ፡ ተግባር ፡ ቢገነዘቡትም ፡ ፖሊሾቹ ፡ መከፋፈላቸውን ፡ እንዳያውቁባቸው ፡ በማለት ፤ ከመጨለሙ ፡ በፊት ፡ እንዳይለያዩ ፡ ወሰኑ ። ከዚያ ፡ ሁሉም ፡ በጊዜ ፡ ራት ፡ ለመብላት ፡ ወደየሰፈራቸው ፡ ሄዱ ።

ከራት ፡ በኋላ ፡ መንገደኞቹ ፡ ያለ ፡ ስጋት ፡ ለመተኛት ፡ ይህ ፡ የመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ሆነ ፡ እንደታያቸው ፡ ሁሉ ፤ ወዲያው ፡ ተኝተው ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ወሰዳቸው ። ፀሐይ ፡ እስክትጠልቅ ፡ ድረስ ፡ ተኙ ። ፀሐይ ፡ ጠልቃ ፡ ሲጨልምም ፤ ተነሱና ፡ ሠረገላዎቻቸውን ፡ ዘይት ፡ ማጠጣትና ፡ ማዘጋጀት ፡ ጀመሩ ፤ ሁሉም ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፤ ሁሉም ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ ቀሪዎቹን ፡ ጓደኞቻቸውን ፡ ተሰናበቱና ፡ በዝግታ ፡ ሠረገላዎቹን ፡ ተከትለው ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ። ፈረሰኞቹ ፡ ኋላ ፡ ኋላ ፤ ቀስ ፡ ብለው ፡ በማኮብኮብ ፡ እርምጃ ፡ እየተጓዙ ፡ አንድም ፡ ጫጫታ ፡ ወይም ፡ ፉጨት ፡ ሳይሰማ ፡ ሁሉም ፡ በጨለማው ፡ ተሠወሩ ። ከፈረሶቹ ፡ ኮቴና ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በቂ ፡ ዘይት ፡ ሳያገኙ ፡ ከቀሩ ፡ የሠረገላ ፡ መሽከርከሪያዎች ፡ ድምጽ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ምንም ፡ ድምጽ ፡ አይሰማም ፡ ነበር ።

ምንም ፡ እንኳን ፡ መንገደኞቹ ፡ በጨለማው ፡ ተውጠው ፡ ባይታዩም ፤ ቀሪዎቹ ፡ ጓደኞቻቸው ፡ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ እጃቸውን ፡ ሲያወዛወዙላቸው ፡ ቆዩ ። ወዲያው ፡ ቀሪዎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ወደየሥፍራቸው ፡ ተመልሰው ፡ በከዋክብት ፡ ብርሃን ፡ አካባቢውን ፡ ሲመለከቱ ፤ የጦር ፡ ሠራዊቱ ፡ ሠረገላዎች ፡ እኩሌታ ፡ መሄዱንና ፡ እንዲሁም ፤ ብዙዎቹ ፡ ጓደ

ኞቻቸው ፡ ከመካከላቸው ፡ አለመኖራቸውን ፡ ተገንዝበው ፤ ልባቸው ፡ አዘነ ። ደስተኛው ፡ መንፈሳቸውም ፡ ተከዞ ፤ በሃሳብ ፡ ተውጠው ፡ አንገታቸውን ፡ ደፉ ።

ታራስ ፡ ኰዛኰቹ ፡ ማዘናቸውንና ፡ ለጐበዝ ፡ ተገቢ ፡ ያልሆነው ፡ ትካዜ ፤ አንገታቸውን ፡ እንደቀለሰው ፡ ተመለከተ ። ነገር ፡ ግን ፡ በፊት ፡ ከጓደኞቻቸው ፡ የመለየቱን ፡ ሃዘን ፡ ይላመዱትና ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ተደስቶ ፡ የበለጠ ፡ ብርታት ፡ እንዲያገኝ ፡ በኰዛክ ፡ የጦር ፡ ጩኸት ፡ አነቃቃቸዋለሁ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ጠባይ ፡ ለሰፊውና ፡ ለኃያሉ ፡ የስላቮ ፡ ተፈጥሮ ፡ ብቻ ፡ የታደለ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የስላቮ ፡ ተፈጥሮ ፡ ከሌሎች ፡ ሲነፃፀር ፡ በባህርና ፡ በጐጭ ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ ያህል ፡ የላቀ ፡ ነው ። ጊዜው ፡ ሞገዳማ ፡ ሲሆን ፡ እንደነጐድጓድ ፡ እያገሳ ፤ ደካማ ፡ ወንዞች ፡ የማይችሉትን ፡ ተራራ ፡ የሚያህል ፡ ማዕበል ፡ ያነሳል ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፋስ ፡ ሳያናውፀው ፡ ፀጥ ፡ ብሎ ፡ በረጋ ፡ ጊዜ ፡ ከማናቸውም ፡ ወንዝ ፡ ይበልጥ ፡ ጠርቶ ፡ ሲንጣለል ፡ ለዓይን ፡ የማይጠገብ ፡ ደስታ ፡ ነው ።

ታራስ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ የቆመውን ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ እንዲያራግፉ ፡ አሽከሮቹን ፡ አዘዘ ። ይህ ፡ ሠረገላ ፡ ከሌሎቹ ፡ የኰዛኰች ፡ ጓዝ ፡ ተሸካሚዎች ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ ትልቅና ፡ ጠንካራ ፡ ነበር ። ትልልቅ ፡ ተሽከርካሪዎቹም ፡ በእጥፍ ፡ ብረት ፡ የተጠረዙ ፡ ናቸው ። ሠረገላው ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ተጭኖ ፡ ጭነቱም ፡ ጠንካራ ፡ የበሬ ፡ ቆዳ ፡ ለብሶ ፡ ዘይት ፡ በጠጣ ፡ ገመድ ፡ ተቀርቅቦአል ። የተጫነው ፡ ጭነት ፡ በቡልባ ፡ እቃ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የኖረ ፡ በበርሚል ፡ ያለ ፡ መልካም ፡ የበሰለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ነበር ። ቡልባ ፡ ይህን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ያመጣው ፡ ድንገት ፡ ታላቅ ፡ አጋጣሚ ፡ ቢደርስ ፡ የኰዛኰቹን ፡ ወኔ ፡ ለመቀስቀስ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ እንዲቀርብ ፡ አስቦ ፡ ነው ። አሽከሮቹ ፡ የኰሎኔሉን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲሰሙ ፡ ፈጥነው ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ሔዱና ፡ በጐራዴያቸው ፡ ወፍራሙን ፡



ገመድ ፡ ቆራርጠው ፡ ጠንካራውን ፡ ቆዳም ፡ ቀዳድው ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ በርሚሎች ፡ አወረዱ ።

ከዚያ ፡ ቡልባ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ሁሉንም ፡ ጠጡ ፤ ያለውን ፡ ሁሉ ፡ ያገኛችሁትን ፡ መጠጫ ፡ ይዛችሁት ፤ ጭልፋ ፡ ወይም ፡ የፈረስ ፡ ማጠጫ ፤ ባልዲ ፡ ወይም ፡ ዋንጫ ፤ እኒህም ፡ እንኳን ፡ ባይኖራችሁ ፡ እፍኛችሁን ፡ አቅርቡ!»

ኰዛኰቹም ፡ አንዳቸውም ፡ ሳይቀሩ ፡ ያገኙትን ፡ መጠጫ ፡ ይዘው ፤ የሌላቸውም ፡ እፍኛቸውን ፡ አዘጋጅተው ፡ ቀረቡ ። የቡልባ ፡ አሽከሮችም ፡ በመካከላቸው ፡ ገብተው ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ ይቀዱ ፡ ጀመር ። ግን ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ እንዲጠጡ ፡ እሱ ፡ ምልክት ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ መጠጣት ፡ እንዳይጀምር ፡ ቡልባ ፡ አዘዘ ። እሱ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ አስቀድሞ ፡ አስቦአል ። መልካም ፡ የበሰለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ምንም ፡ ያህል ፡ ኃይለኛ ፡ ቢሆንና ፡ የሰውንም ፡ መንፈስ ፡ ለማነቃቃት ፡ ቢችል ፡ በሚጠጣበት ፡ ሰዓት ፡ በደንብ ፡ የተመረጡ ፡ ቃላት ፡ ከተጨመሩ ፡ የወይን ፡ ጠጁ ፡ ኃይልም ፡ ሆነ ፡ የሰዎቹ ፡ ወኒ ፡ አጠፊታ ፡ እንደሚሆን ፡ ታራስ ፡ በደንብ ፡ ያውቃል ።

ስለዚህ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፤

«ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፤ አሁን ፡ የጋበዝኳችሁ ፡ መሪአችሁ ፡ እንድሆን ፡ ስለመረጣችሁኝ ፡ አይደለም ። እርግጥ ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ለኔ ፡ ታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ። ሆኖም ፡ የአሁኑ ፡ ግብዣ ፡ ምክንያት ፡ እሱ ፡ አይደለም ። ከጓደኞቻችንም ፡ በመለየት ፡ የተነሳ ፡ አይምሰላችሁ ። ሁለቱም ፡ ነገሮች ፡ ቢሆኑ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ለግብዣው ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ በሆኑ ፡ ነበር ። ግን ፡ የአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ተስማሚ ፡ አይደለም ። ከፊታችን ፡ የተደቀነው ፡ ጦርነት ፡ ብዙ ፡ ድካምና ፡ ታላቅ ፡ የኰዛክ ፡ ጀግንነት ፡ የሚጠይቅ ፡ ነው! ስለዚህ ፡ ጓደኞቼ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድመን ፡ ለተቀደሰው ፡ የኦርቶዶክስ ፡

ሃይማኖት ፡ እንጠጣ! በመላው ፡ ዓለም ፡ ተስፋፍቶ ፡ በየትም ፡ ሥፍራ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንዲኖርና፡ ከሃዲዎች ፡ ሁሉ ፡ ክርስትናን ፡ እንዲቀበሉ ፡ በመመኘት ፡ እንጠጣ! ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ለሴቼ ፡ እንጠጣ! ከሃዲዎችን ፡ ለማስጨነቅ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ እንዲጸና ፡ በየዓመቱም ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ የላቀ ፡ ጀግኖች ፡ ተዋጊዎች ፡ ለማሰለፍ ፡ እንዲችል ፡ እንጠጣ! ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ለኛ ፡ ለራሳችን ፡ ጀግንነት ፡ እንጠጣ! የልጅ ፡ ልጆቻችንና ፡ የነሱም ፡ ልጆች ፡ ቀድሞ ፡ ወንድምነትን ፡ የማይክዱና ፡ የተቸገሩ ፡ ጓደኞቻቸውን ፡ የማያጋልጡ ፡ ጀግኖች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ እያሉ ፡ እንዲያስታውሱን ፡ ይሁን! በሉ ፡ ለሃይማኖታችን ፡ ወንድሞቼ ፡ መኳንንት ፤ ለሃይማኖታችን ፡ በሉ ፡ ለሃይማኖታችን!»

«ለሃይማኖታችን!» ብለው ፡ በመጮህ ፡ ወጣት ፡ ሽማግሌው ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ለሃይማኖታቸው ፡ ጠጡ ።

«ለሴቼ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ጽዋውን ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ አነሳ ።

«ለሴቼ!» ሲል ፡ የኮዛኮቹ ፡ ጩኸት ፡ አስተጋባ ።

ኮዛኮቹ ፡ ለሴቼ ፡ ሰላምታቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ ድምጻቸው ፡ መስኩን ፡ ሁሉ ፡ አቋርጦ ፡ ሩቅ ፡ ሥፍራ ፡ ድረስ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

«የመጨረሻ ፡ ጽዋችንን ፡ ወንድሞቼ ፡ ለእኛ ፡ ጀግንነትና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሁሉ ፡ ስንል ፡ እንጠጣ!» አለ ፡ ቡልባ ።

ኮዛኮቹ ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ለጀግንነታቸውና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የመጨረሻ ፡ ጽዋቸው ፡ አንስተው ፡ ጠጡ ።

ጽዋቸው ፡ ባዶ ፡ ሆኖአል ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ አሁንም ፡ እጃቸውን ፡ እንዳነሱ ፡ ቆሙ ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከመጠጡ ፡ የተነሳ ፡ በዓይኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ ቢታይም ፡ ውስጡን ፡ ጥልቅ ፡ ሃሳብ ፡ ገብቶአቸው ፡ ነበር ። አሁን ፡ በሃ



ሳባቸው ፡ የሚያሰላስሉት ፡ በውጊያው ፡ ስለሚደርሳቸው ፡ ትርፍ ፡ ወይም ፡ ጉዳት ፡ አይደለም ። እድል ፡ አግኝተው ፡ ወርቅ ፤ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ መሣሪያዎች ፤ በጥልፍ ፡ ያጌጡ ፡ ልብሶችና ፡ የሴርካሲያን ፡ ፈረሶች ፡ ለመማረክ ፡ ስለሚችሉት ፡ ሰዎችም ፡ አይደለም ። በረጅም ፡ ተራራ ፡ ቋጥኝ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሰፊውን ፡ ባህር ፡ ነጥብ ፡ ከመሳሰሉ ፡ ጀልባዎቹና ፡ መርከቦቹ ፡ ጋር ፡ ዳር ፡ ዳሩም ፡ አሻንጉሊት ፡ መስለው ፡ የሚታዩትን ፡ ከተማዎችና ፡ ሳር ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ጫካዎችን ፡ እንደሚመለከት ፡ ንስር ፡ አሞራ ፡ እነሱም ፡ ሜዳውን ፡ አገር ፡ እየተመለከቱ ፡ በሃሳባቸው ፡ የሚያሰላስሉትም ፡ የወደፊት ፡ እድላቸውን ፡ ነበር ። ሜዳው ፡ ሁሉ ፡ ደማቸውን ፡ ጠጥቶ ፡ አጥንታቸውን ፡ ለብሶ ፡ የሠረገላ ፤ የጦርና ፡ የጐራዴ ፡ ስብርባሪም ፡ በየሥፍራው ፡ ተበታትኖ ፡ የሚታይበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ። ጭንቅላታቸው ፡ ደም ፡ ከተጋገረበት ፡ ጉንጉን ፡ ጐፈሬአቸው ፡ ጋር ፡ በየሜዳው ፡ ይዘራል ። አሞሮችም ፡ እየወረዱ ፡ ዓይኖቻቸውን ፡ ጭረው ፡ ፈልፍለው ፡ ያወጧቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ አጥንት ፡ የተዘራበት ፡ የዚያ ፡ የሞት ፡ ሰፈር ፡ ዝና ፡ ታላቅ ፡ ይሆናል! ከጀብዶአቸው ፡ አንዱም ፡ ቢሆን ፡ አይረሳም ። የኮዛክ ፡ ጀግንነት ፡ ከጠመንጃ ፡ አፈሙዝ ፡ በኖ ፡ እንደሚጠፋ ፡ ባሩድ ፡ የሚጠፋ ፡ አይደለም ። ሽበቶው ፡ ጢሙ ፡ ደረቱ ፡ ላይ ፡ የወደቀ ፡ የራሱ ፡ ሽበት ፡ ሻሽ ፡ የመሰለ ፡ ሽማግሌ ፡ ባንዱራ ፡ መቺ ፡ ዝናቸውን ፡ የሚያነሳበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ። ጀግንነታቸውም ፡ በዓለም ፡ ይነዛል ። ከነሱ ፡ ኋላ ፡ የሚወለዱት ፡ ሁሉ ፡ ስለነሱ ፡ ያወራሉ ።

## ምዕራፍ ፡ ዘጠኝ ።

ከዛፖሮዢያኖቹ ፡ መካከል ፡ ገሚሱ ፡ ጦር ፡ ታታሮቹን ፡ ለመከተል ፡ መሄዱን ፡ በከተማው ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ ያወቀ ፡ አልነበረም ። በከተማው ፡ አዳራሽ ፡ ህንፃ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ የቆ

ሙት ፥ ዘበኞች ፤ ግማሾቹ ፡ ሠረገላዎች ፤ ወደ ፡ ጫካው ፡ መነ
ዳታቸውን ፡ ተመልክተዋል ። ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ የደፈጣ ፡ ውጊያ ፡
አቅደው ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ አሰቡ ። የፈረንሳዊው ፡ መሐ
ንዲስ ፡ ግምትም ፡ ይኸው ፡ ነበር ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ኮሺ
ቮይው ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ በከንቱ ፡ አልቀረም ፤ ከተማው ፡
እንደገና ፡ በምግብ ፡ ችግር ፡ ተጨንቋል ። በቀድሞ ፡ ዘመናት ፡
እንደተለመደው ፡ ሁሉ ፤ ወታደሮቹ ፡ ስንቃቸውን ፡ በሚገባ ፡
አልመጠኑትም ። ከምሽቱ ፡ ወጥተው ፡ አደጋ ፡ በመጣል ፡
ያገኙትን ፡ ምግብ ፡ ለመዝረፍ ፡ ሞክረው ፡ ነበር ። ግን ፡
እነዚህ ፡ ምሽግ ፡ ለቅቀው ፡ የወጡ ፡ ደፋሮች ፤ ግማሾቹ ፡ ወዲ
ያው ፡ በኮዛኮቹ ፡ ተጨፍጭፈው ፡ ሲያልቁ ፡ የተረፉትም ፡ ባዶ ፡
እጃቸውን ፡ ተመለሱ ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ አጋጣሚ ፡ ለአ
ይሁዶች ፡ ተመቻቸውና ፡ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ዘርዝረው ፡
ተናገሩ ። ዛፖሮዢያኖቹ ፡ ወዴት ፡ እንደሄዱና ፡ ለምንስ ፡
እንደሄዱ ፤ መሪዎቻቸው ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፤ የመንደሮ
ቹና ፡ የሰዎቹ ፡ ቁጥር ፤ የቀሩትስ ፡ እነማን ፡ እንደሆኑ ፤ ሃሳ
ባቸው ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፤ በጠቅላላው ፡ በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ው
ስጥ ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ በከተማው ፡ ታወቀ ። ኮሎኔሎቹ ፡ በዚ
ህ ፡ ወሬ ፡ ተበረታቱና ፡ ለውጊያ ፡ ተዘጋጁ ። ታራስም ፡ የከ
ተማውን ፡ መራወጥ ፡ በማዳመጥ ፡ ነቃና ፡ በፍጥነት ፡ እር
ምጃ ፡ ወሰደ ። ወዲያው ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጠና ፡ የየመንደሩ ፡ ጦር ፡
በሶስት ፡ ቦታ ፡ ሠረገላዎቹን ፡ በዙሪያው ፡ መክቶ ፡ እንዲ
መሽግ ፡ አደረገ ። የሁለት ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ለደፈጣ ፡ ውጊ
ያ ፡ ተመደበና ፡ እንዲሁም ፡ ለጠላት ፡ ፈረሰኞች ፡ መሰና
ክል ፡ እንዲሆን ፡ ሹል ፡ እንጨቶች ፤ የጠበንጃና ፡ የጦር ፡ ሰባ
ሪዎች ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ ተቸከሉ ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ እንደ
ፍላጐቱ ፡ ከተዘጋጀ ፡ በኋላ ፡ ታራስ ፡ ለኮዛኮቹ ፡ ንግግር ፡ አደ
ረገ ። የንግግሩ ፡ ዓላማ ፡ የኮዛኮቹን ፡ ወኔ ፡ ለመቀስቀስ ፡ ወ
ይም ፡ ለማበረታታት ፡ የታቀደ ፡ አልነበረም ። ወኔያቸው ፡
አስቀድሞም ፡ እንደተቀሰቀሰ ፡ ታራስ ፡ አልዘነጋም ። ነገር ፡



ግን ፡ በልቡ ፡ ያለውን ፡ ለማውጣትና ፡ እንዲቀልለው ፡ ሲል ፡
እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«መኳንንት ፡ ሆይ ፤ ስለጓደኝነታችንና ፡ ስለወንድማማ
ችነታችን ፡ ልገልጽላችሁ ፡ እፈልጋለሁ ። ሃገራችን ፡ በሌሎ
ች ፡ መንግሥታት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግምት ፡
እንደነበራት ፡ ከአባቶቻችሁና ፡ ከአያቶቻችሁ ፡ ሰምታች
ሁታል ። ሃገራችን ፡ በግሪኮች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀች ፡ ነበረች ፤
ኮንስታንቲኖፕልንም ፡ ታስገብር ፡ ነበር ። ከተሞቻችን ፡
ሃብታም ፡ ነበሩ ። የራሳችን ፡ ቤተ ፡ መቅደሶችና ፡ እንዲሁ
ም ፡ ካቶሊካውያን ፡ ከሃዲዎች ፡ ሳይሆኑ ፡ እውነተኛ ፡ የሩ
ሲያዊ ፡ ደም ፡ ያላቸው ፡ የራሳችን ፡ ልዑላኖች ፡ ነበሩን ።
ይህንን ፡ ሁሉ ፡ ተገፈፍን ። ሁሉም ፡ ጠፋ ። እንደሙት ፡ ል
ጆች ፡ እኛው ፡ ብቻ ፡ ቀረን ። ሃገራችንም ፡ ኃያል ፡ ባሏ ፡
እንደሞተባት ፡ ሴት ፡ ብቻዋን ፡ ቀረች ። እንዲህ ፡ ባለውም ፡
ጊዜ ፡ ጓደኞቼ ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ በወንድማማችነት ፡ ተሳስረን ፡
ለመቆም ፡ በቃን ። ከጓደኝነት ፡ የሚበልጥ ፡ የተቀደሰ ፡ ዝም
ድና ፡ አይገኝም ። ጓደኝነታችንም ፡ የተመሰረተው ፡ በዚህ ፡
ላይ ፡ ነው ። አባት ፡ ልጁን ፡ ይወዳል ፤ እናት ፡ ልጇዋን ፡
ትወዳለች ። ልጅም ፡ እናትና ፡ አባቱን ፡ ይወዳል ። ግን ፡ ይህ ፡
ሌላ ፡ ነገር ፡ ነው ። እንስሳትም ፡ እንኳን ፡ ልጆቻቸውን ፡
ይወዳሉ ። የደም ፡ ሳይሆን ፡ የመንፈስን ፡ ፍቅርና ፡ ዝምድ
ና ፡ የሚያውቀው ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። ወንድማማችነ
ት ፡ በሌሎች ፡ ሃገሮችም ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፡ በእኛ ፡ በሩሲ
ያውያን ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ያህል ፡ በየትም ፡ አይገ
ኝም ። ብዙዎቻችሁ ፡ በባዕድ ፡ ሃገሮች ፡ ብዙ ፡ አመታት ፡
አሳልፋችኋል ። በዚያም ፡ እንደናንተው ፡ ያሉ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ፍጡር ፡ ሰዎችን ፡ አግኝታችሁ ፡ እንደዘመድ ፡ ተወ
ያይታችኋል ። ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በንግግራቸው ፡
ጠቢብ ፡ ይሁኑ ፡ እንጂ ፡ የልብን ፡ ገልጾ ፡ በመወያየት ፡ ረገድ ፡
ከእናንተ ፡ የተለዩ ፡ ናቸው ። በተፈጥሮ ፡ ሰው ፡ መሆናቸው ፡

ቢታወቅም ፤ እንደናንተ ፡ ፍጹም ፡ የሰውነት ፡ ጠባይ ፡ የላቸውም! የለም ፤ ወንድሞቼ ፤ እንደ ፡ ሩሲያውያን ፡ ከልብ ፡ የሚያፈቅር ፤ በአዕምሮ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ በሙሉ ፡ አካሉ ፤ አምላክ ፡ በሰጠው ፡ ተፈጥሮ ፡ ሁሉ ፡ የሚያፈቅር ፡…» እዚሀ ፡ ላይ ፡ ታራስ ፡ ሽበቶ ፡ ራሱን ፡ ነቅነቀና ፡ እንደገና ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለ ። «እንዲያ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ የሚያውቅ ፡ ማንም ፡ የለም!በሃገራችን ፡ አንዳንድ ፡ የክፋት ፡ መንፈሶች ፡ እንደተመሠረቱ ፡ አውቃለሁ ። ለስንዴና ፡ ለድርቆሽ ፡ ክምራቸው ፤ ለፈረስ ፡ መንጋቸውና ፡ እንዲሁም ፡ በበርሚል ፡ ለታሸገው ፡ ጠጃቸው ፡ ብቻ ፡ የሚያስቡ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። የሚያስጠላ ፡ የባዕድ ፡ ልብስ ፡ አጥልቀው ፡ የእናት ፡ የአባታቸውን ፡ ቋንቋም ፡ ንቀው ፡ ትተውት ፡ የሃገር ፡ ልጅ ፡ ከሃገር ፡ ልጅ ፡ ጋር ፡ መነጋገሩ ፡ ቀርቷል ። ከዚህም ፡ አልፎ ፡ የሃገር ፡ ልጅ ፡ የሃገሩን ፡ ልጅ ፡ በገበያ ፡ እንደሚሸጥ ፡ ከብት ፡ ይሸጠው ፡ ጀመር ። አንድ ፡ የባዕድ ፡ ንጉሥ ፡ ወይም ፡ በቢጫ ፡ ጫማው ፡ በእርግጫ ፡ የሚመታቸው ፡ የፖላንድ ፡ ሹም ፡ ለእነሱ ፡ ከወንድማማችነት ፡ በልጦባቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ወራዶች ፡ መካከል ፡ የመጨረሻው ፡ ወራዳም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፤ ምንም ፡ እንኳን ፡ በውርደት ፡ ቢሽቆጠቆጥና ፡ መሬት ፡ ቢልስ ፡ ትንሽ ፡ የሩሲያዊ ፡ ስሜት ፡ ቅንጣት ፡ አያጣም ። ይህም ፡ ስሜቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ይገነፍልና ፡ ፀጉሩን ፡ እየነጨ ፡ ህይወቱን ፡ በመርገም ፡ ከሃፍረቱ ፡ ለመንፃት ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ የሚሠቃይበት ፡ ቀን ፡ ይመጣል ። በሩሲያዊ ፡ ምድራችን ፡ ላይ ፡ ጓደኝነት ፡ ማለት ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ሁሉም ፡ ይገንዘቡት! በሞት ፡ ረገድ ፡ የሆነ ፡ እንደሆንም ፤ እኛ ፡ አሁን ፡ የተሰለፍንለትን ፡ አሟሟት ፡ ከእነሱ ፡ አንዳቸውም ፡ አያገኙትም! አንዳቸውም! ከአይጥ ፡ ልብ ፡ የማይሻለው ፡ ልባቸው ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ አሟሟት ፡ አይፈቅድላቸውም!»

እነሆ ፡ የኮዛኮች ፡ መሪ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ። ንግግሩን ፡ ከጨረሰም ፡ በኋላ ፡ በኮዛክ ፡ ጀብዱ ፡ የሸበተውን ፡ ራሱን ፡



በትካዜ ፡ ያነቃንቅ ፡ ነበር ። እዚያ ፡ የቆሙት ፡ ሁሉ ፡ በአነጋገሩ ፡ ልባቸው ፡ ተነካ ። ጠና ፡ ጠና ፡ ያሉት ፡ መኳንንት ፡ አንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ በእርጋታ ፡ ቆመው ፡ ዓይናቸው፡ እንባ ፡ እያቀረረ ፡ በእጅጌያቸው ፡ ይጠርጉ ፡ ጀመር ። ታራስ ፡ የተናገራቸው ፡ ቃላት ፡ በጉብዝና ፡ ልፋትና ፡ ችግር ፡ በኖሩት ፡ የበሰሉ ፡ ሰዎችም ፡ ሆነ ፡ የኑሮን ፡ ችግር ፡ ገና ፡ ሳይቀምሱ ፡ ጉብዝናን ፡ የአባት ፡ ቅርስ ፡ አድርገው ፡ በድፍረት ፡ በሚመኙት፡ ጐልማሶች ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ያን ፡ አስደሳች ፡ የጀግና ፡ ወኔ ፡ ቀሰቀሱት ።

ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ የጠላት ፡ ሰልፍ ፡ ከከተማው ፡ መውጣት ፡ ጀምሯል ። ነጋሪት ፡ እየተጐሰመ ፤ መለከት ፡ እየተነፋ ፡ የጠላት ፡ መኳንንት ፡ ስፍር ፡ ቁጥር ፡ በሌላቸው ፡ ገባሮቻቸው ፡ ታጅበው ፡ እየጋለቡ ፡ ወጡ ። ወዲያው ፡ ወፍራሙ ፡ ኮሎኔል ፡ ትዕዛዝ ፡ ሰጠና ፡ ሁሉም ፡ በአንድነት ፡ ሰይፋቸውን ፡ እያወናጨፉ ፡ ጠበንጃቸውን ፡ ደግነው ፡ ወደ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ገሰገሱ ።

ኮዛኮቹም ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ለጠበንጃ ፡ ተኩስ ፡ ሲቀርቡላቸው ፡ ያለማቋረጥ ፡ እያከታተሉ ፡ እሩምታ ፡ ይተኩሱ ፡ ጀመር ። ተኩሱም ፡ መስከና ፡ ኮረብታዎችን ፡ አልፎ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ እንደነጐድጓድ ፡ አስተጋባ ። አካባቢው ፡ ሁሉ ፡ በጢስ ፡ ታፈነ ። ኮዛኮቹ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳያቋርጡ ፡ ተኩሳቸውን ፡ ቀጠሉ ። ከኋላ ፡ ያሉት ፡ እፊት ፡ ላሉት ፡ እያቀባበሉላቸው ፡ አከታትለው ፡ ሲተኩሱ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ዘዴውን ፡ ስላላወቁ ፡ ሳያቀባብሉ ፡ እንዴት ፡ አከታትለው ፡ ይተኩሳሉ ፡ በማለት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። ሁለቱንም ፡ ወገን ፡ የባሩድ ፡ ጢስ ፡ አፍኗቸው ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ አይታይም ። አንድ ፡ በአንድ፡ ከመካከላቸው ፡ እየተነጠሉ ፡ የሚወድቁትንም ፡ ወታደሮች ፡ ለማየት ፡ አልቻሉም ። ነገር ፡ ግን ፡ ፖሊሾቹ ፡ የሚወርድባቸው ፡ ተኩስ ፡ ማየሉንና ፡ የሁናቴውንም ፡ መክፋት ፡ ተገንዝበው ፡ ከጢሱ ፡ አፈና ፡ ለመውጣት ፡ አፈግፍ

ገው ፡ መለስ ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ እንደወደ ቀባቸው ፡ አዩ ። ከኮዛኮቹ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ የሞቱት ፡ ቁጥር ፡ በመቶ ፡ ከሁለት ፡ ወይም ፡ ከሶስት ፡ አይበልጥም ፡ ነበር ። ኮዛኮቹ ፡ አሁንም ፡ ተኩሳቸውን ፡ አላቋረጡም ። ለእርዳታ ፡ የመጣው ፡ ፈረንሳዊው ፡ መሐንዲስ ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ አይቶት ፡ በማያውቀው ፡ በኮዛኮቹ ፡ ታክቲክ ፡ እጅግ ፡ ተደ ንቆ ፤ «እነዚህ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ በዕውነት ፡ ጐበዞች ፡ ናቸው! በሌሎች ፡ አገሮችም ፡ የጦር ፡ ስልት ፡ እንዲህ ፡ መሆን ፡ ይገ ባዋል!» አለና ፡ ወዲያው ፡ የኮዛኮቹ ፡ ምሽግ ፡ በመድፍ ፡ እን ዲደበደብ ፡ አሳሰበ ። የመድፎቹም ፡ ሰፋፊ ፡ የብረት ፡ ጉሮሮ ፡ ምድሩ ፡ እስኪናወጽ ፡ ድረስ ፡ አገሳ ። ጢሱም ፡ የቀድሞውን ፡ አጠፊታ ፡ መስኩን ፡ ሁሉ ፡ አለበሰው ። የባሩዱ ፡ ሽታ ፡ በሩ ቅም ፡ በቅርብ ፡ ላሉ ፡ ከተሞች ፡ ተሰማቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የመድፎቹ ፡ ድግን ፡ ራስ ፡ ሄዶ ፡ ኖሮ ፡ አረሮቹ ፡ በሚያስፈራ ፡ ድምጽ ፡ በኮዛኮቹ ፡ ጭንቅላት ፡ ላይ ፡ አልፈው ፡ ባዶውን ፡ ሜዳ ፡ ፈነቃቀሉት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ፈረንሳዊው ፡ መሐን ዲስ ፡ ከንዴቱ ፡ የተነሳ ፡ ኮዛኮቹ ፡ በዙሪያው ፡ የሚያዘንቡ ትን ፡ የጥይት ፡ በረዶ ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥር ፡ መድፎቹን ፡ ራሱ ፡ አስተካክሎ ፡ ለማነጣጠር ፡ ሄደ ።

ታራስ ፡ ከሩቅ ፡ ሆኖ ፡ ሲመለከት ፡ የኔዛማይና ፡ የስቴ ብሊኪቭ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አደጋ ፡ ሊደ ርስባቸው ፡ መሆኑን ፡ ተገነዘበና ፡ «ከሠረገላው ፡ ቶሎ ፡ ገለል ፡ በሉና ፡ ፈረሶቻችሁ ፡ ላይ ፡ ውጡ!» በማለት ፡ እንደነጐድ ጓድ ፡ በሚያስተጋባ ፡ ድምጽ ፡ ጮኸ ። ነገር ፡ ግን ፡ ወዲያ ው ፡ ኦስታፕ ፡ ጋልቦ ፡ ከጠላቶቹ ፡ ማሃል ፡ ገብቶ ፡ የመድ ፉን ፡ ተኩስ ፡ ባያሰናክል ፡ ኖሮ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ታራስ ፡ የተናገረ ውን ፡ ለመፈጸም ፡ ጊዜም ፡ ባላገኙ ፡ ነበር ። ኦስታፕ ፡ ከጠ ላቶቹ ፡ መሃል ፡ ገብቶ ፡ ከስድስት ፡ መድፈኞች ፡ እጅ ፡ የባሩ ድ ፡ ማቀጣጠያውን ፡ ችቦ ፡ አስጥሎ ፡ ሌሎቹ ፡ አራት ፡ መድ ፈኞች ፡ ካሉበት ፡ ሥፍራ ፡ ከመድረሱ ፡ በፊት ፡ ፖሊሾቹ ፡



ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሱት ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ ፈረንሳዊው ፡ መሐ ንዲስ ፡ ከሁሉ ፡ ትልቅ ፡ የሆነውን ፡ ከባድ ፡ መድፍ ፡ ራሱ ፡ ለመተኮስ ፡ የባሩድ ፡ ማቀጣጠያ ፡ ችቦ ፡ ይዟል ። እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ መድፍ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ከዚያ ፡ ቀደም ፡ አይተው ፡ አያውቁም ። የሚያስፈራራው ፡ ትልቅ ፡ አፉ ፡ ተከፍቶ ፡ በው ስጡም ፡ በሺ ፡ የሚቆጠር ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ ያንዣብባል ። ይህ ፡ ትልቅ ፡ መድፍ ፡ እንደነጐድጓድ ፡ ሲያጐራ ፡ ሌሎቹ ፡ ሶስ ቱም ፡ ተከተሉትና ፡ በድምጻቸው ፡ ምድሩ ፡ ተናወጸ ። ድም ጽም ፡ ብዙ ፡ አደጋ ፡ አደረሰ ። እንግዲህ ፡ ብዙ ፡ ባልቴት ፡ እናቶች ፡ ደረታቸውን ፡ እየደቁ ፡ ለኮዛክ ፡ ልጆቻቸው ፡ ያለ ቅሳሉ ። በግሉኾቭ ፤ በኔሚሮቭ ፤ በቼርኒጐቭና ፡ በሌሎች ም ፡ ከተሞች ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ ባል ፡ የለሽ ፡ ይሆናሉ ። እነዚ ህ ፡ አሳዛኝ ፡ ሴቶች ፡ በየቀኑ ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ እየሄዱ ፡ ተወ ዳጅ ፡ ባሎቻቸውን ፡ በመፈለግ ፡ አላፊ አግዳሚውን ፡ ሁሉ ፡ ይመለከታሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ በከተማው ፡ ብዙ ፡ ሠራዊት ፡ ቢያልፍ ፡ ተወዳጅ ፡ ባሎቻቸውን ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ አያገኟቸውም ።

የኔዛማይ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ ግማሽ ፡ ጨርሶ ፡ እንዳል ነበር ፡ ሆኗል ። በከባድ ፡ በረዶ ፡ እንደሚረግፍ ፡ ሰብል ፤ እነሱም ፡ ረገፉ ።

ኮዛኮቹ ፡ እጅግ ፡ ተናደዱ! በንዴትም ፡ ሁሉም ፡ በአን ድነት ፡ ወደፊት ፡ ገሰገሱ ። አዛገፉ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ የመንደሩ ፡ ጦር ፡ ግማሽ ፡ በመጥፋቱ ፡ በንዴት ፡ ተቃጠለ! ወዲያው ፡ የተረፉትን ፡ ኮዛኮቹን ፡ አስከትሎ ፡ የጠላትን ፡ ሰልፍ ፡ እየ ሰነጣጠቀ ፡ ከማሀል ፡ ገባ ። ከንዴቱ ፡ የተነሳ ፡ መጀመሪ ያ ፡ ያጋጠመውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ ጐመን ፡ ቆራርጦ ፡ ጣለው ። ከዚያም ፡ ብዙ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ከኮርቻ ቸው ፡ እየፈነገለ ፤ ብዙዎቹንም ፡ ከነፈረሳቸው ፡ በጦር ፡ እየ ወጋ ፡ ገሰገሰ ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ደርሶ ፡ ከመድፈኞቹ ፡ አንዱ ን ፡ እንደያዘ ፤ ወዲያው ፡ የኡማን ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ መሪና ፡

ስቴፓን ፡ ጉዝካ ፡ ትልቁን ፡ መድፍ ፡ ለመማረክ ፡ መቃረባቸውን ፡ ተመለከተና ፡ ኮዛኮቹን ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ የጦር ፡ ግንባር ፡ አመራ ። የኔዛማይ ፡ ኮዛኮች ፡ በሄዱበት ፡ ሥፍራ ፡ ሁሉ ፡ የፖሊሾቹን ፡ ሬሣ ፡ እየረፈረፉት ፡ ያልፉ ፡ ጀመር ። የእነሱም ፡ ሰልፍ ፡ እየሳሳ ፡ ሄደ ። በሠረገላዎቹ ፡ አጠገብ ፡ ቮቭቱዜንኮ ፡ ጠንክሮ ፡ ይዋጋል ። ከግንባር ፡ ቼሬቪቼንኮ ፡ ራቅ ፡ ብሎም ፣ ዴግቲያሬንኮ ፣ ከእሱም ፡ ኋላ ፡ የመንደር ፡ ጦር ፡ መሪው ፡ ቬርቲኽቪስት ፡ ይዋጋሉ ። ዴግቲያሬንኮ ፡ ሁለት ፡ መኳንንት ፡ በጦር ፡ ወግቶ ፡ ገድሎ ፡ ከሶስተኛው ፡ ጋር ፡ ገጥሟል ። ይህም ፡ ሶስተኛው ፡ መኰንን ፡ የከበረ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ቀልጣፋ ፡ ሰው ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ ሃምሳ ፡ የሚሆኑ ፡ አሽከሮች ፡ አጅበውታል ። ወዲያው ፡ ዴግቲያሬንኮን ፡ አጣድፎ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ጣለውና ፡ ጐራዴውን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እያወዛወዘ ፣ «እናንት ፡ የኮዛክ ፡ ውሾች ፣ አንዳችሁም ፡ ከእኔ ፡ ለመቋቋም ፡ አትደፍሩም!» አለና ፡ ጮኸ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፣ «ይኸው ፡ እኔ ፡ አለሁ!» አለና ፡ ሞሲይ ፡ ሺሎ ፡ ፈንጠር ፡ ብሎ ፡ ወጣ ። ሺሎ ፡ ከአንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ ፡ በባህር ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ የሆነና ፡ ብዙ ፡ ዓይነት ፡ ችግር ፡ የቀመሰ ፡ ኮዛክ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ በትሬቢዞንድ ፡ አቅራቢያ ፡ ከነተከታዮቹ ፡ ቱርኮች ፡ ማርከውት ፡ ሁሉንም ፡ ባሪያ ፡ አድርገው ፡ ብዙ ፡ ሳምንት ፡ ምግብና ፡ ውሃ ፡ ከልክለው ፡ ሲያሰቃዩዋቸው ፡ ምርኮኞቹም ፡ የኦርቶዶክስ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ከመሻር ፡ ስቃይ ፡ መቀበሉ ፡ ይሻላል ፡ በማለት ፡ ሁሉንም ፡ ቻሉ ። መሪያቸው ፡ ሞሲይ ፡ ሺሎ ፡ ግን ፡ ስቃዩን ፡ አልቻለውም ። የተቀደሰውን ፡ ሃይማኖቱን ፡ አፍርሶ ፡ ያን ፡ የተረገመ ፡ የእስላም ፡ ጥምጥም ፡ በኃጢአተኛው ፡ ራሱ ፡ ላይ ፡ ጠመጠመና ፡ በፓሻው ፡ ተወድዶ ፡ ዕምነት ፡ ከተጣለበት ፡ በኋላ ፡ የእሥር ፤ ቤቱ ፡ ቁልፍ ፡ ያዥና ፡ የባሮቹ ፡ አለቃ ፡ ሆነ ። እስረኞቹ ፡ ባሮችም ፡ ከመካከላቸው ፡ አንዱ ፡



ሃይማኖቱን ፡ ክዶ ፡ ወደ ፡ ጨካኝ ፡ ገዥዎቻቸው ፡ ሲያዘነብል ፡ ክፉቱ ፡ ከማናቸውም ፡ አረመኔ ፡ የባሰ ፡ መሆኑን ፡ ስለሚያውቁ ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ። በዕውነትም ፡ ሞሲይ ፡ ሺሎ ፡ እጅግ ፡ ከፋባቸው ። በአዲስ ፡ ሰንሰለት ፡ ከግንድ ፡ ጋር ፡ አስሮ ፡ እስከ ፡ አጥንት ፡ ድረስ ፡ በሚገሸልጥ ፡ አለንጋ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ ይገርፋቸው ፡ ጀመር ። ቱርኮቹም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አሽከር ፡ በማግኘታቸው ፡ ከመደሰታቸው ፡ የተነሳ ፡ ደንባቸውን ፡ ዘነጉና ፡ ፈንጠዝያ ፡ በማድረግ ፡ መጠጥ ፡ ጠጥተው ፡ ሰከሩ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሺሎ ፡ ስልሳ ፡ አራቱንም ፡ የእስረኞቹን ፡ የሰንሰለት ፡ ቁልፍ ፡ ወስዶና ፡ ሰንሰለታቸውን ፡ እየፈታ ፡ ጐራዴ ፡ ይዘው ፡ ቱርኮቹን ፡ እንዲቆራርጡ ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የሰንሰለታቸውን ፡ ቁልፍ ፡ ሰጣቸው ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኮዛኮቹ ፡ የዘረፉት ፡ ሃብት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበር ። በጀግንነት ፡ ወደ ፡ እናት ፡ ሃገራቸው ፡ ከተመለሱም ፡ በኋላ ፡ ዘፋኞች ፡ የሞሲይ ፡ ሺሎን ፡ ጀግንነት ፡ እያነሱ ፡ ለብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሲያሞግሱት ፡ ኖረዋል ። እንደ ፡ ችሎታው ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ኮሼቮይ ፡ ሆኖ ፡ በተመረጠ ፡ ነበር ። ነገር ፡ ግን ፡ ጠባዩ ፡ ግራ ፡ የገባ ፡ ነው ። አንድ ፡ ጊዜ ፡ አስደናቂ ፡ መልካም ፡ ተግባር ፡ ይፈጽምና ፡ ወዲያው ፡ ደግሞ ፡ ሲወሰልት ፡ ይታያል ። ያለውን ፡ ሃብት ፡ ሁሉ ፡ በመጠጥና ፡ በፈንጠዝያ ፡ ጨርሶ ፡ ከየሰው ፡ ከመበደሩም ፡ በላይ ፡ እንደ ፡ ተራ ፡ ሌባ ፡ የመስረቅ ፡ አመል ፡ አደረበት ። አንድ ፡ ቀን ፡ በሌሊት ፡ ሙሉ ፡ የኮዛክ ፡ መሣሪያ ፡ ከሌላ ፡ መንደር ፡ ወስዶ ፡ ለመጠጥ ፡ ነጋዴው ፡ ሸጠና ፡ በዚህም ፡ ወራዳ ፡ ሥራው ፡ የተነሳ ፣ በገበያ ፡ መሃል ፡ ከግንድ ፡ ጋር ፡ ታሥሮ ፡ አላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀጠቅጠው ፡ አጠገቡ ፡ ዱላ ፡ ተቀመጠ ። ነገር ፡ ግን ፡ የአለፈውን ፡ የጀግንነት ፡ ሞያውን ፡ በማስታወስ ፡ አንድም ፡ ዛፖሮዥያን ፡ ያን ፡ ዱላ ፡ አላነሳበትም ። ሞሲይ ፡ ሺሎ ፡ የተባለው ፡ ኮዛክ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነበር ።

«እናንት ፡ ልክስክስ ፡ ውሾች ፣ እናንተን ፡ ለማሸነፍ ፡

የሚችሉ ፡ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ አሉን!» ብሎ ፡ ጮኸና ፡ ሺሎ ፡ ወደ ፡ ጠላቱ ፡ ገሰገሰ ።

ከዚያ ፡ ሁለቱ ፡ ብቻ ፡ ለብቻ ፡ ገጠሙና ፡ የብረት ፡ ልብሳቸው ፡ እስቲሰረጐድ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍ ፡ ይቀጣቀጡ ፡ ጀመር ። የፖላንዱ ፡ ጦረኛ ፡ የሺሎን ፡ የብረት ፡ ልብስ ፡ ሰንጥቆ ፡ ስጋውን ፡ አገኘውና ፡ የኮዛኩ ፡ ልብሶ ፡ በደም ፡ ተነከረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሺሎ ፡ ቁስሉን ፡ ከምንም ፡ ሳይቆጥረው ፡ ቀጭንና ፡ ጠምዛዛ ፡ ክንዱን ፡ ከፍ ፡ አድርጐ ፡ በመሰንዘር ፡ ጠላቱን ፡ ኃይለኛ ፡ በትር ፡ መታው ። ፖሊሹም ፡ የራስ ፡ ጥሩሩ ፡ ተሰባብሮ ፡ ተበታተነና ፡ ዝልፍልፍ ፡ ብሎ ፡ ወደቀ ። ሺሎም ፡ የወደቀውን ፡ ጠላቱን ፡ በሰይፍ ፡ ይቆራርጠው ፡ ጀመር ። ነገር ፡ ግን ፡ የወደቀውን ፡ ጠላቱን ፡ በንዴት ፡ ከመጨፍጨፍ ፡ ይልቅ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ በተሻለው ፡ ነበር ። ኮዛኩ ፡ ዞሮ ፡ ለመመልከት ፡ ከመቻሉ ፡ በፊት ፡ ከወደቀው ፡ ጠላቱ ፡ አሽከሮች ፡ አንዱ ፡ ደረሰና ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ ጩቤ ፡ ሰካበት ። ሺሎም ፡ ዘወር ፡ ቢል ፡ የወጋው ፡ ጠላቱ ፡ በባሩዱ ፡ ጢስ ፡ ማሃል ፡ ተሰውሮ ፡ ከዓይኑ ፡ ጠፋ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የተወጋውን ፡ አንገቱን ፡ በእጁ ፡ ያዘና ፡ ተንገዳግዶ ፡ ወደቀ ። ወዲያው ፡ ለጓደኞቹ ፤ «ደህና ፡ ሁኑ ፡ መኳንንት ፡ ወንድሞቼ ፤ ጓደኞቼ! የተቀደሰችው ፡ የሩሲያ ፡ ምድር ፡ ለዘለዓለም ፡ ተከብራ ፡ ትኑር!» አለና ፡ ዓይኖቹን ፡ ከደነ ። የኮዛክ ፡ ነፍሱም ፡ ከስጋው ፡ ተለይታ ፡ በረረች ።

በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ ዛዶሮዥኒይ ፡ ከነሰዎቹ ፡ በጦሩ ፡ ማሃል ፡ ይገሰግሳል ፤ ቬርቲኽቪስት ፡ የፖሊሾቹን ፡ ሰልፍ ፡ እየበታተነ ፡ ሲያልፍ ፤ ባላባንም ፡ ከዋናው ፡ ውጊያ ፡ ማሃል ፡ ዘልሎ ፡ ገባ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ! በባሩድ ፡ ቀንዳችሁ ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለን? የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመምን? ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አልሆኑምን?» አለና ፡ የጦር ፡ መሪዎቹን ፡ ጠየቀ ።



እነሱም ፤ «በባሩድ ፡ ቀንዳችን ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለ ፡ ባትኮ! የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመም! ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አይሆኑም!» አሉ ።

ወዲያው ፡ ኮዛኮቹ ፡ እንደገና ፡ በአጥቂነት ፡ ገሰገሱና ፡ የጠላትን ፡ ሰልፍ ፡ ግራ ፡ አጋቡት ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ትንሹ ፡ ኮሎኔል ፡ በየመስኩ ፡ የተበታተኑትን ፡ ሰዎቹን ፡ ለመሰብሰብ ፡ ስምንት ፡ ሰንደቅ ፡ አላማዎች ፡ እንዲተከሉ ፡ አዘዘ ። ፖሊሾቹም ፡ በሰንደቅ ፡ አላማዎቹ ፡ ዙሪያ ፡ ተሰበሰቡ ። ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ሳይደራጁ ፡ ኩኩቤንኮ ፡ የኔዛማይን ፡ መንደር ፡ ኮዛኮች ፡ አስከትሎ ፡ ገስገሰና ፡ ከማሃላቸው ፡ ገብቶ ፡ ወፍራሙን ፡ ኮሎኔል ፡ እሱው ፡ እራሱ ፡ ገጠመው ። ኮሎኔሉም ፡ ኩኩቤንኮን ፡ ለመቋቋም ፡ ስላልቻለ ፡ ፈረሱን ፡ አዙሮ ፡ ጋለበና ፡ ሸሸ ። ኩኩቤንኮም ፡ ተከትሎት ፡ ጋለበና ፡ እያባረረ ፡ ከጦር ፡ ሰራዊቱ ፡ ለየው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በሌላ ፡ ግንባር ፡ የነበረው ፡ ስቴፓን ፡ ጉዝካ ፡ ይህን ፡ ሲመለከት ፤ ኮሎኔሉን ፡ ከፊት ፡ ቀድሞ ፡ ለማቋረጥ ፤ የመጥለፊያ ፡ ገመዱን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ሽምጥ ፡ ጋለበ ። ሲደርስም ፡ ገመዱን ፡ ወርውሮ ፡ በኮሎኔሉ ፡ አንገት ፡ አጠለቀው ። የኮሎኔሉ ፡ ፊት ፡ ወዲያው ፡ ደም ፡ መሰለና ፡ ገመዱን ፡ ለመበጠስ ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ሲታገል ፡ ጉዝካ ፡ በኃይል ፡ ጐተተና ፡ ከፈረሱ ፡ አውርዶ ፡ ጣለው ። ሲወድቅም ፡ ለመሰናከል ፡ የተቸከለ ፡ ችካል ፡ በሆዱ ፡ ተሻጠበትና ፡ እዚያው ፡ ከመሬት ፡ ተጣብቆ ፡ ቀረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጉዝካም ፡ የተሻለ ፡ ዕድል ፡ አላገኘም ። ምን ፡ ጊዜ ፡ እንደደረሱበት ፡ ሳይታወቅ ፤ አራት ፡ ፖሊሾች ፡ ስቴፓን ፡ ጉዝካን ፡ በአራት ፡ ጦር ፡ ወግተው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ አንጠለጠሉት ። ጉዝካም ፡ በአራት ፡ ጦር ፡ ተወግቶ ፡ እንደተንጠለጠለ ፤ «ጠላቶቻችን ፡ ድምጥማጣቸው ፡ ይጥፋ! ሩሲያ ፡ ምድራችን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር!» በማለት ፡ የመጨረሻ ፡ ቃሉን ፡ ተናገረ ።

በጦር ፡ ግንባር ፡ በስተጐን ፡ ሜቴሊትሳ ፤ ፖሊሾቹን ፡ እያከታተለ ፡ ራስ ፡ ራሳቸውን ፡ ይቀጠቅጣል ። በሌላ ፡ ወገን ፡

ደግሞ ፡ ኔቬሊችኪይ ፡ ከነተከታዮቹ ፡ እየገሰገሰ ፡ ይዋጋል ። በሰረገላዎቹ ፡ አጠገብ ፡ ዛክሩቲጉባ ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ያተራምሰዋል ። ራቅ ፡ ብሎ ፡ በሚታዩት ፡ ሠረገላዎችም ፡ አጠገብ ፡ ሶስተኛው ፡ ፒሳሬንኮ ፡ ብቻውን ፡ አንድ ፡ ጓድ ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ለመመለስ ፡ ይከላከላል ። ከእሱ ፡ አልፎ ፡ ባሉት ፡ ሠረገላዎች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ገፍተው ፡ መጥተው ፡ በሠረገላዎቹ ፡ ላይ ፡ እየወጡ ፡ መዋጋት ፡ ጀምረዋል ።

የጦር ፡ መሪያቸው ፡ ታራስ ፤ ፊት ፡ ፊታቸው ፡ እየጋለበ ፤ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ! በባሩድ ፡ ቀንዳችሁ ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለን? የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመምን? ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አልሆኑምን?» አላቸው ።

«በባሩድ ፡ ቀንዳችን ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለ ፤ ባትኮ! የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመም! ኮዛኮች ፡ ድል ፡ አይሆኑም!» አሉት ።

ቦቭዲዩግ ፡ ከልቡ ፡ ሥር ፡ በጥይት ፡ ተመትቶ ፡ ከሠረገላው ፡ ላይ ፡ ወርዶ ፡ ወድቋል ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጨረሻ ፡ ትንፋሹ ፤ «ከዚህ ፡ ዓለም ፡ በመለየቴ ፡ አላዝንም ። ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተወሰነ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ። የሩሲያ ፡ ምድር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር!» አለና ፡ ነፍሱ ፡ ቀድሞ ፡ ላለፉት ፡ ሌሎች ፡ ሽማግሎች ፡ በሩሲያ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ስለሚፈጸመው ፡ ጀብዱና ፡ ለተቀደሰው ፡ ሃይማኖት ፡ ስለሚደረገው ፡ መስዋዕትነት ፡ ለመንገር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በረረች ።

ወዲያው ፡ ከእሱ ፡ ቀጥሎ ፡ የመንደር ፡ ጦር ፡ አለቃው ፡ ባላባን ፡ ወደቀ ። ሲወድቅም ፤ በጦር ፡ በጥይትና ፡ በጐራዴ ፡ ሶስት ፡ ቦታ ፡ ተመትቶ ፡ ነበር ። ባላባን ፡ ከዋናዎቹ ፡ የኮዛክ ፡ ጀግኖች ፡ አንዱ ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ በብዙ ፡ የባህር ፡ ዘመቻዎች ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ሞያ ፡ ሠርቷል ። ነገር ፡ ግን ፡ ከሁሉም ፡ ይበልጥ ፡ የሚደነቅለት ፡ በአናቶሊያ ፡ ወደብ ፡ ላይ ፡ የፈጸመው ፡ ወረራ ፡ ነው ። በዚ



ያን ፡ ጊዜ ፡ ባላባንና ፡ ተከታዮቹ ፡ ብዙ ፡ የቱርክ ፡ ሃብት ፡ ዘርፈው ፡ ሲመለሱ ፡ ክፉ ፡ ዕድል ፡ አጋጠማቸው ። የቱርኮች ፡ መርከብ ፡ ደርሶ ፡ በመድፍ ፡ ከጀልባዎቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ግማሹን ፡ ገለበጠባቸውና ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮችም ፡ ሰመጡ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ባላባንና ፡ ተከታዮቹ ፡ ነፋስ ፡ እየገፋ ፡ እንዲረዳቸው ፡ ሰፋፊ ፡ የኮዛክ ፡ ሱሪያቸውን ፡ ቀድደው ፡ በጀልባዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ወጥረው ፡ አሠሩና ፡ በመድፍ ፡ ፍላጻ ፡ የተሰነጣጠቁትን ፡ ጀልባዎች ፡ ጠጋግነው ፤ በቀን ፡ እንዳይታዩ ፡ ሌሊት ፡ በመጓዝ ፡ እጅግ ፡ ፈጣኑን ፡ የቱርክ ፡ መርከብ ፡ አመለጡት ። ኮዛኮቹ ፡ ሕይወታቸውን ፡ አድነው ፡ ማምለጥ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፤ በኪየቭ ፡ ላለው ፡ የሜዢጐርስክ ፡ ገዳም ፡ አለቃና ፡ እንዲሁም ፡ በዛፖሮዥዬ ፡ ለቅድስት ፡ ድንግል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብዙ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ ያጌጠ ፡ ስጦታ ፡ አመጡ ። ይህንንም ፡ የኮዛኮቹን ፡ መልካም ፡ ዕድል ፡ በማሞገስ ፡ ዘፋኞች ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በዘፈን ፡ ሲያነሱት ፡ ኖረዋል ። አሁን ፡ ባላባን ፡ በሞት ፡ ስቃይ ፡ ተይዞ ፡ አንገቱን ፡ ደፋና ፡ በቀስታ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤ «መኳንንት ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፤ መልካም ፡ የተቀደሰ ፡ ሞት ፡ መሞቴ ፡ ነው ። ሰባት ፡ ቆርጬ ፤ ዘጠኝ ፡ ወግቼ ፡ ጥያለሁ ። ብዙዎችንም ፡ በፈረሴ ፡ ደቅድቄ ፡ ጥያለሁ ። በጥይት ፡ የገደልኋቸውንማ ፡ ቁጥራቸውንም ፡ አላስታውሰው ። ሩሲያ ፡ ምድራችን ፡ ለዘለዓለም ፡ አሸብርቃ ፡ ትኑር!» ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ሲጨርስ ፡ ነፍሱ ፡ በርራ ፡ ሄደች ።

የኮዛኮች ፡ የጀግንነት ፡ አበባ ፡ እየባከነ ፡ ሄደ! ኩኩቤንኮ ፡ ተከብቧል ። ከኔዛማይ ፡ መንደር ፡ ጦር ፡ የተረፉት ፡ ተከታዮቹም ፡ ሰባት ፡ ብቻ ፡ ሲሆኑ ፡ ኃይላቸው ፡ እየደከመ ፡ ሄዷል ። የኩኩቤንኮ ፡ ልብስ ፡ በደም ፡ ርሷል ።

ታራስ ፡ ራሱ ፡ ይህን ፡ ተመለከተና ፡ ሊረዳው ፡ ፈጥኖ ፡ ሄደ ። ግን ፡ አልደረሰለትም ። ታራስና ፡ ሌሎችም ፡ ኮዛኮች ፡ ለእርዳታ ፡ ደርሰው ፡ የከበቡትን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ከማባረራቸው ፡ በፊት ፤ ኩኩቤንኮ ፡ ከልቡ ፡ ሥር ፡ በጦር ፡

ተወግቶ ፡ ወደቀ ። የወጣት ፡ ደሙም ፡ ደንበኛኑ ፡ የተሰበረ ፡ መልካም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ መስሎ ፡ ይጐርፍ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ ኮዛኮች ፡ ተመለከተና ፤ «ጓደኞቼ ፡ ሆይ ፤ እያያችሁኝ ፡ በመሞቴ ፡ አምላክን ፡ አመሰግነዋለሁ ። ከእኛ ፡ በኋላ ፡ የሚፈጠሩት ፤ ከእኛ ፡ የበለጡ ፡ ጀግኖች ፡ እንዲሆኑ ፡ ያድርግልን ። በክርስቶስ ፡ የተወደደችው ፡ የሩሲያ ፡ ምድራችንም ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደተዋበች ፡ ትኑር!» ብሎ ፤ ወጣት ፡ ነፍሱ ፡ ተለይታው ፡ በረረች ። መላዕክትም ፡ ታቅፈው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወሰዷት ። በሰማይም ፡ ክርስቶስ ፤ «ና ፡ በቀኝ ፡ ጐኔ ፡ ተቀመጥ ፡ ኩኩቤንኮ! እነሆ ፡ አንተ ፡ ጓደኞችህን ፡ አልከዳህም ፤ ወራዳ ፡ ተግባርም ፡ አልፈጸምህም ። ቤተ ፡ መቅደሴን ፡ ተከላክለህ ፡ ጠብቀሃታልና ፤ ና ፡ ወደኔ!» ይለዋል ።

የኩኩቤንኮ ፡ ሞት ፡ ሁሉንም ፡ አሳዘናቸው ። የኮዛኮች ፡ ሠልፍ ፡ እየሳሳ ፡ ሄደ ። ብዙ ፤ ብዙ ፡ ጀግኖች ፡ ወድቀዋል ። ሆኖም ፡ አሁንም ፡ ሳያፈገፍጉ ፡ ሥፍራቸውን ፡ እንደያዙ ፡ ናቸው ።

ታራስ ፡ የተረፉትን ፡ ሰዎች ፡ «ታዲያስ ፡ ወንድሞቼ! በባሩድ ፡ ቀንዳችሁ ፡ ገና ፡ ባሩድ ፡ አለን? ጐራዴያችሁ ፡ ገና ፡ አልደነዘምን? የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመምን?» አላቸው ።

እነሱም ፤ «ገና ፡ በቂ ፡ ባሩድ ፡ አለን ፤ ባትኮ! ጐራዴያችንም ፡ ገና ፡ ስለት ፡ ነው! የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ ገና ፡ አልደከመም! ኮዛኮች ፡ አያፈገፍጉም!» ሲሉ ፡ መለሱለት ።

ከዚያ ፤ ምንም ፡ ሰው ፡ የተቀነሰባቸው ፡ ሳይመስል ፡ እንደገና ፡ ወደፊት ፡ ገሠገሡ ። ከመንደር ፡ ጦር ፡ አዛዦች ፡ ውስጥ ፡ የተረፉት ፡ ሦስት ፤ ብቻ ፡ ናቸው ። በየሥፍራው ፡ ደም ፡ ይጐርፋል ። የኮዛኮቹና ፡ የጠላቶቻቸው ፡ ሬሣ ፡ ተነባብሮ ፡ ተከምሮ ፡ ከሰው ፡ ቁመት ፡ በላይ ፡ ሆኗል ። ታራስ ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ቢያስተውል ፤ ገና ፡ ካሁኑ ፡ ጆቢራዎች ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ያንዣብባሉ ። አቤት ፡ ዛሬ ፡ ያጋጠማቸው ፡ ድግሥ!



ኮዛኮቹ ፡ ወደፊት ፡ ገሥግሠው ፡ ሲዋጉ ፡ ሜቴሊትሲያን ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ አንጠለጠሉት ። በአንድ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛው ፡ ፒሳሬንኮ ፡ አንገቱ ፡ በጐራዴ ፡ ተቆርጦ ፡ ተሽከረከረ ። ኦኸሪም ፡ ጉስካ ፡ አራት ፡ ቦታ ፡ ተመትቶ ፡ ወደቀ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «አሁን ፡ ነው ፡ እንግዲህ!» አለና ፡ መሐረቡን ፡ አወዛወዘ ። ኦስታፕም ፡ ምልክቱን ፡ አየና ፤ ካደፈጠበት ፡ ቦታ ፡ ተመድርሮ ፡ ወጥቶ ፡ ፖሊሾቹን ፡ እያጣደፈ ፡ መሰናክል ፡ እንዲሆን ፡ ተብሎ ፡ ጋሬጣና ፡ የጦር ፡ ስብርባሪ ፡ ወደተቸከለበት ፡ ሥፍራ ፡ ነዷቸው ። እዚያ ፡ ሲደርሱም ፡ ፈረሶቻቸው ፡ እየተደናቀፉ ፡ ሲወድቁ ፤ ሰዎቹም ፡ እየወረዱ ፡ ይከስከሱ ፡ ጀመር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ጀርባ ፡ ራቅ ፡ ብለው ፡ ያደፈጡት ፡ የኮርሱኝ ፡ ኮዛኮች ፤ ጠላቶቻቸው ፡ ለጠመንጃ ፡ ተኩስ ፡ መቅረባቸውን ፡ ተመለከቱና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የጥይት ፡ በረዶ ፡ አረገፉባቸው ። ፖሊሾቹ ፡ ከመሸበር ፡ የተነሣ ፡ የሚያደርጉት ፡ ግራ ፡ ገባቸው ። በዚህም ፡ ኮዛኮቹ ፡ ተበረታቱና ፤ «ድሉ ፡ የኛ ፡ ነው!» እያሉ ፡ ከያለበት ፡ ይጮሁ ፡ ጀመር ። ወዲያው ፡ መለከት ፡ እየነፉ ፡ የድል ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማቸውን ፡ ዘረጉ ። ፖሊሾቹ ፡ በሽብር ፡ እየተሩዋሩዋጡ ፡ መሸሸጊያ ፡ ይፈልጉ ፡ ጀመር ።

ታራስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ በር ፡ ተመለከተና ፤ «የለም ፤ ድሉ ፡ የኛ ፡ አይደለም!» አለ ። በዕውነትም ፡ አልተሳሳተም ። የከተማው ፡ በር ፡ ተከፍቶ ፡ ምርጥ ፡ የሆኑ ፡ ጀግኖች ፡ ያሉበት ፡ የፈረሰኛ ፡ ጦር ፡ ገሥግሦ ፡ ወጣ ። ጦረኞቹ ፡ የተቀመጡዋቸው ፡ ፈረሶች ፡ ትልልቅና ፡ ፈጣን ፡ ነበሩ ። በመልኩም ፡ በጀብዱም ፡ ከሁሉ ፡ የላቀ ፡ መኳንንት ፡ ፊት ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ ይጋልባል ። ከነሐስ ፡ ጥሩሩ ፡ ዘልቆ ፡ የወረደው ፡ ጥቁር ፡ ፀጉሩ ፡ በነፋስ ፡ ይውለበለባል ። እጅግ ፡ በተዋቡ ፡ ቆንጆ ፡ ጣቶች ፡ የተጠለፈ ፡ ያማረ ፡ መሐረብ ፡ በክንዱ ፡ ላይ ፡ አስሯል ። ታራስ ፡ ይህ ፡ መኰንን ፡ እንድሬይ ፡

መሆኑን ፣ ባየ ፣ ጊዜ ፤ በመገረም ፣ ደነዘዘ ። አንድሬይ ፣ በክ
ንዱ ፣ ላይ ፣ ለታሠረለት ፣ ማስታወሻ ፣ ተገቢ ፣ ጀግና ፣ መሆኑ
ን ፣ ለማስመስከር ፣ እንደ ፣ አዳኝ ፣ ውሻ ፣ በሚያስደንቅ ፣ ቅል
ጥፍና ፣ ከውጊያው ፣ ማሃል ፣ ገብቶ ፣ ግራና ፣ ቀኝ ፣ ያተራም
ሰው ፣ ጀመር ። ሽማግሌው ፣ ታራስ ፤ አንድሬይ ፣ ከፊቱ ፣
ያሉትን ፣ ሁሉ ፣ በጐራዴ ፣ እየጨፈጨፈ ፣ ሲበታትናቸው ፣
ባየ ፣ ጊዜ ፣ አላስችል ፣ ብሎት ፤ «እንዴት! ጓደኞችህ? ጓደ
ኞችህን ፣ ትገድላለህ ፤ አንተ ፣ የሰይጣን ፣ ልጅ?» አለና ፣ ጮ
ኸ ። አንድሬይ ፣ ግን ፣ ከፊቱ ፣ ያሉት ፣ እነማን ፣ እንደሆኑ ፤
ጠላት ፣ ይሁኑ ፣ ወይም ፣ ወዳጅ ፣ አይታዩትም ። ለእሱ ፣ የሚ
ታየው ፤ የሃር ፣ ጉንጉን ፣ የመሰለ ፣ ረጅም ፣ ጐፈሬ ፤ እንደ
በረዶ ፣ የነጣ ፣ አንገትና ፣ ደረት ፤ በጠቅላላው ፣ ለፍቅርና ፣
ለመሳም ፣ የተፈጠረ ፣ የአንዲት ፣ ቆንጆ ፣ አካል ፣ እንጂ ፣
ሌላ ፣ ምንም ፣ ነገር ፣ አይታየውም ።

«ስሙኝ ፣ ልጆቼ! እንደምንም ፣ በሉና ፣ ወደዚያ ፣ ጫካ ፣
አምጡልኝ!» አለና ፣ ታራስ ፣ ለኮዛኮቹ ፣ ጮኾ ፣ ተናገረ ። ወዲ
ያው ፣ ከመቅጽበት ፣ ፈጣን ፣ ጋላቢ ፣ የተባሉ ፣ ሠላሳ ፣ ኮዛ
ኮች ፣ ትዕዛዙን ፣ ለመፈጸም ፣ ጋልበው ፣ ሄዱ ። እንደሄዱም ፣
ከጠላት ፣ ፈረሰኞች ፣ ግንባር ፣ ቀደሞቹን ፣ ከሌላው ፣ ጦር ፣
ቆርጠው ፣ ለይተው ፣ ጥቂት ፣ ከወጓቸው ፣ በኋላ ፣ ጐሎኮ
ፒቴንኮ ፣ አውቆ ፣ ለማናደድ ፣ ሲል ፣ የአንድሬይን ፣ ጀርባ ፣
በጐራዴ ፣ ጥፌ ፣ ቸብ ፣ አደረገውና ፣ ኮዛኮቹ ፣ በሞላ ፣ ዞረው ፣
በአስደናቂው ፣ የኮዛክ ፣ ፍጥነት ፣ ጋልበው ፣ ሸሹ ። አንድ
ሬይ ፣ እጅግ ፣ ተናደደ! በደም ፣ ሥሮቹ ፣ ሁሉ ፣ ያለው ፣ የወ
ጣት ፣ ደሙ ፣ ይፈላ ፣ ጀመር! ወዲያው ፣ ፈረሱን ፣ ኮለኮለና ፣
ኮዛኮቹን ፣ ተከትሎ ፣ ሽምጥ ፣ ጋለበ ። አንድ ፣ ጊዜም ፣ ዞሮ ፣
ወደኋላው ፣ አልተመለከተም ። በእሱ ፣ ፍጥነት ፣ ልክ ፣ ሊከ
ተሉት ፣ የቻሉት ፣ ሐያ ፣ የሚሆኑ ፣ ፈረሰኞች ፣ ብቻ ፣ መሆ
ናቸውን ፣ አላወቀም ። ኮዛኮቹ ፣ እንደጋለቡ ፣ ሄደው ፣ ወደ ፣
ጫካው ፣ ዘወር ፣ አሉ ። አንድሬይም ፣ እነሱን ፣ ተከትሎ ፣



እየጋለበ ፣ ጐሎኮፒቴንኮን ፣ ሊደርስበት ፣ ሲል ፤ አንድ ፣ ጠን
ካራ ፣ እጅ ፣ የፈረሱን ፣ ልጓም ፣ ለቀም ፣ አድርጐ ፣ ያዘበት ።
ወዲያው ፣ አንድሬይ ፣ ዘወር ፣ ብሎ ፣ ቢመለከት ፣ ታራስ ፣
ከፊቱ ፣ ቆሞ ፣ አየ! በዚህን ፣ ጊዜ ፣ ሰውነቱ ፣ ሁሉ ፣ ተንቀ
ጠቀጠ ፤ ፊቱም ፣ በአንድ ፣ አፍታ ፣ ጠወለገ ።

በተማሪ ፣ ቤት ፣ ጓደኛው ፣ በማስመሪያ ፣ መትቶት ፣ የሮ
ጠ ፣ ልጅ ፤ የመታውን ፣ ጓደኛውን ፣ ሲያባርር ፣ እበሩ ፣ ላይ ፣
ድንገት ፣ ከአስተማሪው ፣ ጋር ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣ በተገናኘ ፣ ጊዜ ፣
ንዴቱን ፣ ውጦ ፣ በድንጋጤ ፣ እንደሚቆም ፣ ሁሉ ፣ የአንድ
ሬይም ፣ ንዴት ፣ ከመቅጽበት ፣ ጠፋና ፤ ከፊቱ ፣ የቆመው ፣
የሚያስፈራው ፣ አባቱ ፣ ብቻ ፣ ታየው ።

ታራስ ፣ የልጁን ፣ ዓይን ፣ ዓይኑን ፣ ትክ ፣ ብሎ ፣ እየተመ
ለከተ ፤ «በል ፤ አሁን ፣ ታዲያ ፣ ምን ፣ እናድርግ?» አለው ። አን
ድሬይ ፣ ግን ፣ ምን ፣ እንደሚመልስ ፣ ስላላወቀ ፣ ዓይኖቹን ፣
መሬት ፣ ላይ ፣ ተክሎ ፣ ዝም ፣ አለ ።

«ታዲያስ ፣ ልጄ ፤ ፖሊሾቹ ፣ ጠቀሙህ?»

አንድሬይ ፣ ምንም ፣ መልስ ፣ አልሰጠም ።

«እንዴት ፣ ሃይማኖትህን ፣ ትክዳለህ? እንዴት ፣ ጓደ
ኞችህን ፣ ትክዳለህ? በል ፣ እንግዲህ ፤ ከፈረስህ ፣ ውረድ!»
አለው ፣ ታራስ ።

አንድሬይም ፣ እንደ ፣ ታዛዥ ፣ ሕፃን ፣ ከፈረሱ ፣ ወርዶ ፣
ከታራስ ፣ ፊት ፣ ቆመ ።

«በል ፣ ሳትንቀሳቀስ ፣ ቀጥ ፣ ብለህ ፣ ቁም! እኔው ፣ ወለ
ድሁህ ፤ እኔው ፣ እገድልሃለሁ!» አለና ፣ ታራስ ፣ ያነገተውን ፣
ጠበንጃ ፣ አወለቀ ።

አንድሬይ ፣ አመድ ፣ መስሎ ፣ ገርጥቶ ፣ ቆመ ። እንደ
ቆመም ፣ አንድ ፣ ስም ፣ በመጥራት ፣ ከንፈሮቹ ፣ ቀስ ፣ ብለው ፣
ተንቀሳቀሱ ። የጠራው ፤ የሃገሩን ፣ ስም ፤ የእናቱን ፣ ስም ፤
ወይም ፣ የወንድሞቹን ፣ ስም ፣ አይደለም ። የዚያችን ፣ የፖ
ላንድ ፣ ቆንጆ ፣ ስም ፣ ነው ። ወዲያው ፣ ታራስ ፣ ተኮሰ ።

በስለት ፡ እንደተመታ ፡ አገዳ ፡ አንገቱን ፡ ዘንበል ፡ አድርጐ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ሳይተነፍስ ፤ አንድሬይ ፡ ሣሩ ፡ ላይ ፡ ሽብልል ፡ አለ ።

የገዛ ፡ ልጁ ፡ ገዳይ ፤ ለረጅም ፡ ጊዜ ፡ ቆሞ ፡ በድኑን ፡ አካል ፡ ተመለከተው ። ከሞተ ፡ በኋላም ፡ እንኳን ፡ የተዋበ ፡ ጐልማሳ ፡ ነበር ። ከአጭር ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የሕይወትን ፡ ኃይልና ፡ ግርማ ፡ የተጐናጸፈው ፤ የማንንም ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ የሚማርክ ፡ ቆንጆው ፡ የወንድ ፡ መልኩ ፡ አሁንም ፡ እንደተዋበ ፡ ነው ።

«እንዴት ፡ ያለ፡ ኮዛክ ፡ ይሆን ፡ ነበር! ቁመቱ ፡ ሎጋ ፤ ቅንድቡ ፡ ጥቁር ፤ መልኩ ፡ ገራም ፤ በውጊያ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ክንደ ፡ ጠንካራ! ታዲያ ፡ አሁን ፡ በከንቱ ፡ ተቀጨ ። እንደ ፡ ልክስክስ ፡ ውሻ ፤ በውርደት ፡ ተቀጨ!» አለ ፡ ታራስ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ኦስታፕ ፡ ጋልቦ ፡ መጣና ፤ «ባትኮ ፤ ምንድን ፡ ነው ፡ ያደረግኸው? አንተ ፡ ነህ ፡ የገደልኸው?» አለና ፡ ጠየቀው ።

ታራስም ፡ ራሱን ፡ በመነቅነቅ ፡ መለሰለት ።

ኦስታፕ ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የጋረዳቸውን ፡ የወንድሙን ፡ ዓይኖች ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተና ፡ በሐዘን ፡ ተዋጠ ። ወዲያው ፡ አባቱን ፤ «ባትኮ ፤ ጠላቶቻችን ፡ እንዲያዋርዱት ፡ ወይም ፡ አሞራ ፡ እንዳይበላው ፡ በክብር ፡ እንቅበረው ፡» አለው ።

ታራስም ፤ «እኛም ፡ ሳንረዳቸው ፡ እነሱው ፡ ይቀብሩታል ። ብዙ ፡ የሚያለቅሱለትና ፡ የሚያዝኑለትም ፡ ሞልተዋል ፡» አለ ።

ሆኖም ፡ ለአንድ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ያህል ፡ ቆሞ ፡ እዚኸው ፡ ወድቆ ፡ ተኩላ ፡ ይብላው ፡ ወይስ ፡ ስለጀግንነቱ ፡ የክብር ፡ ቀብር ፡ ይደረግለት? እያለ ፡ ሲያሰላስል ፤ ወዲያው ፡ ጐሎኮፒቴንኮ ፡ ወደሱ ፡ እየጋለበ ፡ ሲመጣ ፡ አየ ።

«ወዮልን ፤ ኮሎኔል! ፖሊሾቹ ፡ ተጨማሪ ፡ ጦር ፡ ለእርዳታ ፡ ደርሶላቸው ፡ ጠንክረዋል!»



ጐሎኮፒቴንኮ ፡ ይህን ፡ ከመናገሩ ፤ ቮቭቱዜንኮ ፡ ጋልቦ ፡ ደረሰ ።

«ወዮልን ፡ ኮሎኔል! አዲስ ፡ ጉልበት ፡ ጦር ፡ መጥቶብናል!»

ቮቭቱዜንኮ ፡ ይህን ፡ ከመናገሩ ፡ ፒሳሬንኮ ፡ በእግሩ ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ፡ «ባትኮ ፡ የት ፡ ነው ፡ ያለህ? ኮዛኮች ፡ ይፈልጉሃል ። የጦር ፡ አለቃው ፡ ኔቪሊችኪይ ፡ እንዲሁም ፡ ዛዶሮዥኒይና ፡ ቼሬቪቼንኮ ፡ ሞተዋል! ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮች ፡ አንተን ፡ ሳናይ ፡ አንሞትም ፡ ብለው ፡ ጸንተው ፡ ቆመዋል ። በመሞቻቸው ፡ ሰዓት ፡ አንተ ፡ እንድታያቸው ፡ ይፈልጋሉ ፡» አለ ።

«ፈረስህ ፡ ላይ ፡ ውጣ ፤ ኦስታፕ!» አለና ፡ ታራስ ፡ በዚች ፡ በመጨረሻዋ ፡ የሞት ፡ ሰዓት ፡ ኮዛኮቹን ፡ ሊያያቸውና ፡ እነሱም ፡ የጦር ፡ መሪያቸውን ፡ እንዲያዩት ፡ ወደነሱ ፡ ለመሄድ ፡ ተጣድፎ ፡ ተነሳ ።

ነገር ፡ ግን ፡ እነታራስ ፡ ከነበሩበት ፡ ጫካ ፡ ጋልበው ፡ ከመውጣታቸው ፡ በፊት ፤ ጦርና ፡ ጐራዴ ፡ የያዙ ፡ የጠላት ፡ ፈረሰኞች ፡ የጫካውን ፡ ዙሪያ ፡ ከብበው ፡ በየዛፎቹ ፡ መካከል ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ አሉ ።

«ኦስታፕ! ኦስታፕ! አይዞህ ፡ በርታ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ጐራዴውን ፡ መዝዞ ፡ ወዲህም ፡ ወዲያም ፡ ይሰነዝር ፡ ጀመር ።

ስድስት ፡ ፈረሰኞች ፡ ተመድርፈው ፡ ወደ ፡ ኦስታፕ ፡ ገሰገሱ ። ግን ፡ ክፉ ፡ ዕጣ ፡ ወደቀባቸው ። ያንዱ ፡ አንገት ፡ ወዲያው ፡ ተሽከርክሮ ፡ በረረ ። ሌላው ፡ ፈረሱን ፡ እገታለሁ ፡ ሲል ፡ ወርዶ ፡ በጭንቅላቱ ፡ ተከሰከሰ ። ሶስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ደረቱ ፡ በጦር ፡ ተበሳ ። አራተኛው ፡ ፈረሱ ፡ በጥይት ፡ ተመታና ፡ አገርግሮ ፡ ሲወድቅ ፡ ከሥር ፡ አድርጐ ፡ ጨፈለቀው ።

«እንዲያ ፡ ነው ፤ ልጄ! ጐሽ ፡ እንዲያ ፡ ነው ፤ ኦስታፕ! እኔም ፡ እንዲሁ ፡ እሠራላቸዋለሁ!» ብሎ ፡ ጮኸና ፤ ታራስ ፡ ጠላቶቹን ፡ መጨፈጭፍ ፡ ቀጠለ ። ዓይኑን ፡ ከኦስታፕ ፡ ላይ ፡

ሳይነቅል ፡ ጐራዴውን ፡ ግራና ፡ ቀኝ ፡ እየሰነዘረ ፡ በከበቡት ፡ ጠላቶቹ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያሳርፈው ፡ ጀመር ። ወዲያው ፣ ስምንት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ አስታጥን ፡ ሲከብቡት ፡ አየና ፣ «አስታጥ! አስታጥ! አይዞህ ፡ ጠንክር!» እያለ ፡ ሲያበረታታው ፣ አስታጥ ፡ ግን ፡ በቁጥር ፡ ስላየሉበት ፡ ሊቋቋማቸው ፡ አልቻለም ።

ወዲያው ፡ ገመድ ፡ ወርውረው ፡ አንገቱን ፡ ጠለፉትና ፡ ተብትበው ፡ አሥረው ፡ ወሰዱት ።

ታራስ ፣ «አስታጥ! ወይኔ ፡ አስታጥ! አስታጥ!» እያለ ፡ ከፊቱ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ሁሉ ፡ እየጨፈጨፈ ፣ ለልጁ ፡ ለመድረስ ፡ ይጥር ፡ ጀመር ።

ግን ፡ ወዲያው ፡ እሱም ፡ ራሱ ፡ በአንድ ፡ ከባድ ፡ ነገር ፡ ሲመታ ፡ ተሰማው ። የሚያየው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚዞር ፡ የሚሽከረከር ፡ መሰለው ። ለአጭር ፡ ጊዜ ፣ የሰው ፡ ጭንቅላት ፣ ጦር ፣ ጢስና ፡ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ተዘበራርቆ ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ዞረበት ። ከዚያ ፡ ጭጋግ ፡ እንደጋረደው ፡ ሁሉ ፡ ብዥ ፡ አለበት ። ወዲያው ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ወርካ ፡ ጅው ፡ ብሎ ፡ ወደቀና ፡ ዓይኖቹን ፡ ከባድ ፡ ጉም ፡ ሸፈናቸው ።

## ምዕራፍ ፡ አሥር ።

ታራስ ፡ ከከባድ ፡ ስካር ፡ በኋላ ፡ ከእንቅልፍ ፡ ነቅቶ ፡ ጠፍቶ ፡ የነበረውን ፡ አዕምሮውን ፡ እንዳገኘ ፡ ሰው ፡ ያለበት ፡ አካባቢ ፡ ግራ ፡ ገብቶት ፣ «እንዴት ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ የተኛሁት!» አለ ። እጅና ፡ እግሩ ፡ በድካም ፡ ዝሎ ፡ ተሳስሯል ። እንግዳ ፡ የሆነ ፡ ክፍል ፡ ጣራና ፡ ግድግዳ ፡ ድብዝዝ ፡ ብሎ ፡ በፊቱ ፡ እንደሚሽከረከር ፡ ሁሉ ፡ ብዥ ፡ ብዥ ፡ አለበት ። በመጨረሻ ፡ አጠገቡ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ ትንፋሹን ፡ ሲያዳምጥ ፡ የቆየውን ፡ ቶቭካችን ፡ አየው ።

ቶቭካችም ፡ በልቡ ፣ አዎ ፣ እንዲያውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ተኝተህ ፡ ልትቀር ፡ ነበር!» ብሎ ፡ አሰበና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳይናገር ፡ ታራስ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ እንዲጋደም ፡ በምልክት ፡ አሳየው ።

ታራስ ፡ ግን ፣ «ንገረኝ ፡ እንጂ ፣ ለመሆኑ ፡ የት ፡ ነው ፡ ያለሁት?» አለና ፡ የሆነውን ፡ ሁሉ ፡ ለማስታወስ ፡ ይሞክር ፡ ጀመር ።

ጓደኛውም ፣ «እርፈህ ፡ ተኛ! ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ምን ፡ ትፈልጋለህ? የሥራ ፡ አካላትህ ፡ እንደተቆራረጠ ፡ አትመለከትም? አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳልቆም ፡ አንተን ፡ ይዤ ፡ ስጋልብ ፡ ይኸው ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ቀኔ ፡ ነው ። አንተም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ መንገድ ፡ ስንመጣ ፡ ትኩሳት ፡ ተነስቶብህ ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ስትቀባጅር ፡ ነበር ። በፀጥታ ፡ ስትተኛ ፡ ይህ ፡ የመጀመሪያ ፡ ጊዜህ ፡ ነው ። ስለዚህ ፣ ኋላ ፡ ስቃይ ፡ እንዳይደርስብህ ፡ እርፈህ ፡ ብትተኛ ፡ ይሻልሃል ።» አለና ፡ ተቆጣው ።

ታራስ ፡ አሁንም ፡ ምን ፡ እንደደረሰበት ፡ ከመጀመሪያው ፡ ለማስታወስ ፡ መሞከሩን ፡ አልተወም ።

«አዎ ፣ ተከብቤ ፣ ፖሊሾች ፡ ሊማርኩኝ ፡ እንደነበር ፡ ትዝ ፡ ይለኛል! ያንን ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ጥሶ ፡ ለመውጣት ፡ ምንም ፡ ዘዴ ፡ አልነበረኝም!» አለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቶቭካች ፣ ተንኮለኛ ፡ ህፃን ፡ እያስቸገራት ፡ ትዕግሥቷ ፡ እንዳለቀ ፡ ሞግዚት ፡ በቁጣ ፡ ጮኾ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፣

«ዝም ፡ በል ፡ ነው ፡ የምልህ ፣ አንት ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! እንዴት ፡ እንዳመለጥህ ፡ ማወቁ ፡ ምን ፡ ይጠቅምሃል? ዋናው ፡ ነገር ፡ ማምለጥህ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ማወቅ ፡ የሚገባህ ፣ የማይከዱህ ፡ ሰዎች ፡ መኖራቸውን ፡ ብቻ ፡ ነው! ገና ፡ ረጅም ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ሌሊት ፡ መጓዝ ፡ አለብን ፣ ለመሆኑ ፡ እንደተራ ፡ ኮዛክ ፡ የምትፈለግ ፡ መስሎሃል? የለም ፣ እጅህን ፡ ይዞ ፡ ለሚሰጣቸው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ጉርሻ ፡ አውጀዋል ።»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፤ «አስታፕስ ፡ እንዴት ፡ ሆነ?»
ብሎ ፡ ጮኸና ፡ አስታፕ ፡ እሱው ፡ እያየው ፡ ተይዞ ፡ እንደታ
ሠረና ፡ አሁንም ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ መሆኑ ፡ ትዝ ፡ ብሎት ፡
ለመነሳት ፡ ይፍጨረጨር ፡ ጀመር ።

የሽማግሌ ፡ ልቡ ፡ በሐዘን ፡ ተጨበጠ ። ቁስሉ ፡ የታ
ሰረበትን ፡ ከየሥፍራው ፡ መንጫጭቆ ፡ ወረወረው ። ሊናገርም ፡
ሞከረ ። ግን ፡ ትኩሳትና ፡ ቅዠት ፡ ተነሳበትና ፡ እየተንቀ
ጠቀጠ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ይቀባጅር ፡ ጀመር ። ታማ
ኙ ፡ ጓደኛው ፡ በንዴት ፡ እየተሳደበ ፡ ቆሞ ፡ ይመለከተዋል ።
ወዲያው ፡ እጅና ፡ እግሩን ፡ ያዘና ፡ እንደ ፡ ህፃን ፡ ጨብጦ ፡
ቁስሉን ፡ ሁሉ ፡ እንደገና ፡ ካሰረለት ፡ በኋላ ፡ በጀንዲ ፡ ጠቅል
ሎ ፡ ከኮርቻው ፡ ጋር ፡ በገመድ ፡ ጠፍር ፡ አስሮት ፡ እሱም ፡
ተፈናጥጦ ፡ ይዞት ፡ ጋለበ ።

«ብትሞትም ፡ ብትቆምም ፡ እዚያው ፡ አደርስሃለሁ!
ፖሊሾች ፡ በኮዛክ ፡ አጽምና ፡ ደምህ ፡ እያፌዙ ፡ ሰውነትህን ፡
ቆራርጠው ፡ እንዲጥሉህ ፡ አልፈቅድላቸውም ። አሞራ ፡ ዓይ
ንህን ፡ ቢያነቁረውም ፤ የሃገራችን ፡ መስክ ፡ አሞራ ፡ ይሁን ፡
እንጂ ፤ ከፖላንድ ፡ ምድር ፡ የሚነሳ ፡ አሞራ ፡ አይሆንም ።
ሞትህም ፡ ቆምህም ፤ ኡክሬይን ፡ አደርስሃለሁ!» አለና ፡ ታማ
ኙ ፡ ጓደኛ ፡ ሌት ፡ ተቀን ፡ ጋልቦ ፡ ታራስን ፡ አሁንም ፡ ያው ፡
እንደ ፡ በድን ፡ እንደሆነ ፡ ከዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ አደረሰው ።
እዚያም ፡ ያለመሰልቸት ፡ በቅጠላ ፡ ቅጠልና ፡ በቅባት ፡ መድ
ሃኒት ፡ እያከመ ፡ ከዚህም ፡ ሌላ ፡ አንዲት ፡ አይሁዳዊት ፡ መድ
ሃኒት ፡ አዋቂ ፡ ሴት ፡ ፈልጐ ፡ አምጥቶ ፡ እሷም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡
ልዩ ፡ አይነት ፡ መድሃኒት ፡ እየቀመመች ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡
ካጠጣችው ፡ በኋላ ፡ ታራስ ፡ ማገገም ፡ ጀመረ ። የመድሃኒ
ቱ ፡ ኃይል ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ የጸናው ፡ የእ
ሱ ፡ የራሱ ፡ የመንፈስ ፡ ብርታት ፡ ረድቶት ፡ በአንድ ፡ ወር ፡
ተኩል ፡ ጊዜ ፡ ቁስሉ ፡ ሁሉ ፡ ድኖ ፡ ቆሞ ፡ ለመሄድ ፡ ቻለ ።
ምን ፡ ያህል ፡ ከባድ ፡ ቁስል ፡ ቆስሎ ፡ እንደነበር ፡ ምልክት ፡



ሆኖ ፡ የሚያስረዳው ፡ በጐራዴ ፡ ተመትቶ ፡ የዳነው ፡ የቁስ
ሉ ፡ ለምጥ ፡ ብቻ ፡ ነበር ።ነገር ፡ ግን ፡ ትካዜና ፡ ሐዘን ፡ እን
ደተጫነው ፡ ይታይበት ፡ ጀመር ። ግንባሩ ፡ ዘወትር ፡ እንደ
ተኮፋተረ ፡ ነው ። አካባቢውን ፡ ሲመለከት ፤ በሴቹ ፡ ውስጥ ፡
ሁሉም ፡ ነገር ፡ ተለውጧል ። የቀድሞ ፡ ጓደኞቹ ፡ ሁሉ ፡
ሞተዋል ። ለተቀደሰው ፡ የሃይማኖትና ፡ የወንድማማችነት ፡
ዓላማ ፡ ከተሰለፉት ፡ ውስጥ ፡ አንድም ፡ እንኳን ፡ አልተረፈ
ም ። ታታሮቹን ፡ ተከታትለው ፡ ከኮሼቮይው ፡ ጋር ፡ የዘመ
ቱትም ፡ ከጠፉ ፡ ቆይተዋል ። አንዳንዶቹ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፤
አንዳንዶቹም ፡ ምግብና ፡ ውኃ ፡ በሌለበት ፡ በክሪሚያ ፡ የጨ
ው ፡ ባህር ፡ ረግረግ ፤ አንዳንዶቹም ፡ ተማርከውና ፡ ተዋር
ደው ፡ ቀልጠው ፡ ቀርተዋል ። የቀድሞው ፡ ኮሼቮይና ፡ ሌሎ
ቹም ፡ የታራስ ፡ የጥንት ፡ ጓደኞች ፡ አሁን ፡ የሉም ። በጊዜ
ያቸው ፡ ጠንካራ ፡ የኮዛክ ፡ ኃይል ፡ በነበሩት ፡ ጀግኖች ፡ ላይ ፡
አሁን ፡ አረም ፡ በቅሎባቸዋል ። ለታራስ ፡ ያለፈው ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ እንዳንድ ፡ ድብልቅልቅ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ድግስ ፡ ሆኖ ፡
ታየው ። በድግሱም ፡ ላይ ፡ ተጋባዦች ፡ እንግዶችና ፡ አሽ
ከሮች ፡ ሰሃንና ፡ ድስቱን ፡ ሁሉ ፡ ሰባብረው ፤ አንድ ፡ ጠብታ ፡
የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንኳን ፡ ሳይተርፍ ፡ ከፍተኛ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸ
ውን ፡ ብርጭቆዎችና ፡ ጸዋዎች ፡ ዘርፈው ፤ በመጨረሻ ፡ ጌ
ትዮው ፤ «ምነው ፡ ይህ ፡ ድግስ ፡ ባልተደገሰ ፡ ኖሮ ፡» ብሎ ፡
ይፀፀታል ።

በሠፈሩ ፡ ያሉት ፡ ሁሉ ፡ ታራስን ፡ ለማጽናናትና ፡ ለማ
ስደሰት ፡ ቢደክሙ ፡ ምንም ፡ አልሆነላቸውም ። ሽበቶና ፡
ረጅም ፡ ጢም ፡ ያላቸው ፡ ባንዱራ ፡ መችዎችም ፡ ሁለትና ፡
ሶስት ፡ ሆነው ፡ እየመጡ ፡ የኮዛክ ፡ ጀግንነቱን ፡ ለማሞገስ ፡
ቢሞክሩ ፡ ከንቱ ፡ ልፋት ፡ ሆነባቸው ። ማናቸውንም ፡ ነገር ፡
በቀዘቀዘ ፡ አስተያየት ፡ እየተመለከተ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡
ፊቱ ፡ መሪር ፡ ሃዘን ፡ ይጐናፀፍና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፤ «ወይ ፡
ልጄ! ልጄ ፡ አስታፕ!» እያለ ፡ ይተክዛል ።

ዛፖሮዥያኖች ፡ ለዘረፉ ፡ ባህር ፡ አቋርጠው ፡ ዘመቱ ። ሁለት ፡ መቶ ፡ ጀልባዎች ፡ በድኔፐር ፡ ወጥተው ፡ ዘለቁና ፡ የእስያ ፡ ማይነርን ፡ ወደቦች ፡ ለእሳትና ፡ ለጐራዴ ፡ ዳረጓቸው ። የጨፈጨፋት ፡ የእስላም ፡ ሕዝብም ፡ የራስ ፡ ጥምጥም ፡ ደም ፡ በጠባው ፡ መስክ ፡ ተበታትኖና ፡ በውሃው ዳርም ፡ ሲንሳፈፍ ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። እስያ ፡ ማይነር ፡ ብዙ ፡ ሰፋፊ ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ሱሪዎችና ፡ ጥቋቁር ፡ የኮዛክ ፡ አለንጋ ፡ የጨበጡ ፡ ጠያይም ፡ እጆች ፡ ተመለከተች ። ዛፖሮዥያኖቹ ፡ በየጓሮው ፡ የወይኑን ፡ ፍሬ ፡ ጨርሰው ፡ አትክልቱን ፡ መነጣጥረው ፡ አጠፉት ። በየመስጊዱ ፡ የፈረሶቻቸው ፡ ፋንድያ ፡ ተከመረበት ። የከበሩ ፡ የፔርሺያ ፡ ጨርቃ ፡ ጨርቆችን ፡ እየቀዳደዱ ፡ ድግ ፡ አደረጓቸው ። ብዙ ፡ ዘመን ፡ ካለፈም ፡ በኋላ ፡ አጫጭር ፡ የዛፖሮዥያን ፡ የትንባሆ ፡ ማጨሻቸው ፡ በየመስኩ ፡ ወድቆ ፡ ይገኝ ፡ ነበር ። ሃገሩን ፡ አውከውና ፡ ዘርፈው ፡ በደስታ ፡ ተመልሰው ፡ ጉዞ ፡ ጀመሩ ። በጀልባዎቻቸው ፡ ሲጓዙም ፤ ባለአሥር ፡ መድፍ ፡ የቱርክ ፡ መርከብ ፡ ደረሰባቸውና ፡ በአንድ ፡ እሩምታ ፡ ተኩስ ፡ ትናንሽ ፡ ጀልባዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በታተነባቸው ። ከነሱም ፡ ሲሶ ፡ የሚሆኑት ፡ እዚያው ፡ ሰምጠው ፡ ሲቀሩ ፤ ሌሎቹ ፡ ግን ፡ ተረዳድተው ፡ ሶስት ፡ እንስራ ፡ ሙሉ ፡ ወርቅ ፡ እንደጫኑ ፡ ከድኔፐር ፡ ወደብ ፡ ደረሱ ። ነገር ፡ ግን ፡ ታራስ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከምንም ፡ አልቆጠረውም ። እንደሚያድን ፡ ሁሉ ፡ መስኩን ፡ አቋርጦ ፡ ሩቅ ፡ ይሄድና ፡ አንድም ፡ ጥይት ፡ ሳይተኩስ ፡ ይመለሳል ። ለአደን ፡ ብሎ ፡ በሚወጣበት ፡ ሰዓት ፡ ጠበንጃውን ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አጋድሞ ፡ በትካዜ ፡ ይጨበጥና ፡ ከባህሩ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፤ «ልጄ ፡ ኦስታፕ! ወይ ፡ ልጄ ፤ ኦስታፕ!» እያለ ፡ በመደጋገም ፡ ሲተክዝ ፡ ለብዙ ፡ ሰዓት ፡ ይጐለታል ። ከፊቱ ፡ ጥቁር ፡ ባህር ፡ ተንጣልሎ ፡ ያንፀባርቃል ። የባህር ፡ አሞሮች ፡ ራቅ ፡ ባሉ ፡ ቄጠማዎች ፡ መካከል ፡ ይጫጫሃሉ ። የታራስ ፡



ነጭ ፡ ጢም ፡ እንደ ፡ ብር ፡ ይብለጨለጫል ። እንባውም ፡ ከዓይኖቹ ፡ እየተንኳለለ ፡ ይወርዳል ።

ወደ ፡ ኋላ ፡ ታራስ ፡ ይህንን ፡ መሪር ፡ ሃዘንና ፡ ትካዜ ፡ በፍጹም ፡ አልቻለውም ።

«የሆነው ፡ ይሁን ፡ እንጂ ፤ ሄጄ ፡ የደረሰበትን ፡ ሁናቴ ፡ ማወቅ ፡ አለብኝ ። በሕይወት ፡ አለ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ መቃብር ፡ ውስጥ ፡ ይሆን? ወይስ ፡ ሞቶ ፡ ቀባሪ ፡ አጥቶ ፡ ወድቆ ፡ ይሆን? የመጣው ፡ ይምጣ ፡ እንጂ ፡ ሄጄ ፡ ማወቅ ፡ አለብኝ!» አለና ፡ አሰበ ።

ወዲያው ፡ በአንድ ፡ ሳምንት ፡ ውስጥ ፡ ሙሉ ፡ የዘመቻ ፡ ትጥቁን ፡ ታጥቆና ፡ በፈረስ ፡ ሆኖ ፡ ዑማን ፡ ደረሰ ። እዚያም ፡ እንደደረሰ ፡ መስኮቶቹ ፡ በጢስ ፡ ጠቁረው ፤ ግራውም ፡ ተቀዳድዶ ፡ የወፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ወደሆነ ፡ ቆሻሻ ፡ ጐጆ ፡ አመራ ። ከጐጆው ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ጥራጊና ፡ ቆሻሻ ፡ ተከምሯል ። ከመስኮቶቹ ፡ በአንዱ ፡ ዳር ፡ ዳሩ ፡ ቀለማቸው ፡ በተበላሸ ፡ ሉሎች ፡ ያጌጠ ፡ ሻሽ ፡ ያሰረች ፡ አይሁዳዊት ፡ ራስ ፡ ብቅ ፡ አለ ።

ታራስ ፡ ከፈረሱ ፡ ወረደና ፡ የልጓሙን ፡ ጠፍር ፡ ከበሩ ፡ በተሰካ ፡ ቆልማማ ፡ ብረት ፡ ላይ ፡ እያሠረ ፤ «ባልሽ ፡ አለ?» አለና ፡ ጠየቀ ።

«እቤት ፡ ነው ፡» አለችና ፡ አይሁዲ ፡ በፍጥነት ፡ ለፈረሱ ፡ በቆና ፡ ስንዴ ፤ ለመኮንኑም ፡ አንድ ፡ ዋንጫ ፡ ጠላ ፡ ይዛ ፡ ቀረበች ።

«ታዲያስ ፤ አይሁድሽ ፡ የት ፡ ነው?» አላት ፡ ታራስ ።

«በወዲያኛው ፡ ክፍል ፡ ጸሎት ፡ ያደርሳል ፡» አለችና ፡ ቡልባ ፡ ጠላውን ፡ ሲጠጣ ፤ አይሁዲ ፡ ሰላምታ ፡ በማቅረብና ፡ መልካም ፡ ጤና ፡ በመመኘት ፡ በትህትና ፡ ትሽቆጠቆጥ ፡ ጀመር ።

«እዚህ ፡ ቆይና ፡ ለፈረሴ ፡ እህልና ፡ ውሃ ፡ ስጭው ። እኔ ፡ ከባልሽ ፡ ጋር ፡ ጉዳይ ፡ ስላለኝ ፡ ገብቼ ፡ ለብቻው ፡ አነጋግረዋለሁ ፡» አለና ፡ ታራስ ፡ ገባ ።

አይሁዱ ፤ ያንኬል ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይደለም ። በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ በወለድ ፡ አግድ ፡ አበዳሪና ፡ ባለ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ ሆኖ ፡ ተደለድሎ ፤ ቀስ ፡ በቀስ ፡ የአካባቢውን ፡ መኳንንትና ፡ ሎሌዎቻቸውን ፡ በእጁ ፡ አግብቶ ፡ ገንዘባቸውን ፡ ይመጠምጣል ። በአጭር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አይሁዳዊ ፡ ተግባሩ ፡ በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ ሥር ፡ ሰድዷል ። በዚያ ፡ ቀበሌ ፡ በሶስት ፡ ማይል ፡ ዙሪያ ፡ ቢፈለግ ፡ አንድም ፡ ቅጥ ፡ ያለው ፡ ጐጆ ፡ አይገኝም ። ቤቱ ፡ ሁሉ ፡ አርጅቶ ፡ በመፍረስ ፡ ላይ ፡ ነው ። ሁሉም ፡ ነገር ፡ በመጠጥ ፡ እየባከነ ፤ ከድህነትና ፡ ከቡትቶ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልተረፈም ። በጠቅላላው ፡ ቀበሌው ፡ የዘመቻ ፡ ወይም ፡ የበሽታ ፡ ወረራ ፡ ያጠቃው ፡ ይመስላል ። ያንኬል ፡ በዚያ ፡ ሥፍራ ፡ ተጨማሪ ፡ አሥር ፡ ዓመታት ፡ ቢቆይ ፡ ምናልባት ፡ መላውን ፡ የመስፍኑን ፡ ግዛት ፡ እንደዚያ ፡ ባራቆተው ፡ ነበር ።

ታራስ ፡ ከክፍሉ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ። አይሁዱ ፡ ራሱን ፡ በአደፈ ፡ ጨርቅ ፡ ተከናንቦ ፡ ይፀልያል ። በሃይማኖቱ ፡ መሠረት ፡ ሲፀልይ ፡ ምራቁን ፡ መትፋት ፡ ስላለበት ፡ ለመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ለመትፋት ፡ ዘወር ፡ ሲል ፡ ከኋላው ፡ የቆመውን ፡ ቡልባን ፡ አየ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባን ፡ ለሚይዝ ፡ ሰው ፡ የተዳረገው ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ በዓይኑ ፡ ላይ ፡ ብልጭ ፡ አለበት ። ግን ፡ ለሃብት ፡ በመጓጓቱ ፡ ሃፍረት ፡ ተሰማውና ፡ በአይሁድ ፡ ነፍስ ፡ ውስጥ ፡ ዘወትር ፡ እንደ ፡ ትል ፡ የሚርመሰመሰውን ፡ የወርቅ ፡ ፍላጐት ፡ ከሃሳቡ ፡ ለማጥፋት ፡ አጥብቆ ፡ ሞከረ ።

አይሁዱ ፡ ወዲያው ፡ እጅ ፡ እየነሳ ፤ አብረው ፡ እንዳይታዩም ፡ በጥንቃቄ ፡ በሩን ፡ ሲቆልፍ ፡ ታራስ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ «ያንኬል! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ሕይወትህን ፡ አድኛታለሁ ። እኔ ፡ ባላድንህ ፡ ዛፖሮዥያኖች ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ቆራርጠው ፡ ይጥሉህ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ያንተ ፡ ተራ ፡ ነው ። አንድ ፡ የምትረዳኝ ፡ ነገር ፡ አለ ።»



«የምን ፡ እርዳታ? የምችለው ፡ ነገር ፡ ከሆነ ፡ ለምን ፡ አልረዳዎትም?»

«በንግግር ፡ ጊዜ ፡ አታጥፋ ። ቶሎ ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ውሰደኝ ።»

ያንኬል ፡ በመደነቅ ፡ ቅንድቦቹን ፡ ሸብሽቦ ፤ «ወደ ፡ ዋርሶ? እንዴት ፡ ወደ ፡ ዋርሶ?» አለ ።

«በወሬ ፡ ጊዜ ፡ አታጥፋ ፡ ነው ፡ የምልህ ። ወደ ፡ ዋርሶ ፡ ውሰደኝ ። የመጣው ፡ ይምጣ ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ላየውና ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ ላናግረው ፡ እፈልጋለሁ ።»

«ለማን ፡ ነው ፡ አንዱ ፡ ቃል?»

«ለእሱ ፤ ለኦስታፕ ፤ ለልጄ!»

«እንዴት? ጌታዬ ፡ አያውቁም ፡ እንዴ ፡...»

«ሁሉንም ፡ አውቃለሁ ። እኔን ፡ ይዞ ፡ ለሚያቀርብ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ዳርገዋል ። የነፍሴን ፡ ዋጋ ፡ ያውቁታል ፤ እኒህ ፡ አህዮች! እኔ ፡ ለአንተ ፡ አምስት ፡ ሺ ፡ እሰጥሃለሁ ። አሁን ፡ ሁለቱ ፡ ሺ ፡ ይኸውልህ ፤ የቀረውን ፡ ስመለስ ፡» አለና ፡ ቡልባ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ከቆዳ ፡ ከረጢት ፡ ዘረገፈለት ።

አይሁዱ ፡ ወዲያው ፡ ፎጣ ፡ አመጣና ፡ ገንዘቡን ፡ ሸፈነው ። ወዲያውም ፡ አንድ ፡ ዱካት ፡ አንስቶ ፡ በጣቱም ፡ በጥርሱም ፡ እየመረመረ ፡ ያደንቅ ፡ ጀመር ።

«አቤት ፡ እንዴት ፡ የሚያምሩ ፡ ሳንቲሞች! አቤት ፡ የወርቁ ፡ ማማር! ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ወርቅ ፡ የዘረፉት ፡ ሰው ፡ ይብላኝለት ! መቸም ፡ ይህን ፡ መሳይ ፡ የሚያምር ፡ ዱካት ፡ ተዘርፎ ፡ ባህር ፡ ገብቶ ፡ ራሱን ፡ ይገድላል ፡ እንጂ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ እንኳን ፡ በሕይወት ፡ እንዳልቆየ ፡ እርግጠኛ ፡ ነኝ ።»

«አንተንም ፡ ሳልጠይቅ ፡ እኔው ፡ ብቻዬን ፡ ወደ ፡ ዋርሶ ፡ በሄድሁ ፡ ነበር ። ግን ፡ መደበቅና ፡ ማታለል ፡ ስለማይሆንልኝ ፡ እነዚያ ፡ የተረገሙ ፡ ፖሊሾች ፡ ያውቁኝና ፡ ሊይዙኝ ፡

ይችላሉ ። እናንት ፡ አይሁዶች ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ በተለይ ፡ የተፈጠራችሁ ፡ ናችሁ ። ዘዴውን ፡ ሁሉ ፡ ታውቃላችሁ ። ሰይጣንን ፡ ራሱን ፡ ቢሆንም ፡ እንኳን ፡ ማታለል ፡ አያቅታችሁም ። ስለዚህ ፡ ነው ፡ ወዳንተ ፡ የመጣሁ ። ወዲህም ፡ ደግሞ ፡ በዋርሶ ፡ ብቻዬን ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ ልሠራ ፡ አልችልም ። በል ፡ አሁን ፡ ጋሪህን ፡ ጫንና ፡ እዚያ ፡ አድርሰኝ!»

«ለመሆኑ ፡ ጌታዬ ፡ እንደሚያስቡት ፡ እንዲያው ፡ ተነሰቼ ፡ ባዝራዬን ፡ ጭ'፤ ሂጅ ፡ ግራጭ ! በማለት ፡ ብቻ ፡ የምንደርስ ፡ ይመስለዎታል? ጌታዬን ፡ ሳልሸሽግ ፡ እንዲህ ፡ እንዳሉ ፡ በግልጽ ፡ የምወስደዎት ፡ ይመስለዎታል?»

«በላ ፡ ሸሽገኝ ። እንደፈለግህ ፡ አድርገህ ፡ ሸሽገኝ! እንዲያውም ፡ ምናልባት ፡ በባዶ ፡ በርሚል ፡ ብትከትተኝ ፡ ይሻላል ።»

«ውይ! ውይ! ለመሆኑ ፡ ጌታዬ ፡ በበርሚል ፡ ውስጥ ፡ ለመደበቅ ፡ የሚችሉ ፡ ይመስለዎታል? ለሚያይ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በበርሚሉ ፡ ውስጥ ፡ ቮድካ ፡ ያለ ፡ እንደሚመስል ፡ ጌታዬ ፡ አያውቁምን?»

«ታዲያ ፡ ይምሰላቸዋ ።»

«እንዴት! ቮድካ ፡ ይምሰላቸው ?» አለና ፡ አይሁዱ ፡ ግራ ፡ ቀኝ ፡ ጆሮ ፡ ግንዱ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጸጉሩን ፡ በሁለት ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አነሳው ።

«ምነው ፤ ምን ፡ አስደነገጠህ?» አለው ፡ ቡልባ ።

«ቮድካን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲጠጣው ፡ መሆኑን ፡ ጌታዬ ፡ እንዴት ፡ አያውቁም? እዚያ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ መጠጥ ፡ ይወዳሉ ። ያየ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በርሚሉን ፡ ተከትሎ ፡ ሽንቁሮ ፡ ይሞክርና ፡ ወዲያው ፡ ቮድካ ፡ እንደማይወጣው ፡ ይገነዘባል ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ 'አይሁድ ፡ ባዶ ፡ በርሚል ፡ ይዞ ፡ አይሄድም ። እዚህ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የተሰወረ ፡ ተንኮል ፡ አይጠፋም! አይሁዱን ፡ ያዙት! አይሁዱን ፡ እሠሩት! ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ተረከቡት! አይሁዱን ፡ ወዲያ ፡



ወህኒ ፡ ቤት ፡ ውሰዱት!' ይባላል ። ማናቸውም ፡ ዓይነት ፡ ወንጀል ፡ ቢሠራ ፡ የሚወነጀለው ፡ አይሁዱ ፡ ነው ። አይሁድን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ነው ፡ የሚገምተው ። አይሁድ ፡ ከሆነ ፡ የሰው ፡ ፍጡር ፡ እንኳን ፡ አይመስላቸውም ።»

«በል ፡ እንግዲያው ፡ አሣ ፡ በተጫነ ፡ ጋሪ ፡ ውስጥ ፡ ደብቀኝ ።»

«አይቻልም ፡ ጌታዬ ። በመላው ፡ የፖላንድ ፡ ምድር ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ውሻ ፡ ተርቧል ። አሣውን ፡ ሁሉ ፡ ይሰርቁና ፡ እርስዎን ፡ ያገኙዎታል ።»

«እንግዲህ ፡ ከፈለግህ ፤ በሰይጣን ፡ ጀርባ ፡ ላይ ፡ ቢሆንም ፡ አስቀምጠኝ ። ብቻ ፡ እዚያ ፡ ልድረስ!»

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ አይሁዱ ፡ እጅጌውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየሰበሰበ ፡ ክንዶቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ወደ ፡ ታራስ ፡ ቀረበና ፡ «ይስሙኝ! ይስሙኝ ፡ ጌታዬ! ዘዴው ፡ ይኸውልዎት ። የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሕንፃና ፡ የጦር ፡ ምሽግ ፡ አሁን ፡ በየሥፍራው ፡ በመሠራት ፡ ላይ ፡ ነው ። የፈረንሳይ ፡ መሃንዲሶች ፡ ስለመጡ ፡ በየመንገዱ ፡ ብዙ ፡ ድንጋይና ፡ ሸክላ ፡ ይጓዛል ። ጌታዬ ፡ በጋሪው ፡ ላይ ፡ ይጋደሙና ፡ በላይዎ ፡ ላይ ፡ ሸክላ ፡ እደረድርብዎታለሁ ። ጌታዬ ፡ ጤናማና ፡ ጠንካራ ፡ ይመስላሉ ። ስለዚህ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ትንሽ ፡ ከበድ ፡ ቢል ፡ ለጉዳት ፡ አይሰጠዎም ። ደግሞ ፡ ከሥር ፡ በኩል ፡ ጌታዬን ፡ ለመመገብ ፡ ቀዳዳ ፡ አበጃለሁ ፡» አለ ።

ታራስም ፤ «ብቻ ፡ እዚያ ፡ አድርሰኝ ፡ እንጂ ፤ የፈለግኸውን ፡ አድርግ!» አለና ፡ ተስማማ ።

አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ቆይቶ ፤ ሸክላ ፡ የተጫነ ፡ አንድ ፡ ጋሪ ፡ በሁለት ፡ አጋሰሶች ፡ እየተሳበ ፡ ከዑማን ፡ ወጣ ። ከአጋሰሶቹ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ረጅሙ ፡ ያንኬል ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ያለ ፡ የቬርስታ ፡ ምልክት ፡ መስሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ጌኛው ፡ ፈረስ ፡ ሲያንገጨግጨው ፡ ከአይሁድ ፡ ቆቡ ፡ ዘልቆ ፡ በጆሮ ፡ ግንዱ ፡ የወረደው ፡ ጸጉሩ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይወዛወዛል ።

## ምዕራፍ ፡ አሥራ ፡ አንድ ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አሁኑ ፡ የነጋዴዎች ፡ ሥቃይ ፡ የሆኑት ፡ የቀረጥ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖችና ፡ ፈታሾች ፡ ስላልነበሩ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የፈለገውን ፡ ነገር ፡ ጭኖ ፡ ያለ ፡ ችግር ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ሰው ፡ መንገደኛውን ፡ አቁሞ ፡ የፈተሸ ፡ እንደሆነም ፤ ለገዛ ፡ ጥቅሙ ፡ ሲል ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ይኸውም ፡ በተለይ ፡ የተጫነው ፡ ዕቃ ፡ ዓይኑን ፡ የማረከው ፡ እንደሆነና ፡ ሰውየው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የሥልጣን ፡ መብት ፡ የኖረው ፡ እንደሆን ፡ ነው ። ሽክላዎቹ ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ስለማያጓጉ ፡ ያለችግር ፡ የከተማውን ፡ በር ፡ አልፈው ፡ ገቡ ። ቡልባ ፡ ከተጋደመበት ፡ ጠባብ ፡ የሸክላ ፡ ወጥመድ ፡ ሆኖ ፡ የመንገዱ ፡ ጫጫታና ፡ የጋሪ ፡ ነጂዎች ፡ ጩኸት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ የሚሰማው ። ያንኬል ፡ አቧራ ፡ ባለበሰው ፡ አጭር ፡ አጋሰሱ ፤ ላይና ፡ ታች ፡ እየነጠረ ፡ ዱካውን ፡ ለማደናገር ፡ ከተዘዋወረ ፡ በኋላ ፤ በዋርሶ ፡ ያሉት ፡ አይሁዶች ፡ በሞላ ፡ ስለሚኖሩበት ፤ የቆሻሻ ፡ ወይም ፡ የአይሁድ ፡ መንገድ ፡ ወደሚባለው ፡ ጉራንጉርና ፡ ጨለማ ፡ ሠፈር ፡ እጥፍ ፡ አለ ። ይህ ፡ ሠፈር ፡ የተመነቃቀረ ፡ ቆሻሻ ፡ ጓሮ ፡ የሚመስል ፡ ነበር ። የፀሐይ ፡ ብርሃንም ፡ አርፎበት ፡ የሚያውቅ ፡ አይመስልም ። እድሜ ፡ ያጠቆራቸው ፡ የእንጨት ፡ ቤቶችም ፡ የባሰ ፡ አጨልመውታል ። አልፎ ፡ አልፎ ፡ በቤቶቹ ፡ መካከል ፡ ከቀይ ፡ ሸክላ ፡ የተሠራ ፡ የግንብ ፡ አጥር ፡ ይታያል ። ግን ፡ እሱም ፡ ከብዙ ፡ ሥፍራ ፡ መጥቆር ፡ ጀምሯል ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ በፀሐይ ፡ ብርሃን ፡ የሚያንፀባርቅ ፡ ኖራ ፡ የተቀባ ፡ ግንብ ፡ የሚታይበት ፡ ሥፍራ ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ነው ። በዚህ ፡ ሠፈር ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለዓይን ፡ ያስጠላል ። መንደርተኛው ፡ ሁሉ ፡ የማያስፈልገውን ፡ ማናቸውንም ፡ አሮጌና ፡ ቆሻሻ ፡ ነገር ፤ ለአላፊ ፡ አግዳሚው ፡ ስሜት ፡ ሳያስብ ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ አውጥቶ ፡ ይጥለዋል ። በፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ የሚ



ያልፍ ፡ ሰው ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ከአንዱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ የተጋደሙትን ፡ የልብስ ፡ ማሰጫ ፡ አጠናዎች ፡ በእጁ ፡ ሊነካቸው ፡ ይችላል ። ከአጠናዎቹም ፡ ላይ ፡ የአይሁዶች ፡ የእግር ፡ ሹራቦች ፡ ቁምጣ ፡ ሱሪዎች ፡ ወይም ፡ የደረቀች ፡ ዳክየ ፡ ተንጠልጥለው ፡ ይታያሉ ። አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ቆንጆ ፡ ቢጤ ፡ የሆነች ፡ የአይሁድ ፡ ልጃገረድ ፡ ፊት ፡ ከነጨሌ ፡ጌጧ ፡ ከአንድ ፡ አሮጌ ፡ መስኮት ፡ ብቅ ፡ ትላለች ። ጸጉራቸው ፡ ቁጥርጥር ፡ ያለና ፡ የተራቆቱ ፡ የአይሁድ ፡ ኩታሮችም ፡ እየተንጫጩ ፡ በጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ይንከባለላሉ ። ጠቃጠቆ ፡ ያዥጐረጐረው ፡ ቀይ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ አንድ ፡ አይሁድ ፡ በመስኮት ፡ ብቅ ፡ አለና ፡ በቋንቋው ፡ ያንኬልን ፡ ሲያነጋግረው ፡ ያንኬልም ፡ ወደዚያው ፡ ሰውየ ፡ ግቢ ፡ ጋሪውን ፡ ነድቶ ፡ ገባ ። በመንገዱ ፡ የሚያልፍ ፡ አንድ ፡ ሌላ ፡ አይሁድ ፡ ደግሞ ፡ ቆም ፡ አለና ፡ ከእነሱ ፡ ጋር ፡ ጣልቃ ፡ ገብቶ ፡ ያወራ ፡ ጀመር ። በመጨረሻ ፡ ቡልባ ፡ ከሸክላው ፡ ስር ፡ ተንኳትቶ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሶስቱም ፡ አይሁዶች ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ወሬ ፡ ይዘው ፡ ተመለከተ ።

ያንኬል ፡ ወደሱ ፡ ዞረና ፡ ሁሉም ፡ ነገር ፡ ደህና ፡ መሆኑን ፡ እስታጥም ፡ በከተማው ፡ ወህኒ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እንዳለና ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ዘበኞቹን ፡ ለመደለል ፡ አስቸጋሪ ፡ ቢሆን ፡ ሊያገናኘው ፡ እንደሚሞክር ፡ ነገረው ።

ቡልባም ፡ ከሶስቱ ፡ አይሁዶች ፡ ጋር ፡ ወዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ገባ ።

አይሁዶቹ ፡ እንደገና ፡ በቋንቋቸው ፡ ንግግር ፡ ጀመሩ ። ታራስም ፡ ቋንቋው ፡ ስለማይገባው ፡ እነሱን ፡ በተራ ፡ እያስተዋለ ፡ በፊቱ ፡ ላይ ፡ የጋለ ፡ የተስፋ ፡ ስሜት ፡ ይታይ ፡ ጀመር ። የሽማግሌ ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ ወጣት ፡ ልብ ፡ በፍጥነት ፡ ይመታ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡ የደስታ ፡ ስሜት ፡ ባለው ፡ አነጋገር ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«ስሙ ፡ አይሁዶች ፡ ሆይ! የውቅያኖስን ፡ መደብ ፡ መቆፈር ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ የሚያቅታችሁ ፡ አይደላችሁም ። አንድ ፡ አይሁድ ፡ ከፈለገ ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ሊሰርቅ ፡ ይችላል ፤ እየተባለ ፡ ሲተረት ፡ ሲነገር ፡ ኖሯል ። ልጄን ፡ አስታጥን ፡ ነፃ ፡ አውጡልኝ ! ከሰይጣኖች ፡ እንዲያመልጥ ፡ እርዱት ። ይህን ፡ ለሚያደርግልኝ ፡ ሰው ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ልሰጠው ፡ ቃል ፡ ገብቼ ፡ ነበር ። አሁን ፡ ግን ፡ እንደገና ፡ አሥራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ዱካት ፡ ለመጨመር ፡ ዝግጁ ፡ ነኝ ። ብዙ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ጸዋዎቼን ፤ የቀበርኩትን ፡ ወርቅ ፡ ሁሉ ፤ ቤቴንና ፡ የመጨረሻ ፡ ልብሴ ፡ እንኳን ፡ ሳይቀር ፡ እሰጣችኋለሁ ። ከዚህም ፡ በላይ ፡ እድሜዬን ፡ በሙሉ ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ ከማገኘው ፡ ሃብት ፡ ግማሹን ፡ ልሰጣችሁ ፡ ቃል ፡ እገባለሁ ።»

ያንኬል ፡ ተስፋ ፡ የመቁረጥ ፡ ትካዜ ፡ እየታየበት ፤ «አዬ ፡ የሚቻል ፡ አይደለም!» አለ ።

ሁለተኛውም ፡ አይሁድ ፤ «የለም ፡ የሚቻል ፡ አይደለም!» አለና ፡ ሶስቱም ፡ አይሁዶች ፡ ተያዩ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ሶስተኛው ፡ አይሁድ ፤ «ብንሞክርስ? እግዚአብሔር ፡ ይረዳን ፡ ይሆናል ፡» አለ ።

ከዚያ ፡ ሶስቱም ፡ በጀርመንኛ ፡ ይነጋገሩ ፡ ጀመር ። ቡልባ ፡ ምንም ፡ ቢያዳምጥ ፡ ንግግራቸው ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። የሚሰማው ፡ ደጋግመው ፡ የሚያነሱት ፡ ማርዶሃይ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

ወዲያው ፡ ያንኬል ፡ እንዲህ ፡ አለው ፤ «ይስሙ ፡ ጌታዬ! በዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደር ፡ የሌለው ፡ አንድ ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡ አለና ፡ እሱን ፡ ማማከር ፡ አለብን! ልክ ፡ እንደ ፡ ሶሎሞን ፡ ጠቢብ ፡ ነው ። እሱ ፡ ሊሠራው ፡ ያልቻለውን ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ሊሠራው ፡ አይችልም ፡ ስለዚህ ፡ እዚህ ፡ ተቀምጠው ፡ ይጠብቁን ፤ የቤቱ ፡ ቁልፍ ፡ ይኸውና ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ እንዳያስገቡ ።»



አይሁዶቹ ፡ ወደ ፡ መንገዱ ፡ ወጡ ።

ታራስ ፡ በሩን ፡ ቆለፈና ፡ በመስኮቱ ፡ ቆሻሻውን ፡ የአይሁዶች ፡ መንገድ ፡ ያስተውል ፡ ጀመር ። ሶስቱ ፡ አይሁዶች ፡ መንገዱ ፡ መሃል ፡ ቆመው ፡ በችኮላ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ሌላ ፡ አራተኛ ፡ ቀጥሎም ፡ አምስተኛ ፡ አይሁዶች ፡ መጥተው ፡ ከነሱ ፡ ተደባለቁ ። «ማርዶሃይ ፡» የሚለው ፡ ቃል ፡ አሁንም ፡ ሲደጋገም ፡ ታራስ ፡ ሰማ ። አይሁዶቹ ፡ የመንገዱን ፡ አንዱን ፡ አቅጣጫ ፡ እየተገላመጡ ፡ ሲያስተውሉ ፡ ከቆዩ ፡ በኋላ ፡ ከዚያው ፡ አቅጣጫ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቅ ፡ አለ ። አይሁዶቹም ፡ በአንድ ፡ ቃል ፡ «አሃ ፡ ማርዶሃይ! ማርዶሃይ!» እያሉ ፡ ጮኹ ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ከያንኬል ፡ ትንሽ ፡ አጠር ፡ ያለ ፡ ግን ፡ የባሰ ፡ የተጨማደደና ፡ የላይ ፡ ከንፈሩ ፡ አለመጠን ፡ ትልቅ ፡ የሆነ ፡ አይሁድ ፡ መጥቶ ፡ በመኃኀት ፡ ከሚጠብቁት ፡ ከአምስቱ ፡ አይሁዶች ፡ ጋር ፡ ተደባለቀ ። እነሱም ፡ በጥድፍያ ፡ ጉዳያቸውን ፡ ሲገልጹለት ፡ ማርዶሃይ ፡ ገልመጥ ፡ እያለ ፡ ታራስ ፡ የቆመበትን ፡ ትንሽ ፡ መስኮት ፡ ይመለከት ፡ ስለነበር ፡ ጉዳዩ ፡ ስለራሱ ፡ መሆኑን ፡ ታራስ ፡ ተገነዘበው ። ማርዶሃይ ፡ እጆቹን ፡ እያወዛወዘ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ንግግራቸውን ፡ ሲያቋርጥ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ሲያዳምጥ ፡ አልፎ ፡ አልፎም ፡ ወደጐን ፡ ምራቁን ፡ እየተፋ ፡ እንደቆመ ፡ የአይሁድ ፡ ቀሚሱን ፡ ገለበና ፡ ቆሻሻ ፡ ሱሪው ፡ እየታየ ፡ ከኪሱ ፡ ጌጣጌጥ ፡ ነገር ፡ አወጣ ። በመጨረሻ ፡ አይሁዶቹ ፡ የቆመው ፡ ጠባቂ ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ ምልክት ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጫጫታ ፡ ስለጀመሩ ፡ ታራስ ፡ ስጋት ፡ አደረበት ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አይሁዶች ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ እንጂ ፡ በሌላ ፡ ሥፍራ ፡ እንደማይነጋገሩ ፡ ቋንቋአቸውንም ፡ ሰይጣን ፡ ራሱ ፡ እንኳን ፡ ሊረዳው ፡ እንደማይችል ፡ ትዝ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ታራስ ፡ ልቡ ፡ ረጋ ።

አንድ ፡ ሁለት ፡ ደቂቃ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ አይሁዶቹ ፡ ወደ ፡ ክፍሉ ፡ ገቡና ፡ ማርዶሃይ ፡ ወደ ፡ ቡልባ ፡ ቀርቦ ፡ ትከ

ሻውን ፡ መታ ፡ መታ ፡ እያደረገ ፡ «እኛና ፡ እግዚአብሔር ፡ አብረን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ከተነሳን ፡ ሁልጊዜ ፡ ይሳካልናል ፡» አለው ።

ታራስ ፡ ይህን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ወደር ፡ የሌለውን ፡ የሰሎሞን ፡ ምትክ ፡ ተመለከተና ፡ አዲስ ፡ ተስፋ ፡ አደረበት ። በእውነትም ፡ የዚህ ፡ አይሁድ ፡ መልክ ፡ ሲታይ ፡ የአሰበው ፡ ነገር ፡ እንደሚሳካለት ፡ እምነትና ፡ ተስፋ ፡ የሚሰጥ ፡ ነበር ። የላይ ፡ ከንፈሩ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ የጢሙ ፡ ጠጉሮችም ፡ በቁጥር ፡ ከአሥራ ፡ ሁለት ፡ የማይበልጡ ፡ ሲሆኑ ፡ እነሱም ፡ የበቀሉት ፡ በግራ ፡ ገጹ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ፊቱ ፡ በተንኮል ፡ ተግባሩ ፡ የአገኛቸው ፡ በትሮች ፡ ምልክት ፡ በብዛት ፡ ይታይበታል ። ከብዛታቸውም ፡ የተነሳ ፡ እንደተፈጥሮ ፡ ምልክት ፡ ሳይቆጥራቸው ፡ አይቀርም ።

ማርዶሃይ ፡ ጠቢብነቱን ፡ ከሚያደንቁለት ፡ ጓደኞቹ ፡ ጋር ፡ ወጥቶ ፡ ሄደና ፡ ቡልባ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ። ውጤቱ ፡ ባልታወቀ ፡ ሁናቴ ፡ ላይ ፡ በመሆኑ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ደርሶበት ፡ የማያውቅ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የመጓጓት ፡ ስሜት ፡ አደረበት ። ልቡም ፡ በመጓጓት ፡ ትኩሳት ፡ ይነድድ ፡ ጀመር ። አሁን ፡ እንደ ፡ ወርካ ፡ ጠንካራና ፡ ልበ ፡ ጽኑው ፡ የቀድሞው ፡ ቡልባ ፡ አልሆነም ። እርብትብትና ፡ ልበ ፡ ደካማ ፡ ሆነ ። ትንሽ ፡ ድምጽ ፡ ሲሰማ ፡ ወይም ፡ በመንገዱ ፡ ዳር ፡ አንድ ፡ አይሁድ ፡ ውልብ ፡ ሲል ፡ ይደነግጥ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ሁናቴ ፡ ሳይበላና ፡ ሳይጠጣ ፡ ዓይኖቹንም ፡ ከትንሽዋ ፡ መስኮት ፡ ሳይለይ ፡ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ ዋለ ። በመጨረሻ ፡ በአመሻሽ ፡ ላይ ፡ ማርዶሃይና ፡ ያንኬል ፡ ብቅ ፡ ሲሉ ፡ ቡልባ ፡ ልቡ ፡ መምታት ፡ ተሳነው ።

«ታዲያስ? ተሳካላችሁ?» አለና ፡ በመጓጓት ፡ ጠየቃቸው ።

ነገር ፡ ግን ፡ አይሁዶቹ ፡ መልስ ፡ ከመስጠታቸውም ፡ በፊት ፡ በማርዶሃይ ፡ ጆሮ ፡ ግንድ ፡ አጠገብ ፡ ተጠቅልሎ ፡



ይታይ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ ጸጉር ፡ አሁን ፡ አለመኖሩን ፡ ቡልባ ፡ ተመለከተ ። ማርዶሃይ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ እንዳሰበ ፡ ግልጽ ፡ ነው ፡ ግን ፡ ከመርበትበቱ ፡ የተነሳ ፡ አንድም ፡ ቃል ፡ ለቡልባ ፡ ሊገባው ፡ አልቻለም ። ያንኬል ፡ ራሱም ፡ ጉንፋን ፡ እንዳስጨነቀው ፡ ሰው ፡ አፉን ፡ በእጁ ፡ እያፈነ ፡ ይቅበጠበጥ ፡ ጀመር ።

በመጨረሻ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«አዬ ፡ የኔ ፡ ጌታ! የሚሆን ፡ አደለም! እግዚአብሔር ፡ ይመስክር ፡ በፍጹም ፡ አደለም! ሰዎቹ ፡ በጣም ፡ መጥፎ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ማርዶሃይ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሚችለው ፡ በላይ ፡ ጥሮ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ሃሳባችን ፡ እንዲከናወን ፡ አምላክ ፡ አልፈቀደም ። ሶስት ፡ ሺ ፡ ወታደሮች ፡ እዚህ ፡ ሰፍረዋል ፤ እስረኞቹም ፡ ነገ ፡ ሊገደሉ ፡ ነው ።»

ታራስ ፡ የአይሁዶቹን ፡ ዓይን ፡ ዓይናቸውን ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ተመለከተ ። ግን ፡ እንደቀድሞው ፡ በመጓጓት ፡ ወይም ፡ በቁጣ ፡ ስሜት ፡ አይደለም ።

ያንኬል ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፤ «ጌታዬ ፡ ሊያዩት ፡ ቢፈቅዱ ፡ ነገ ፡ በጠዋት ፡ ጀንበር ፡ ሳትወጣ ፡ መሆን ፡ አለበት ። ዘበኞቹ ፡ ተስማምተው ፡ ከአለቆቹ ፡ አንዱም ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቶናል ። ብቻ ፡ በወዲያኛው ፡ ዓለም ፡ ደስታ ፡ ያሳጣቸውና ፡ እንዴት ፡ ገብጋባ ፡ ፍጥረቶች ፡ ናቸው! ከኛ ፡ ከማናችንም ፡ እንኳን ፡ የባሱ ፡ ስስታሞች ፡ ናቸው! ለያንዳንዳቸው ፡ አምሳ ፡ ዱካት ፡ ሰጥቼ ፡ ለአለቅየው ፡ ደግሞ ፡...» ሲል ፡ ታራስ ፡ እንደቀድሞው ፡ ጽኑና ፡ ቆረጥ ፡ በሆነው ፡ አነጋገሩ ፤ «መልካም ፤ በሉ ፡ ውሰዱኝ!» አላቸው ።

ታራስ ፡ ከጀርመን ፡ አገር ፡ የመጣ ፡ መኮንን ፡ በመምሰል ፡ ሳይታወቅ ፡ እንዲያልፍ ፡ ያንኬል ፡ ባቀረበው ፡ አሳብ ፡ ተስማማ ። አርቆ ፡ አስተዋዩ ፡ አይሁድም ፡ ነገሩን ፡ አስቀድሞ ፡ አስቦበት ፡ ኖሮ ፡ አስፈላጊውን ፡ ልብስ ፡ አዘጋጅቷል ።

ጊዜው ፡ ጨልሞአል ። የቤቱ ፡ ባለቤት ፡ ጸጉረ ፡ ቀዩ ፡
አይሁድ ፡ አንድ ፡ ስስ ፡ ፍራሽ ፡ አመጣና ፡ በአንድ ፡ አግዳ
ሚ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ዳውጃ ፡ አልብሶ ፡ ለታራስ ፡ አነጠፈለት ።
ያንኬል ፡ እንደዚያው ፡ ባለ ፡ ፍራሽ ፡ ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተጋደ
መ ። ጸጉረ ፡ ቀዩ ፡ አይሁድ ፡ በአንድ ፡ ትንሽ ፡ መለኪያ ፡ አንድ ፡
ነገር ፡ ጠጣና ፡ ኮቱን ፡ አውልቆ ፡ ቁም ፡ ሳጥን ፡ በሚመስ
ል ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚስቱ ፡ ጋር ፡ ገባ ። በዚያ ፡ ቁም ፡ ሳ
ጥን ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ ሕፃናት ፡ የውሻ ፡ ቡችላ ፡ መስለው ፡
ወለሉ ፡ ላይ ፡ ተጋድመዋል ። ታራስ ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ አልተ
ኛም ፤ ሳይንቀሳቀስ ፡ ቁጭ ፡ ብሎ ፡ በጣቶቹ ፡ ጠረጴዛውን ፡
በመቆርቆር ፡ እየተከዘ ፡ የትንባሆ ፡ ማጤሻውን ፡ ከአፉ ፡
ሳይለይ ፡ ያጤስ ፡ ጀመር ። ያንኬል ፡ ጢሱ ፡ እየከነከነው ፡ በእ
ንቅልፍ ፡ ልቡ ፡ እያነጠሰ ፡ አፍንጫውን ፡ በብርድ ፡ ልብሱ ፡
ሸፈነ ። የጐህ ፡ ብርሃን ፡ በሰማዩ ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ፍንጥቅ ፡ ከማ
ለቱ ፡ ታራስ ፡ ያንኬልን ፡ በእግሩ ፡ ጐሸም ፡ አደረገውና ፤
«ተነሳ ፡ አይሁድ ፤ የጀርመን ፡ መኳንንት ፡ ልብስ ፡ ያልከ
ውን ፡ ስጠኝ!» አለው ።

በአንድ ፡ አፍታ ፡ ልብሱን ፡ ለበሰ ፤ ጢሙንና ፡ ቅንድ
ቡን ፡ በቀለም ፡ አጥቁሮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጠቆር ፡ ያለች ፡ ትን
ሽ ፡ ቆብ ፡ አደረገ ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ በደንብ ፡ የሚያውቁት ፡
ኮዛኮች ፡ እንኳን ፡ ሊለዩት ፡ ባልቻሉም ፡ ነበር ። እድሜው ፡
ከሠላሳ ፡ አምስት ፡ የማይበልጥ ፡ መሰለ ። የጤናማነት ፡ መልክ ፡
በጉንጮቹ ፡ ላይ ፡ ያበራ ፡ ጀመር ። በፊቱ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ የጦር ፡
ሜዳ ፡ ቁስሉ ፡ ጠባሳም ፡ የበለጠ ፡ ግርማ ፡ ሰጠው ። በወርቅ ፡
ያጌጠው ፡ ልብስ ፡ በእውቅ ፡ እንደተሰፋ ፡ ሁሉ ፡ ልክ ፡ ሆኖ ፡
ተስማማው ።

መንገዶቹ ፡ ገና ፡ ከእንቅልፍ ፡ አልነቁም ። ቅርጫት ፡
የታቀፈ ፡ ገበያተኛ ፡ ፍጥረት ፡ በከተማው ፡ ገና ፡ ብቅ ፡ አላለ
ም ። ቡልባና ፡ ያንኬል ፡ የትቀመጠ ፡ እርኩም ፡ ከሚመስል ፡
አንድ ፡ ቤት ፡ ደረሱ ። በዚህ ፡ ጥቁርና ፡ ትልቅ ፡ ቤት ፡ በአ



ንዱ ፡ ገጽ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ እርኩም ፡ አንገት ፡ መለስ ፡ ብሎ ፡
የወጣ ፡ የዘበኛ ፡ መቆሚያ ፡ ደርብ ፡ አለ ። ይህ ፡ ቤት ፡ ለብዙ ፡
ተግባር ፡ የሚያገለግል ፡ ነው ። በውስጡ ፡ የወታደር ፡ ሰፈር
ና ፡ የወህኒ ፡ ቤት ፡ ሲኖረው ፡ እንዲሁም ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይገ
ኝበታል ። እነቡልባ ፡ በሩን ፡ አልፈው ፡ ሲገቡ ፡ ሰፊ ፡ አዳ
ራሽ ፡ አገኙ ። በዚያም ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ ተኝቶ
አል ። ፊት ፡ ለፊታቸው ፡ አንድ ፡ አጭር ፡ በር ፡ አለ ። በበሩ
ም ፡ አጠገብ ፡ ሁለት ፡ ዘበኞች ፡ ተቀምጠው ፡ አንዱ ፡ የአን
ዱን ፡ እጅ ፡ በሁለት ፡ ጣት ፡ በመምታት ፡ አንድ ፡ ዓይነት ፡
ጨዋታ ፡ ይጫወታሉ ። ዘበኞቹ ፡ የእንግዶቹን ፡ መምጣት ፡
ከምንም ፡ ሳይቆጥሩት ፡ ችላ ፡ ብለው ፡ ሲጫወቱ ፡ ያንኬል ፤
«እኛ ፡ ነን ፤ ሰማችሁኝ ፡ ጌቶቼ? እኛ ፡ ነን ፡» ባለ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡
ዘወር ፡ አሉ ።

ከዚያ ፡ ከሁለቱ ፡ አንዱ ፡ አንድ ፡ እጁን ፡ ጓደኛው ፡ እን
ዲመታው ፡ እንደዘረጋለት ፡ በሌላው ፡ እጁ ፡ እያመለከተ ፤
«ግቡ!» አላቸው ።

ገብተውም ፡ በጠባብ ፡ መተላለፊያ ፡ ሄደው ፡ እንደ ፡
መጀመሪያው ፡ ካለ ፡ አዳራሽ ፡ ደረሱ ።

ወዲያው ፤ «ቁም ፡ ማነህ? ማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ እንዳ
ያልፍ ፡ ክልክል ፡ ነው!» የሚል ፡ የብዙ ፡ ወታደሮች ፡ ድምጽ ፡
ሰሙ ።

«እኛ ፡ ነን ፤ እኛ ፡ ነን ፡ የተከበራችሁ ፡ ጌቶቼ!» አለ ፡
ያንኬል ፡ ግን ፡ ማንም ፡ አላዳመጠውም ። እንደ ፡ እድል ፡
ሆኖ ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ በአለባበሱ ፡ አለቃ ፡ የሚመስል ፡ አንድ ፡
ወፍራም ፡ ሰውዬ ፡ ገባ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ያንኬል ፤ «ጌታዬ ፡ እኛ ፡ ነን! የሚያው
ቁን ፡ ነን ፡ እኚህ ፡ መኮንንም ፡ በድጋሚ ፡ ለእርስዎ ፡ ምስጋ
ና ፡ ያቀርባሉ ፡» አለ ።

አለቅየው ፡ «ተዋቸው ፡ ይለፉ ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ እን

ዳታስገቡ! ጕራዴያችሁን ፡ ሳትፈቱ ፡ እንደውሻ ፡ ተጋድማችሁ ፡ ጠብቁ ፡»አለ ።

ከዚያ ፡ ያንኬል ፤ «እኛ ፡ ነን ፡ …እኔ ፡ ነኝ ፡ …ወዳጆች ፡ ነን!» እያለ ፡ ላገኘው ፡ ሁሉ ፡ እየለፈለፈ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ በመጨረሻ ፡ ካለው ፡ በር ፡ ሲደርሱ ፤ «አሁን ፡ ልንገባ ፡ እንችላለን?» አለና ፡ አንዱን ፡ ዘበኛ ፡ ጠየቀው ።

«አዎ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ቤቱ ፡ ያሳልፏችሁ ፡ እንደሆን ፡ አላውቅም ፤ ያን ፡ ተለውጦ ፡ አሁን ፡ በሱ ፡ ስፍራ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ያለው ፡» ሲል ፡ አይሁዱ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፤ «ወይኔ ፡ ወይኔ! ይህ ፡ የሚያሰጋ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ ጌታዬ!» አለ ።

ታራስ ፡ ግን ፤ «በል ፡ ሂድ ፡ እለፍ!» አለውና ፡ ያንኬል ፡ በታዛዥነት ፡ ቀድሞ ፡ ተጓዘ ። በወህኒ ፡ ቤቱ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ባለሶስት ፡ ደረጃ ፡ ጢም ፡ ያለው ፡ ወታደር ፡ ቆሞአል ። የጢሙ ፡ የላይኛው ፡ ደረጃ ፡ ወደኋላ ፡ ተጠምዞአል ። ሁለተኛውም ፡ ወደፊት ፡ ሾሎ ፤ ሶስተኛው ፡ ደግሞ ፡ ወደታች ፡ ስለ ተንጠለጠለ ፡ ቁርጥ ፡ ድመት ፡ አስመስሎታል ።

አይሁዱ ፡ የተቻለውን ፡ ያህል ፡ ጀርባውን ፡ አጐበጠና ፡ እየተሽቆጠቆጠ ፡ ወደሱ ፡ ቀረበ ።

«ክቡር ፡ ሆይ! እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ!»

«እኔን ፡ ነው ፡ የምታነጋግረው ፡ አይሁድ?»

«አዎ ፡ እርስዎን ፡ ነው ፡ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ መኮንኔ!»

ባለሶስት ፡ ደረጃ ፡ ጢማሙ ፡ ሰውየም ፡ ዓይኖቹ ፡ በደስታ ፡ እያበሩ ፤ «ወይጉድ ፡ ታድያ ፡ እኔኮ ፡ አንድ ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ ነኝ!» አለው ።

አይሁዱ ፡ ራሱን ፡ ነቀነቀና ፡ እጆቹን ፡ ዘርግቶ ፡ «እረግ ፡ በፈጣሪ ፡ …ወየወዱ ፡ ራሳቸው ፡ መስለውኝ ፡ ነበር! ይገርማል ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ግርማ ፡ አላቸው ! ፈጣሪዬ ፡ ይመስክር ፡ ልክ ፡ ኮሎኔል ፡ ይመስላሉ! እንደኔ ፡ ቢሆን ፡ ጌታዬ ፡ እርስዎን ፡ እንደዝንብ ፡ በሚበር ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ አስቀምጦ ፡ የአንድ ፡ ክፍል ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ማድረግ ፡ ነበር!» አለ ።



በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሩ ፡ የታችኛውን ፡ ደረጃ ፡ ጢሙን ፡ እየዳሰሰ ፡ ዓይኖቹ ፡ የደስታ ፡ ብርሃን ፡ ተጐናጸፉ ።

አይሁዱም ፡ ውዳሴውን ፡ ቀጠለ ።

«ወታደሮች ፡ እንዴት ፡ ግሩም ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። ልብሳቸው ፡ እንደ ፡ ጸሐይ ፡ ያንጸባርቃል ፤ በየትም ፡ ስፍራ ፡ ያሉ ፡ ቆነጃጅት ፡ ሴቶች ፡ ወታደር ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አቤት ፡ የሚሆኑት ፡ መሆን!»

ወታደሩ ፡ የላይኛውን ፡ ደረጃ ፡ ጢሙን ፡ ጠመዘዘና ፡ እንደሚያስካካ ፡ ፈረስ ፡ በጥርሶቹ ፡ መሃል ፡ አፏጨ ።

አይሁዱም ፡ ንግግሩን ፡ ቀጠለና ፤ «አንድ ፡ እርዳታ ፡ እንዲያደርጉልን ፡ ጌታዬን ፡ እለምናለሁ ። እነሆ ፡ እኒህ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የመጡ ፡ ልዑል ፤ ኮዛኮቹን ፡ ለማየት ፡ ይፈልጋሉ ። ኮዛኮች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደሆኑ ፡ በሕይወታቸው ፡ አይተው ፡ አያውቁም ፡» አለ ።

የውጭ ፡ መንግሥታት ፡ ልዑላንና ፡ መኳንንት ፡ ወደ ፡ ፖላንድ ፡ መምጣታቸው ፡ ያልተለመደ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ። እስያ ፡ ቀመስ ፡ የሆነውን ፡ ይህን ፡ የአውሮፓ ፡ ዳርቻ ፡ ለማየት ፡ ሲሉ ፡ ብቻ ፡ ዘወትር ፡ ይመጣሉ ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሞስኮቪንና ፡ ኡክሬይንን ፡ እንደ ፡ እስያ ፡ ክፍል ፡ ነበር ፡ የሚቆጥሩት ። ስለዚህ ፡ ይህን ፡ በመገንዘብ ፡ ወታደሩ ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሳና ፡ በበኩሉ ፡ ትንሽ ፡ ቃላት ፡ ለመናገር ፡ አሰበ ።

«ክቡርነትዎ ፡ እነሱን ፡ ለማየት ፡ ለምን ፡ እንደፈለጉ ፡ በእውነቱ ፡ አላውቅም ። እነሱ ፡ ውሾች ፡ እንጂ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉም ። ሃይማኖታቸውም ፡ የረከሰ ፡ ነው ፡» አለ ።

በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ቡልባ ፤ «ሃሰት ፡ ነው ፡ አንተ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ! አንተ ፡ ራስህ ፡ ነህ ፡ ውሻ ፤ ሃይማኖታችንን ፡ የረከሰ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ እንዴት ፡ ደፈርህ ? የእናንተው ፡ የከሃዲዎች ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡ እርኩስ ፡ » አለ ።

ወታደሩም ፤ «አሃ! ማን ፡ እንደሆንክ ፡ አወቅሁህ ፡ ወዳጄ ፤ አንተም ፡ ራስህ ፡ እዚህ ፡ ከምጠብቃቸው ፡ አንዱ ፡ ነህ ፡

ለካ ! ቆይ ፡ አሁን ፡ ወታደሮቻችንን ፡ ስጠራ ፡ ታያለህ!»
አለ ።

ታራስ ፡ ጥፋቱን ፡ ተገነዘበ ፡ ግን ፡ ከሆነ ፡ ወዲህ ፡ ምንም ፡
ሊያደርግ ፡ አልቻለም ። ሆኖም ፡ ያንኬል ፡ ቶሎ ፡ ብሎ ፡ በዘ
ዴ ፡ አዳነው ።

«እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ጌታዬ! አንድ ፡ ልዑል ፡ እንዴት ፡
ኮዛክ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል? ኮዛክ ፡ ቢሆኑ ፡ ኖሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ልብስና ፡ የልዑላን ፡ መለዮ ፡ ከየት ፡ ያመጡ ፡ ነበር?»

«በቃ ፡ ውሸት ፡ አልፈልግም!» አለና ፡ ወታደሩ ፡ ለመ
ጮኸ ፡ አፉን ፡ ከፈተ ።

«ግርማዊ ፡ ሆይ! ዝም ፡ ይበሉ! ዝም ፡ ይበሉ! ስለእግ
ዚአብሔር ፡ ብለው! ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ታይቶ ፡ የማይታወቀ
ውን ፡ ያህል ፡ ውለታዎን ፡ እንከፍለዎታለን ። ሁለት ፡ የወርቅ ፡
ዱካት ፡ እንሰጥዎታለን ።»

«አሃ! ሁለት ፡ ዱካት! ሁለት ፡ ዱካት ፡ ለኔ ፡ ምንም ፡ አይ
ደል ። ጸጉር ፡ ቆራጭ ፡ የጢሜን ፡ ግማሽ ፡ ሲላጨኝ ፡ ሁለት ፡
ዱካት ፡ ነው ፡ የምከፍለው ። በል ፡ አሁን ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡
ስጠኝ ፡ አይሁድ ፤ አለዚያ ፡ አሁን ፡ መጮኺ ፡ ነው!»
አለ ።

«አሁን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ምን ፡ አስጠየቀው!» ብሎ ፡
በሃዘን ፡ ፊቱ ፡ ጠውልጎ ፡ የቆዳ ፡ ከረጢቱን ፡ ከወገቡ ፡ ፈታና ፡
ሲመለከት ፡ በውስጡ ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ገንዘብ ፡ አለመኖሩን ፡
ወታደሩም ፡ ከመቶ ፡ በላይ ፡ ቁጥር ፡ አለመቻሉን ፡ ተገን
ዝቦ ፡ ወዲያው ፡ ደስ ፡ አለው ።

ወታደሩ ፡ የበለጠ ፡ ባለመጠየቁ ፡ እንደመጸጸት ፡ ብሎ ፡
ገንዘቡን ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ ሲያገላብጥ ፡ ተመለከተና ፡ ያንኬል ፡
ወደ ፡ ቡልባ ፡ ዞሮ ፤ «ጌታዬ ፡ ቶሎ ፡ እንሂድ! እንዳዩት ፡ እዚ
ህ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ክፉዎች ፡ ናቸው ፡» አለው ።

ቡልባ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ወታደሩ ፡ ዞሮ ፤ «እንዴት ፡ አንት ፡
ሰይጣን! ገንዘቡን ፡ ወስደህ ፡ ደግሞ ፡ ኮዛኮቹን ፡ አላሳይም ፡



ልትል ፡ ነው? የለም ፤ ማሳየት ፡ አለብህ ። ገንዘቡን ፡ ከተቀ
በልህ ፡ እምቢ ፡ ልትል ፡ አትችልም ፡» አለው ።

ወታደሩም ፤ «ሂዱ ፡ ነው ፡ የምላችሁ! አለዚያ ፡ አሁኑኑ ፡
ሰው ፡ መጥራቴ ፡ ነው!» ሲል ፡ ያንኬል ፤ «ጌታዬ! ጌታዬ!
ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ እንሂድ ፤ እነዚህ ፡ የተረገሙ ፡
ሰዎች ፡ የሚያስጠላ ፡ ቅጣት ፡ ይጣልባቸው!» እያለ ፡ ቡል
ባን ፡ ይለምን ፡ ጀመር ።

ቡልባ ፡ ቀስ ፡ ብሎ ፡ ዞረና ፡ አንገቱን ፡ ደፍቶ ፡ ተጓዘ ፤
ያንኬልም ፡ በከንቱ ፡ ባባከነው ፡ ዱካት ፡ ተማርሮ ፡ ነበርና ፡
ኋላ ፡ ኋላው ፡ እየተከተለ ፡ በጸጸት ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ነበር ፤

«እስቲ ፡ ምን ፡ አስቆጣዎት? ያ ፡ ውሻ ፡ የፈለገውን ፡ ቢና
ገር ፡ ምን ፡ ቸገረዎ ፡ ነበር ። እነሱ ፡ ያለ ፡ ዘለፋ ፡ የማይኖሩ ፡
ፍጥረቶች ፡ ናቸው ። ወይኔ! እንዲህ ፡ ያለ ፡ እድል! እኛኑ ፡ ለማ
ባረር ፡ ብቻ ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ ያስከፍለን! እኛን ፡ ግን ፡ ጸጉራ
ችንን ፡ እየነጩ ፡ ፊታችንም ፡ ለማየት ፡ እስኪያስጠላ ፡ ድረስ ፡
ሲቀጠቅጡን ፡ መቶ ፡ ዱካት ፡ የሚሰጠን ፡ የለም! አይ ፡ ፈጣ
ሪዬ! ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አመጣህብኝ!»

ነገር ፡ ግን ፡ የነገሩ ፡ አለመሳካት ፡ ንዴት ፡ የባሰውን ፡
በቡልባ ፡ ዓይኖች ፡ ላይ ፡ እንደነበልባል ፡ ይንቀለቀል ፡ ጀመር ።

«ና ፡ እንሂድ! ወደ ፡ አደባባይ ፡ ሄደን ፡ እንዴት ፡ እንደ
ሚያሰቃዩት ፡ መመልከት ፡ አለብኝ ፡ » አለው ።

ያንኬል ፤ «ምነው ፡ ጌታዬ! ለምን ፡ ለመሄድ ፡ ይፈል
ጋሉ? አሁን ፡ ልንረዳው ፡ አንችልም ፡» ሲል ፡ ቡልባ ፡ ግን ፡
«መሄድ ፡ አለብን!» በማለት ፡ ክርር ፡ አለ ።

አይሁዱም ፡ እንደሞግዚት ፡ በትካዜ ፡ ቁና ፡ ተነፈ
ሰና ፡ ይከተል ፡ ጀመር ።

የመገደያውን ፡ አደባባይ ፡ ለማግኘት ፡ የሚያዳግት ፡
አልነበረም ። ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተሰብስቦበት ፡ ይታያል ። በዚያ ፡
የጭካኔ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ትርኢት ፡ ለተራው ፡ ሕ
ዝብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለከፍተኞች ፡ ሰዎችም ፡ አስደሳች ፡

ሆኖ ፡ የሚቆጠር ፡ ነበር ። እጅግ ፡ ሃይማኖተኛ ፡ ባልቴቶች፥ እንዲሁም ፡ ፈሪ ፡ ልጃገረዶች ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ከማየት ፡ አይቦዝኑም ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከአዩት ፡ በኋላ ፡ በደም ፡ የተጨማለቀ ፡ ሬሣ ፡ በሕልማቸው ፡ እየመጣ ፡ በቅዠት ፡ ቢያስጮኻቸውም ፡ እድል ፡ ካጋጠማቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ለማየት ፡ አይታክቱም ። ብዙዎቹ ፤ «አቤት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ጭካኔ!» ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ዓይናቸውን ፡ ጨፍነው ፡ ፊታቸውንም ፡ ያዞራሉ ። ሆኖም ፡ አገዳደሉን ፡ እስከመጨረሻው ፡ ሳይመለከቱ ፡ አይመለሱም ። አንዳንዶቹም ፡ አፋቸውን ፡ ከፍተውና ፡ እጆቻቸውም ፡ ዘርግተው ፡ አገዳደሉን ፡ ለመመልከት ፡ ሲንገበገቡ ፡ ይታያሉ ። ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ለመመልከትም ፡ በሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተራምደው ፡ በማለፍ ፡ በወደዱ ፡ ነበር ።

እዚያ ፡ ከተሰበሰበው ፡ ሕዝብ ፡ ጠባብና ፡ ትንንሽ ፡ ጭንቅላት ፡ መካከል ፡ የአንድ ፡ ሥጋ ፡ አራጅ ፡ ወፍራም ፡ ፊት ፡ ይታያል ። እሱም ፡ እዚያ ፡ ቆሞ ፡ ነገሩን ፡ ሁሉ ፡ በአዋቂነት ፡ የሚያመዛዝን ፡ መስሎ ፡ እየተመለከተ ፤ በዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በአንድ ፡ መጠጥ ፡ ቤት ፡ አብሮት ፡ ስለሚሰክር ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ ከሚለው ፡ አንድ ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ሠሪ ፡ ጋር ፡ ይነጋገራል ። እዚያ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ ሕዝብ ፡መካከል ፡ አንዳንዶቹ ፡ ስለሚያዩት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በማላገጥና ፡ በክፋት ፡ እየተናገሩ ፡ እንዲያውም ፡ እርስ ፡ በእርስ ፡ ውርርድ ፡ ይወራረዳሉ ። አብዛኛው ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚደረገውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የማየት ፡ ፍላጐት ፡ ብቻ ፡ ያደረባቸው ፡ አፍንጫቸውን ፡ እየጐረጐሩ ፡ የቆሙ ፡ ተራ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

በፊት ፡ ለፊቱ ፡ መስመር ፡ የከተማው ፡ ዘበኞች ፡ ከተሰለፉበት ፡ አጠገብ ፡ የወታደር ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ወጣት ፡ መኮንን ፡ (ወይም ፡ መኰንን ፡ ለመምሰል ፡ የሚጥር ፡) ቆሟል ። አለባበሱ ፡ ሲታይ ፡ በቤቱ ፡ አንድ ፡ ቀዳዳ ፡ ሸሚዝና ፡ አንድ ፡ አሮጌ ፡ ጫማ ፡ ብቻ ፡ ሲቀር ፡ ሌላውን ፡ ያለ ፡ የሌለውን ፡



ለብሶ ፡ እንደመጣ ፡ ግልጽ ፡ ሆኖ ፡ ይታይ ፡ ነበር ። እንደ ፡ ዱካት ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የተንጠለጠለበት ፡ ሰንሰለት ፡ በአንገቱ ፡ አጥልቆአል ። ከእጮኛው ፡ ከዩዜሱ ፡ ጐን ፡ ቆሞ ፡ የሃር ፡ ቀሚሷን ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ነክቶ ፡ እንዳያበላሽባት ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ይገላመጣል ። ለእጮኛውም ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ሳይቀር ፡ በዝርዝር ፡ ያስረዳታል ።

«እዚህ ፡ የምታያቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፤ የኔ ፡ ፍቅር ፡ ዩዜሱ ፤ ወንጀለኞቹ ፡ ሲገደሉ ፡ ለማየት ፡ የመጡ ፡ ናቸው ። ያ ፡ መጥረቢያና ፡ ሌላም ፡ መሳርያ ፡ ይዞ ፡ የምታይው ፡ ሰውየም ፡ ገዳዩ ፡ ሲሆን ፡ እሱም ፡ ወንጀለኞቹን ፡ ካሰቃየ ፡ በኋላ ፡ ይገድላቸዋል ። ከእነሱ ፡ አንዳቸውን ፡ በሽክርክረቱ ፡ ሲሰባብረውና ፡ በሌላም ፡ መንገድ ፡ ሲያሰቃየው ፡ የወንጀለኛው ፡ ነፍሱ ፡ ገና ፡ አትወጣም ። ኋላ ፡ ግን ፡ አንገቱን ፡ ሲቆርጠው ፡ ይሞታል ። ከዚያ ፡ በፊት ፡ ወንጀለኛው ፡ ይጮኻል ፡ ይፈራገጣል ፤ ግን ፡ አንገቱ ፡ ከተቆረጠ ፡ ወዲያ ፡ ለዘለዓለም ፡ መጮኽ ፡ ወይም ፡ መብላትና ፡ መጠጣት ፡ አይችልም ። ምክንያቱም ፡ የኔ ፡ ፍቅር ፤ ጭንቅላቱ ፡ ከሰውነቱ ፡ ተለይቶ ፡ ስለሚወድቅ ፡ ነው ።»

ዩዜሱ ፡ የሚነግራትን ፡ ሁሉ ፡ በድንጋጤና ፡ በመገረም ፡ ታዳምጣለች ።

የቤቶቹ ፡ ጣራ ፡ ሕዝብ ፡ ተከምሮበታል ። ከየመስኮቶቹም ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ ይታያል ። በበረንዳዎቹ ፡ ላይ ፡ የጨዋው ፡ ወገኖች ፡ ተቀምጠዋል ። የአንድ ፡ የምትስቅ ፡ ወይዘሮ ፡ እንደ ፡ ስኳር ፡ የነጣ ፡ የሚያምር ፡ ክንድ ፡ በረንዳውን ፡ ተደግፎ ፡ ይታያል ። በረንዳው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ የሚመለከቱም ፡ መኳንንት ፡ ክብር ፡ የተሰማቸውና ፡ የተጀነኑ ፡ ወፈፍራም ፡ መኳንንት ፡ ነበሩ ። የአማረ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ አሳላፊ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመደሰቻ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ይዞ ፡ እየዞረ ፡ ያሳልፋል ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ዓይኑ ፡ መልካም ፡ ቀበጥ ፡ ወይዘሮ ፡ አንድ ፡ ብስኩት ፡ ወይም ፡ ፍሬ ፡ ወተ

ት ፣ በመሰሉት ፣ ጣቶችዋ ፣ ታነሳና ፣ ቁልቁል ፣ ወደተሰበሰበው ፣ ሰው ፣ ትጥላለች ። የተራቡት ፣ ፈረሰኛ ፣ ወታደሮችም ፣ ለመያዝ ፣ ቆባቸውን ፣ አውልቀው ፣ ሲዘረጉ ፣ ቁመቱ ፣ ከሁሉም ፣ ከፍ ፣ የሚለው ፣ አንድ ፣ ወታደር ፣ ቀድሞ ፣ ይቀልበውና ፣ ስሞ ፣ ወደአፉ ፣ ይልከዋል ። ከፎቁ ፣ በረንዳ ፣ ሥር ፣ በተንጠለጠለ ፣ አንድ ፣ የብረት ፣ ጐጆ ፣ ውስጥ ፣ ያለ ፣ ንስር ፣ አሞራም ፣ አንገቱን ፣ ወደ ፣ አንድ ፣ ጐን ፣ ዘንበል ፣ አድርጐ ፣ ከተመልካቾቹ ፣ መካከል ፣ አንዱ ፣ በመሆን ፣ ቁልቁል ፣ ያስተውል ፣ ነበር ። ወዲያው ፣ በሕዝቡ ፣ መሃል ፣ ጫጫታው ፣ በዛና ፣ ከሁሉም ፣ ወገን ፣ «አመጡዋቸው ፤ ኮዛኮቹን ፣ አመጡዋቸው!» የሚል ፣ ድምጽ ፣ ይሰማ ፣ ጀመር ።

ኮዛኮቹ ፣ ያለ ፣ ቆብ ፣ ጐፈሪያቸው ፣ ተገልጦ ፣ ጺማቸውም ፣ ሳይላጭ ፣ መጡ ። አመጣጣቸውም ፣ በፍርሃት ፣ ወይም ፣ በሃዘን ፣ ሳይሆን ፣ በረጋ ፣ የኩራት ፣ መንፈስ ፣ ነበር ። ከተዋበ ፣ ውድ ፣ ጨርቅ ፣ የተሰፋው ፣ ልብሳቸው ፣ አርጅቶ ፣ ተቀዳድዷል ። የተሰበሰበውን ፣ ሕዝብ ፣ ዘወር ፣ ብለው ፣ አላዩም ፣ ወይም ፣ እጅ ፣ አልነሱም ። ከሁሉ ፣ ፊት ፣ ፊት ፣ ያለው ፣ ኦስታፕ ፣ ነበር ።

ሽማግሌው ፣ ቡልባ ፣ ልጁን ፣ ኦስታፕን ፣ ሲያይ ፣ የተሰማው ፣ ስሜት ፣ ምን ፣ ይሆን? ልቡስ ፣ ምን ፣ አስቦ ፣ ይሆን? ከሕዝቡ ፣ መሃል ፣ ቆሞ ፣ ሁናቴውን ፣ ሁሉ ፣ ይመለከት ፣ ነበር ። ኦስታፕ ፣ ቆመ ። ከሌሎቹ ፣ በፊት ፣ መሪሩን ፣ ጽዋ ፣ የሚቀምሰው ፣ እሱ ፣ ነው ። ጓደኞቹን ፣ ተመለከተና ፣ ጮኸ ፣ ብሎ ፣ «አንዳችንም ፣ ብንሆን ፣ ምንም ፣ ድምጽ ፣ እንድናሰማና ፣ እዚህ ፣ የተሰበሰቡት ፣ እርኩስ ፣ ከሃዲዎች ፣ ሁሉ ፣ ክርስቲያን ፣ በስቃይ ፣ ሲጮኽ ፣ እንዳይሰሙ ፣ እግዚአብሔር ፣ ይርዳን!» ብሎ ፣ ወደ ፣ መገደያው ፣ ደርብ ፣ ወጣ ።

ቡልባም ፤ «ጐሽ ፣ የኔ ፣ ልጅ! እንዲያ ፣ ነው ፣ የኔ ፣ ልጅ!» ብሎ ፣ ሽበቶ ፣ ራሱን ፣ አቀረቀረ ።



ገዳዩ ፣ የኦስታፕን ፣ ቡትቶ ፣ ከላዩ ፣ ላይ ፣ መንጭቆ ፣ አወለቀው ። እጅና ፣ እግሩም ፣ ተወጥረው ፣ ታሰሩ ፤ ከዚያ ፣... ግን ፣ ያን ፣ አሰቃቂ ፣ አገዳደል ፣ ዘርዝሮ ፣ በመግለጽ ፣ የአንባቢን ፣ መንፈስ ፣ አናውክም ። ጭካኔው ፣ ያ ፣ የአረመኔ ፣ ዘመን ፣ ያፈለቀው ፣ ጠባይ ፣ ነው ። ሰው ፣ ደም ፣ ጠማሽ ፣ ወታደራዊ ፣ ኑሮ ፣ በሚኖርበት ፣ በዚያ ፣ ዘመን ፣ ልቡ ፣ እንደ ፣ ድንጋይ ፣ ጠጥሮ ፣ ከሰብአዊ ፣ ርኅራኄ ፣ ጨርሶ ፣ የራቀ ፣ ነበር ። ይህን ፣ አሰቃቂ ፣ ተግባር ፣ ለመቃወም ፣ የሚሞክሩ ፣ ጥቂት ፣ ሰዎች ፣ ቢገኙም ፣ ልፋታቸው ፣ ከንቱ ፣ ነበር ። ንጉሡና ፣ እንዲሁም ፣ መልካም ፣ አስተያየት ፣ ያላቸው ፣ መኳንንት ፣ ሳይቀሩ ፣ እንዲህ ፣ ያለው ፣ የጭካኔ ፣ ቅጣት ፣ በኮዛኮች ፣ ዘንድ ፣ የባሰ ፣ ቂም ፣ ከማትረፉ ፣ በቀር ፣ የማይጠቅም ፣ መሆኑን ፣ ለማስረዳት ፣ ቢሞክሩም ፣ ሰሚ ፣ አላገኙም ። አስተዋይ ፣ ባልሆነ ፣ የህፃን ፣ አመራር ፣ ምክር ፣ ቤቱን ፣ በመንግሥቱ ፣ ላይ ፣ እንዳለ ፣ ጉድፍ ፣ ባደረጉት ፣ ሕገ ፣ ወጥና ፣ ትዕቢተኛ ፣ መኳንንት ፣ ፊት ፣ የነገሥታትና ፣ የጠቢብ ፣ መማክርት ፣ ሥልጣን ፣ ምንም ፣ ፍሬ ፣ አልነበረውም ።

ኦስታፕ ፣ ስቃዩን ፣ ሁሉ ፣ በጸጥታ ፣ ተቀበለ ፤ ሩቅ ፣ ላሉት ፣ ተመልካቾች ፣ እንኳን ፣ እስኪሰማ ፣ ድረስ ፣ የእጅና ፣ የእግሩን ፣ አጥንት ፣ ሲሰባብሩት ፣ እንኳን ፣ እንኳን ፣ መጮኽ ፣ አላቃሰተም ። ታራስ ፣ በሕዝቡ ፣ መሃል ፣ ቆሞ ፣ አንገቱን ፣ እንዳቀረቀረ ፣ አንዳንድ ፣ ጊዜ ፣ ቀና ፣ ብሎ ፣ ቀስ ፣ ብሎ ፣ «ጐሽ ፣ ልጄ! እንዲያ ፣ ነው ፣ ልጄ!» ይላል ።

ኦስታፕ ፣ ወደ ፣ መጨረሻው ፣ የሞት ፣ ስቃይ ፣ ጐትተው ፣ ሲወስዱት ፣ ብቻ ፣ ኃይሉና ፣ ጽናቱ ፣ እየሟሟ ፣ የሄደ ፣ መሰለ ። ዓይኖቹን ፣ እያንከራተተ ፣ ዙሪያውን ፣ ተመለከተ ፤ አምላክ ፣ ሆይ! የሚታየው ፣ ሁሉ ፣ እንግዳና ፣ ያልታወቀ ፣ ፊት ፣ ነው! አንድ ፣ ተወዳጅ ፣ ሰው ፣ እዚያ ፣ ቆሞ ፣ አሟሟቱን ፣ ባየለት ፣ ኖሮ! የደካማ ፣ የእናቱን ፣ ሃዘንና ፣ ስቅስቅታ ፣ ለመስማት ፣ ወይም ፣ ደረትዋን ፣ እየደቃችና ፣ ጸጉርዋን ፣ እየነ

ጨች ፡ የምትጮኽ ፡ ሚስት ፡ አልተመኘም ። አሁን ፡ የተመኘው ፡ ጠቢብ ፡ ቃሉ ፡ የሚያጽናናውና ፡ በሞቱ ፡ ሰዓት ፡ አዲስ ፡ ጉልበት ፡ የሚሰጠው ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ ለማየት ፡ ነው ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ብርታቱ ፡ ሁሉ ፡ ከዳውና ፡ ነፍሱ ፡ እየተጨነቀች ፤ «ባትኮ! የት ፡ ነህ? ትሰማኛለህ ?» ብሎ ፡ ጮኸ ።

ረጭ ፡ ባለው ፡ ጸጥታ ፡ የተሰበሰበው ፡ ሚሊዮን ፡ ሕዝብ ፡ እስኪንቀጠቀጥ ፡ ድረስ ፡ «እሰማሃለሁ!» ሲል ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ድምጽ ፡ አስተጋባ ።

ወዲያው ፡ ፈረሰኛ ፡ ዘበኞች ፡ በፍለጋ ፡ እየተጣደፉ ፡ በግርግሩ ፡ መሃል ፡ ያስሱ ፡ ጀመር ። ያንኬል ፡ የሞት ፡ ያህል ፡ ገረጣ ፤ ፈላጊዎቹ ፡ ፈረሰኞችም ፡ ሲያልፉት ፡ በድንጋጤ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ታራስን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ አለ ። ታራስ ፡ ግን ፡ ከኋላው ፡ የለም ፤ አንድም ፡ ምልክት ፡ ሳይተው ፡ ጠፍቶ አል ።

## ምዕራፍ ፡ አስራ ፡ ሁለት ።

የታራስ ፡ ምልክት ፡ እንደጠፋ ፡ አልቀረም ። መቶ ፡ ሃያ ፡ ሺ ፡ የኮዛክ ፡ ጦር ፡ ሠራዊት ፡ በኡክሬይን ፡ ጠረፍ ፡ ብቅ ፡ አለ ። ይህ ፡ ጦር ፡ እንደቀድሞው ፡ ለዘረፋ ፡ የወጣ ፡ ወይም ፡ ታታሮችን ፡ የሚያባርር ፡ ቀላል ፡ ጦር ፡ አልነበረም ። የሕዝቡ ፡ ትዕግሥት ፡ ስለአለቀ ፡ መላው ፡ አገር ፡ ተነስቶአል ። የመብቱን ፡ መነካት ፤ የባህሉን ፡ መናቅ ፤ አባት ፡ ያቆየው ፡ ሃይማኖቱንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ መደፈር ፤ የባእድ ፡ መሳፍንትንና ፡ ጳጳሳት ፡ ጭቆና ፤ በክርስቲያን ፡ ምድር ፡ የአይሁድን ፡ የበላይነት ፡ ለመበቀል ፡ ሕዝቡ ፡ ቆርጦ ፡ ተነስቶ አል ።

የጦሩ ፡ አዝማች ፡ ሄትማን ፡ አስትራኒትሳ[3] ፡ ነው ። እሱም ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ ወጣት ፡ ቢሆን ፡ ልበ ፡ ሙሉ ፡ ጐበዝ ፡ ነበር ። ከጐኑ ፡ የጥንት ፡ የጦር ፡ ጓደኛውና ፡ አማካሪው ፡



ጉንያፋ ፡ አለ ። እያንዳንዳቸው ፡ አስራ ፡ ሁለት ፡ ሺ ፡ ወታደር ፡ ያላቸውን ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ስምንት ፡ ኮሎኔሎች ፡ ይመራሉ ። በፈረሰኛና ፡ በእግረኛ ፡ ክፍልም ፡ ሌሎች ፡ ብዙ ፡ መኮንኖች ፡ ነበሩ ። ከተመዘገቡት ፡ ኮዛኮች ፡ ሌላ ፡ በቁጥር ፡ ከእነሱ ፡ የማያንስ ፡ ወዶ ፡ ዘማች ፡ ጦር ፡ በእግርም ፡ በፈረስ ፡ ተከትሎአል ። በየትም ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ ኮዛኮች ፡ አንድነት ፡ ነው ፡ የተቀሰቀሱት ። ከቺጊሪን ፤ ከፔሬያስላቭ ፤ ከባቱሪንና ፡ ከግሉኾቭ ፡ ከላኛውና ፡ ከታችኛው ፡ የድኔፐር ፡ ዳርቻ ፡ በውስጡ ፡ ካሉት ፡ ደሴቶችም ፡ ተነስተው ፡ መጥተዋል ። ስፍር ፡ ቁጥር ፡ የሌላቸው ፡ ፈረሶችና ፡ ሰረገላዎች ፡ ሜዳውን ፡ አለበሱት ። ከነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ኮዛኮች ፡ ከስምንቱ ፡ ክፍለ ፡ ጦሮች ፡ ውስጥ ፡ ምርጥ ፡ የሆነው ፡ በታራስ ፡ ቡልባ ፡ የሚመራው ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ነበር ። ታራስ ፡ በማናቸውም ፡ ረገድ ፡ ከሌሎች ፡ ጐልቶ ፡ ይታያል ። የበሰለ ፡ እድሜው ፡ የጦር ፡ ልምዱ ፡ ወታደር ፡ የማዘዝ ፡ ችሎታው ፡ እንዲሁም ፡ በጠላት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ከማናቸውም ፡ የበለጠ ፡ መሪር ፡ ጥላቻ ፡ ከሌሎቹ ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታወቅ ፡ አድርጎታል ። ኮዛኮቹ ፡ ራሳቸው ፡ እንኳን ፡ ሳይቀሩ ፡ የጭካኔ ፡ መንፈሱን ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ገመቱት ። በአእምሮው ፡ የሚገባው ፡ ፍርድ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ብቻ ፤ በጦር ፡ ምክር ፡ ስብሰባ ፡ ላይም ፡ የሚያቀርበው ፡ ምክር ፡ የማጥፋት ፡ ምክር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

የተደረገውን ፡ ጦርነትና ፡ የኮዛኮቹን ፡ ሥራ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ለመግለጽ ፡ አይመችም ። ሁሉም ፡ በታሪክ ፡ የማስታወሻ ፡ ገጾች ፡ ላይ ፡ ሰፍሮ ፡ ይገኛል ። በሩሲያ ፡ ምድር ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የተነሳ ፡ ጦርነት ፡ እንዴት ፡ እንደሆነ ፡ የታወቀ ፡ ነው ። ከሃይማኖት ፡ የጠነከረ ፡ ምንም ፡ ኃይል ፡ አይገኝም ። ሃይማኖት ፡ በሞገደኛ ፡ ባህር ፡ መሃል ፡ እንደ ቆመ ፡ ቋጥኝ ፡ የማይናወጽ ፡ ነው ። የማይሰበር ፡ ግድግዳውን ፡ ከጠሊቁ ፡ ባህር ፡ መደብ ፡ ተክሎ ፡ ቆሞ ፡ ከማናቸውም ፡ አንጻር ፡ እየታየ ፡ አላፊውን ፡ ማእበል ፡ በድፍረት ፡ ይ

መለከተዋል ። ከሱ ፡ ጋር ፡ የሚጋጭ ፡ መርከብም ፡ ወየ
ውለት! ተሰባብሮና ፡ ተስነጣጥቆ ፡ በላዩም ፡ ላይ ፡ ያለው ፡
ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተደምስሶ ፡ ይሰምጣል ። የተሳፋሪዎቹ ፡ ሰዎ
ችም ፡ የጭንቅ ፡ ጩኸት ፡ አየሩን ፡ ያናጋዋል ።

የፖላንድ ፡ ጦር ፡ ኮዛኮች ፡ ነጻ ፡ ካወጡዋቸው ፡ ከተሞ
ች ፡ እንዴት ፡ እየሸሸ ፡ እንደሄደ ፤ ወለድ ፡ አግድ ፡ አበዳሪ ፡
አይሁዶች ፡ ሁሉ ፡ እንዴት ፡ እንደተሰቀሉ ፤ የንጉሡ ፡ ሄት
ማን ፡ ኒኮላይ ፡ ፖቶጽኪይ ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊቱ ፡ ጋር ፡ በዚህ ፡
ኃያል ፡ ጦር ፡ ፊት ፡ እንደተጨነቀ ፡ ተባርሮና ፡ ተንከራትቶ ፡
በአንድ ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ አብዛኛው ፡ ሠራዊቱ ፡ እን
ዳለቀበት ፡ አስፈሪው ፡ የኮዛክ ፡ ጦር ፡ በፖሎኖየ ፡ ከተማ ፡
ከብቦ ፡ ሠራዊቱን ፡ ጨርሶበት ፡ የፖሊሹ ፡ ሄትማን ፡ የኮዛ
ኮቹን ፡ ፍላጐት ፡ ሁሉ ፡ ለመፈጸም ፤ መብታቸውንም ፡ ለመ
መለስ ፤ በንጉሡና ፡ በሚኒስትሮቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ በመሃላ ፡
ቃል ፡ እንደገባ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ በታሪክ ፡ ማስታወሻዎች ፡
ላይ ፡ በዝርዝር ፡ ሰፍሮ ፡ ይገኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ኮዛኮቹ ፡ የፖ
ሊሽ ፡ መሃላ ፡ ዋጋ ፡ እንደሌለው ፡ ስለሚያውቁ ፡ በዚህ ፡
አልተታለሉም ። ፖቶጽኪይም ፡ የከተማው ፡ የሩሲያ ፡ ቀ
ሳውስት ፡ ሕይወቱን ፡ ባያተርፉት ፡ ኖሮ ፡ በስድስት ፡ ሺ ፡
ዱካት ፡ በተገዛ ፡ ሰንጋ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ በአደባባይ ፡ የመሳ
ፍንትንና ፡ የወይዛዝርትን ፡ ዓይን ፡ ለመማረክ ፡ ባልበቃ ፡ ነ
በር ። ቀሳውስቱ ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖአቸውን ፡ ለብሰው ፤ ሥዕ
ል ፡ መስቀል ፡ ተሸክመው ፡ በአቡኑ ፡ በራሳቸው ፡ መሪነ
ት ፡ ሲመጡ ፡ ጊዜ ፡ ኮዛኮቹ ፡ ቆባቸውን ፡ አውልቀው ፡ አን
ገታቸውን ፡ ደፉ ። በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ ለንጉ
ሡም ፡ እንኳን ፡ ቢሆን ፡ እንዲያ ፡ ያለ ፡ አክብሮት ፡ አላሳ
ዩም ፡ ነበር ። በራሳቸው ፡ የክርስቲያን ፡ ቤተ ፡ ክህነት ፡ ላይ ፡
ግን ፡ ለማመጽ ፡ ስለአልደፈሩ ፡ ለቀሳውስቶቻቸው ፡ ታዛ
ዥ ፡ ሆኑ ። የኮዛኮቹ ፡ ሄትማንና ፡ ኮሎኔሎቹ ፡ ፖቶጽኪይን ፡
የክርስቲያንን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዳይጨቁንና ፡ የኮዛክ



ንም ፡ ክብር ፡ እንዳይነካ ፡ ካስማሉት ፡ በኋላ ፡ ሊለቁት ፡ ተስ
ማሙ ። አንድ ፡ ኮሎኔል ፡ ብቻ ፡ እንዲህ ፡ ባለው ፡ የሰላም ፡
ስምምነት ፡ አልተስማማም ። እሱም ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ ነበር ።
ከጸጉሩ ፡ አንድ ፡ ጭብጥ ፡ ነጨና ፤ «ስሙኝ ፡ ሄትማኑና ፡
ኮሎኔሎች! እንዲህ ፡ ያለ ፡ የሴት ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ! ፖሊ
ሾችን ፡ አትመኑአቸው ። እነዚህ ፡ ውሾች ፡ በኋላ ፡ ይከዱ
ናል!» አለ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ሄትማኑ ፡ ውሉ ፡ ቀርቦለት ፡ በፈረመ ፡ ጊዜ ፡
ታራስ ፡ የከበረ ፡ የቱርክ ፡ ጐራዴውን ፡ አወጣና ፡ እንደ ፡
አገዳ ፡ ከሁለት ፡ ሰብሮ ፡ ሰባሪዎቹን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ ወረ
ወረና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«ደህና ፡ ሁኑ! እነዚህ ፡ ሁለት ፡ ሰባሪዎች ፡ እንደገና ፡
ተገናኝተው ፡ ጐራዴ ፡ እንደማይሆኑ ፡ እነሆ ፡ እኛም ፡ ጓደ
ኞቼ ፡ ሆይ ፤ ዳግመኛ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ አንተያይም ። እነሆ ፡
የመሰናበቻ ፡ ቃሌን ፡ አስታውሱ! በሞታችሁ ፡ ሰዓት ፡ ታስ
ታውሱኛላችሁ! አሁን ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ የተዋዋላችሁ ፡
መሰላችሁ? አሁን ፡ የሚያልፍላችሁ ፡ መሰላችሁ? የለም ፡
ሌሎች ፡ ናቸው ። ከበላዮቻችሁ ፡ ሆነው ፡ የሚያልፍላቸው ፡
አንተም ፡ ሄትማን ፡ ጭንቅላትህ ፡ እንደስልቻ ፡ ተገፎ ፡ የስ
ንዴ ፡ ገለባ ፡ ከተሞላ ፡ በኋላ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ በየገበያው ፡
እየዞረ ፡ ሲታይ ፡ ይኖራል ። እናንተም ፡ መኳንንት ፡ ሆይ ፤
የምትድኑ ፡ አይምሰላችሁ! እንደ ፡ በግ ፡ በብረት ፡ ድስት ፡
ያልተቀቀላችሁ ፡ እንደሆን ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ በስብሳችሁ ፡
ትቀራላችሁ!»

ወደ ፡ ወታደሮቹ ፡ ደግሞ ፡ ዞወር ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤

«እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ወጣቶቼ ፡ ሳትልከሰከሱ ፡ እውነ
ተኛ ፡ የኮዛክ ፡ ሞት ፡ ለመሞት ፡ የምትፈልጉ ፡ እነማናችሁ?
ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ቤታችሁ ፡ ተመልሳችሁ ፡ ከሃዲ ፡
በመሆን ፡ የፖሊሽ ፡ ቄስ ፡ በጀርባችሁ ፡ አዝሎ ፡ ለመዞር ፡
ትፈልጋላችሁ?»

የቡልባ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ወታደሮች ፡ በሞላ ፤ «እርስዎን ፡ እንከተላለን ፡ ኮሎኔል!» ብለው ፡ ሲጮኹ ፡ ከሌላም ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ብዙዎቹ ፡ ወደሱ ፡ አዘንብለው ፡ ተቀላቀሉ ።

«እንዲህ ፡ ከሆነ ፡ ተከተሉኝ!» አለና ፡ ታራስ ፡ ቆቡን ፡ ቅንድቡ ፡ ድረስ ፡ አጥልቆ ፡ ለመቅረት ፡ የወሰኑትን ፡ ገላመጠና ፡ ፈረሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

«በክፉ ፡ ነገር ፡ ስማችን ፡ እንዳይነሳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳን! ተከተሉኝ ፡ ጎበዝ! ካቶሊኮቹን ፡ እንጎበኛቸዋለን!»

ይህንን ፡ ተናግሮ ፡ ታራስ ፡ ፈረሱን ፡ ሲሸነቁጥ ፡ መቶ ፡ የሚሆን ፡ ሠረገላና ፡ እንዲሁም ፡ ብዙ ፡ ኮዛኮች ፡ በእግርም ፡ በፈረስ ፡ ተከተሉት ። ዞወር ፡ ብሎ ፡ ከዘመቻው ፡ የቀሩትን ፡ ገላመጣቸው ፡ ዓይኖቹም ፡ በቁጣ ፡ ተሞልተው ፡ ነበር ። ማንም ፡ ሊያስቀረው ፡ አልደፈረም ። መላው ፡ የጦር ፡ ሠራዊት ፡ እየተመለከተ ፡ የሱ ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ተነጥሎ ፡ ዘመተ ። ታራስም ፡ ዞሮ ፡ የቀሩትን ፡ እንደገና ፡ ገላመጣቸው ።

ሄትማኑና ፡ ኮሎኔሎቹ ፡ አቀርቅረው ፡ ቆመው ፡ መጥፎ ፡ ትንቢት ፡ እንደታያቸው ፡ ሁሉ ፡ በትካዜ ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በሃሳብ ፡ ተዋጡ ። ታራስ ፡ የተናገረው ፡ ትንቢት ፡ ከንቱ ፡ ሆኖ ፡ አልቀረም ። ሁሉም ፡ እንደተናገረው ፡ ተፈጸመ ። ወዲያው ፡ ብዙ ፡ ሳይቆይ ፡ በካኔቭ ፡ መሃላው ፡ ፈረሰና ፡ የሄትማኑ ፡ እንዲሁም ፡ የሌሎች ፡ የዋና ፡ ዋናዎቹ ፡ ጭንቅላት ፡ ተቆርጦ ፡ በአጠና ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠለጠለ ።

ታራስስ ፡ ከምን ፡ ደረሰ? ታራስ ፡ ከነሠራዊቱ ፡ ወደ ፡ ፖላንድ ፡ ጠልቆ ፡ ገብቶ ፡ ከአሥራ ፡ ስምንት ፡ ከተሞችና ፡ አርባ ፡ የካቶሊክ ፡ ቤተ ፡ መቅደሶች ፡ አቃጥሎ ፡ ክራኮቭ ፡ ደረሰ ። የገደላቸው ፡ መኳንንትና ፡ ያፈራረሳቸው ፡ የመሳፍንት ፡ ህንጻዎችም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። የታራስ ፡ ኮዛኮች ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ የተቀበረውን ፡ የወይንና ፡ የማር ፡ ጠጅ ፡ ከመሳፍንቱ ፡



እቃ ፡ ቤት ፡ ቆፍረው ፡ እያወጡ ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ረበረቡት ። ውድ ፡ ዋጋ ፡ ያላቸውን ፡ ልብሶችና ፡ በእቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚያገኙትን ፡ ማናቸውንም ፡ እቃ ፡ ሰባብረውና ፡ ቀዳድደው ፡ አቃጠሉት ። የታራስ ፡ ቋሚ ፡ ትእዛዝ ፡ «ምንም ፡ ነገር ፡ አትማሩ!» የሚል ፡ ነበር ። ቅንድባቸው ፡ ጥቋቁርና ፡ ደረታቸውም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ለነጣው ፡ ፊታቸው ፡ ሉል ፡ ለሚመስለው ፡ የተዋቡ ፡ ወይዛዝርት ፡ እንኳን ፡ ኮዛኮቹ ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አላሳዩም ። በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ቢጠለሉም ፡ አልዳኑም ። ታራስ ፡ ከነቤተ ፡ መቅደሱ ፡ አቃጠላቸው ። በነበልባሉ ፡ መሃል ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ የነጣው ፡ ጣታቸው ፡ እየተርገበገበ ፡ በሚዘገንን ፡ ድምጽ ፡ ሲጮኹ ፡ ደረቅዋ ፡ ምድር ፡ እንኳን ፡ ባዘነችላቸው ፡ ነበር ። የመስኩ ፡ ሳርም ፡ ሳይቀር ፡ በኃዘን ፡ አንገቱን ፡ በደፋ ። ጨካኞቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ርኅራኄ ፡ አላሳዩም ። ሕጻናትን ፡ ሳይቀር ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ በጦር ፡ ወግተው ፡ እያንጠለጠሉ ፡ ነበልባሉ ፡ ውስጥ ፡ ይጨምሩአቸዋል ።

«ይህ ፡ የአስታጥ ፡ የተዝካር ፡ ድግስ ፡ ነው ፡ እናንት ፡ ከሃዲዎች!»

ታራስ ፡ ይህን ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይናገርም ፤ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ የአስታጥ ፡ ማስታወሻ ፡ ድግስም ፡ በደረሰበት ፡ ከተማና ፡ መንደር ፡ ሁሉ ፡ ልማድ ፡ አደረገው ። የፖሊሽ ፡ መንግሥት ፡ ይህን ፡ ሲመለከት ፡ ከተራ ፡ ወረራ ፡ የላቀ ፡ ድርጅት ፡ መሆኑን ፡ በመገንዘብ ፡ ያንኑ ፡ የቀድሞውን ፡ ፖቶጽኪይን ፡ አምስት ፡ ክፍለ ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ እንዲዘምት ፡ አዘዘው ።

ኮዛኮቹ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ ፈረሶቻቸው ፡ እስኪዝሉ ፡ ድረስ ፡ ጋልበው ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ሲሸሹ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በድኔስተር ፡ ዳር ፡ እንደሰፈሩ ፡ ደረሱባቸው ።

ኮዛኮቹ ፡ የሰፈሩበት ፡ የፈራረሰ ፡ ጥንታዊ ፡ ግቢ ፡ ከድኔስተር ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ባለ ፡ ገደል ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ነበር ። ኮዛ

ኮቹ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እንዳሉ ፡ ገደሉ ፡ ከጀርባቸው ፡ ሆኖ ፡ የንጉሡ ፡ ሄትማን ፡ ፖቶጽኪይ ፡ ከሚዳው ፡ በኩል ፡ በሁለት ፡ አቅጣጫ ፡ ከበባቸው ። ኮዛኮቹ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሉ ፡ በግንቡ ፡ ፍራሽ ፡ ሽክላና ፡ ድንጋይ ፡ ተከላከሉ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ስንቃቸውም ፡ ኃይላቸውም ፡ እየተቀነሰ ፡ ስለሄደ ፡ ታራስ ፡ በጠላቶቹ ፡ መሃል ፡ እየተዋጋ ፡ ለማለፍ ፡ ቆረጠ ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ ሲነሱ ፡ ታራስ ፡ ቆም ፡ ብሎ ፤ «ቆዩ! የትንባሆ ፡ ማጨሻዬን ፡ ጥያለሁ ፤ እነዚህ ፡ ከሃዲ ፡ ፖሊሾች ፡ ትንባሆዬን ፡ እንኳን ፡ አይወስዱትም!» ባይል ፡ ኖሮ ፡ በእውነትም ፡ ኮዛኮቹ ፡ እየተዋጉ ፡ በፈጣን ፡ ፈረሶቻቸው ፡ የጠላቶቻቸውን ፡ ሰልፍ ፡ ጥሰው ፡ ባለፉ ፡ ነበር ። ሽማግሌው ፡ ታራስ ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ በባሕርም ፡ በየብስ ፡ አብሮት ፡ ሲዞምት ፡ የኖረውን ፡ የትንባሆ ፡ ማጨሻውን ፡ ጐንበስ ፡ ብሎ ፡ በሳሩ ፡ ውስጥ ፡ ይፈልግ ፡ ጀመር ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ የጠላት ፡ ወታደሮች ፡ ተንደርድረው ፡ ደረሱና ፡ ኃያል ፡ ትከሻው ፡ ላይ ፡ ሰፈሩበት ፤ ተፍጨርጭሮ ፡ ለማምለጥ ፡ ሞከረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የያዙት ፡ ወታደሮች ፡ እንደወትሮው ፡ እየተፈናጠሩ ፡ አልወደቁም ። «አይ ፡ እርጅና! አይ ፡ እርጅና!» አለና ፡ ኃይለኛው ፡ ኮዛክ ፡ አለቀሰ ። ነገር ፡ ግን ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ጉልበት ፡ ለብዙ ፡ ሰው ፡ ጉልበት ፡ ተሸነፈ ፡ እንጂ ፡ በእርጅና ፡ ምክንያት ፡ አልነበረም ። ሠላሳ ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ እግርና ፡ እጁን ፡ ተጠምጥመው ፡ ያዙትና ፤ «ተፈላጊውን ፡ ይዘነዋል ፤ እንግዲህ ፡ ለዚህ ፡ ውሻ ፡ የሚገባውን ፡ ፍርድ ፡ እንፈልግለት!» እያሉ ፡ ይንጫጩ ፡ ጀመር ። ከዚያ ፡ በጠቅላይ ፡ አዛዣቸው ፡ ፈቃድ ፡ ከነነፍሱ ፡ ሊያቃጥሉት ፡ ተነሱ ። አጠገባቸው ፡ ጫፉ ፡ በመብረቅ ፡ ተመትቶ ፡ ግንዱ ፡ ብቻ ፡ የቀረ ፡ ዛፍ ፡ አገኙና ፡ በብረት ፡ ሰንሰለት ፡ ከግንዱ ፡ ጋር ፡ አሰረው ፡ ከሩቅ ፡ እንዲታይም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እጆቹን ፡ በምስማር ፡ ቸነከሩዋቸው ። ከዚያ ፡ ከሥሩ ፡ ደረቅ ፡ እንጨት ፡ ከመሩ ፤ ታራስ ፡ ግን ፡ ቁልቁል ፡ ወደነሱ ፡ አልተመለከተም ። እሱን ፡ ለማ



ቃጠል ፡ ስለሚያዘጋጁት ፡ እሳትም ፡ አላሰበም ። እሱ ፡ የሚመለከተው ፡ እየተታኮሱ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ የሚከላከሉትን ፡ ኮዛኮች ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ከፍ ፡ ብሎ ፡ ከተቸነከረበት ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ቁልጭ ፡ ብለው ፡ ይታዩታል ።

«በርቱ ፡ ጐበዝ ፤ ያችን ፡ ኮረብታ ፡ ድረሱ! ከጫካው ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ካለው ፡ ኮረብታ ፡ ከደረሳችሁ ፡ አያገኙዋችሁም!» አለና ፡ ጮኸ ። ነገር ፡ ግን ፡ ነፋሱ ፡ ስላገደው ፡ ድምጹ ፡ እነሱን ፡ አልደረሳቸውም ።

«እየ ፡ ጉድ! ጠፉ! በከንቱ ፡ አለቁ!» አለና ፡ በመጨነቅ ፡ ቁልቁል ፡ ወደ ፡ ድኔስተር ፡ ወንዝ ፡ ተመለከተ ።

ወዲያው ፡ በዓ ኖቹ ፡ ላይ ፡ ደስታ ፡ ያበራ ፡ ጀመር ። ከወንዙ ፡ ዳር ፡ በቁጥቋጦዎች ፡ መሃል ፡ ብቅ ፡ ብሎ ፡ የአራት ፡ ጀልባዎች ፡ ጫፍ ፡ ታየው ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ በአለ ፡ ኃይሉ ፡ ጮኸ ፡ ተጣራ ።

«ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር ፡ ጐበዝ! ወደ ፡ ወንዙ ፡ ዳር! በስተግራ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ መንገድ ፡ ቁልቁል ፡ ውረዱ! ከወንዙ ፡ ዳር ፡ ጀልባዎች ፡ አሉና ፡ እንዳይከተሏችሁ ፡ ሁሉንም ፡ ይዛችሁ ፡ አምልጡ!»

ይህን ፡ ሲናገር ፡ ነፋሱ ፡ የሚነፍሰው ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ስለነበር ፡ ድምጹ ፡ ኮዛኮቹን ፡ ደረሳቸው ። ግን ፡ ምክር ፡ በመስጠቱ ፡ የተነሳ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ በመጥረቢያ ፡ ደንደስ ፡ ከኋላ ፡ ጭንቅላቱን ፡ መታውና ፡ የሚያየው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ዓይኑ ፡ ላይ ፡ ዞረበት ።

ኮዛኮቹ ፡ ከገደሉ ፡ በሚያወርደው ፡ መንገድ ፡ ሽምጥ ፡ ጋለቡ ። ግን ፡ አባራሪዎቻቸውም ፡ እንደደረሱባቸው ፡ ስለተገነዘቡና ፡ የመንገዱ ፡ ጠመዝማዛነት ፡ መሰናክል ፡ ስለሆነባቸው ፡ ለአጭር ፡ ጊዜ ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ገቱና ፡ እንደገና ፡ አፏጭተው ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ ገርፈው ፡ አስነሱ ። የታታር ፡ ፈረሶቻቸውም ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ተወርውረው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ዘለው ፡ ከገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ድኔስተር ፡ ውኃ ፡ ውስጥ ፡ ተደፈ

ቁ ። ሁለት ፡ ፈረሰኞች ፡ ብቻ ፡ ከውኃው ፡ ሳይደርሱ ፡ ከገደሉ ፡ ሥር ፡ ካለው ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ከነፈረሶቻቸው ፡ ድምጻቸው ፡ ሳይሰማ ፡ ተከስክሰው ፡ ቀሩ ። ሌሎቹ ፡ ኮዛኮች ፡ ግን ፡ ከነፈረሶቻቸው ፡ እየዋኙ ፡ ደርሰው ፡ ጀልባዎችን ፡ መፋታት ፡ ጀምረዋል ። ፖሊሾቹ ፡ ለመዝለል ፡ እያመነቱ ፡ ከገደሉ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ይህን ፡ ተሰምቶ ፡ የማይታወቅ ፡ የኮዛክ ፡ ድርጊት ፡ ያደንቁ ፡ ነበር ። አንድ ፡ ደፋር ፡ ኮሎኔል ፡ ግን ፡ አንድሬይን ፡ ወጥመድ ፡ ያገባቸው ፡ የዚያች ፡ ውብ ፡ ቆንጆ ፡ ወንድም ፡ ብዙ ፡ አላመነታም ። ወዲያው ፡ ፈረሱን ፡ ኮለኮለና ፡ ከገደሉ ፡ ላይ ፡ ዘለለ ። ግን ፡ ከውኃው ፡ ሳይደርስ ፡ የሾለው ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አርፎ ፡ ተበጣጥሶ ፡ ወደቀ ። አንጎሉም ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ በየቁጥቋጦው ፡ ላይ ፡ ተረጨ ።

በመጥረቢያው ፡ በትር ፡ ደንዝዞ ፡ የነበረው ፡ ታራስ ፡ ቡልባ ፡ አእምሮው ፡ መለስ ፡ ብሎለት ፡ ወደ ፡ ድኔስተር ፡ ሲመለከት ፡ ኮዛኮቹ ፡ ጀልባዎቹን ፡ እየቀዘፉ ፡ እየራቁ ፡ ሲሄዱ ፡ አየ ። ከላይ ፡ የሚተኮሱ ፡ ጥይቶችም ፡ አልደረሱባቸውም ። በዚህን ፡ ጊዜ ፡ የሽማግሌው ፡ ኮሎኔል ፡ የታራስ ፡ ቡልባ ፡ ዓይኖች ፡ በደስታ ፡ አንጸባረቁ ።

ከላይ ፡ ሆኖ ፡ ተጣርቶ ፡ እየራቁ ፡ የሚሄዱትን ፡ ጓደኞቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፤

«ደህና ፡ ሁኑ ፡ ጓደኞቼ! እንዳትረሱኝ! በሚመጣው ፡ የጸደይ ፡ ወቅትም ፡ እንደገና ፡ ለወረራ ፡ እንድትመለሱ! እንዴት ፡ እናንት ፡ ከሃዲ ፡ ፖሊሾች? ኮዛክን ፡ ድል ፡ የሚያደርግ ፡ ፍጥረት ፡ ያለ ፡ ይመስላችኋል? ቆዩማ! ከአሁኑ ፡ እንኳን ፡ በሩቅም ፡ በቅርብ ፡ ንግርት ፡ ይወራል ፡... ከሩሲያ ፡ ምድር ፡ አንድ ፡ ገዥ ፡ ይነሳል ። በምድርም ፡ ላይ ፡ ለሱ ፡ የማይገብር ፡ አንድም ፡ አይገኝም!»

ከሥር ፡ የተከመረው ፡ እንጨት ፡ ተያይዞ ፡ ነበልባሉ ፡ እግሩን ፡ እየጠበሰ ፡ በዛፉ ፡ ወደላይ ፡ ወጣ ። ግን ፡ ምን ፡ እሳት ፡



ነው ፤ ምን ፡ ስቃይ ፡ ነው ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ኃይል ፡ ነው ፡ የሩሲያዊን ፡ ኃይል ፡ የሚያሸንፈው!

ድኔስተር ፡ ትንሽ ፡ ወንዝ ፡ አይደለም ፤ ተከታዮቹ ፡ ውኃዎች ፡ ጨፌዎቹና ፡ ጥልቅ ፡ ጉድጓዶቹም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። እንደ ፡ መስተዋት ፡ የጠራው ፡ ውኃው ፡ ይፈልቃል ። በላዩም ፡ የሚያንዣብቡት ፡ የወንዝ ፡ አሞሮችና ፡ በየጨፌዎቹ ፡ የሚደበቁት ፡ አእዋፍ ፡ ዜማ ፡ ይሰማል ። ኮዛኮቹ ፡ በባለሁለት ፡ መሪ ፡ ጠባብ ፡ ጀልባዎቻቸው ፡ በፍጥነት ፡ እየቀዘፉ ፡ ጉዞአቸውን ፡ ቀጠሉ ። እየቀዘፉ ፡ መሪአቸውን ፡ ቡልባንም ፡ በማንሳት ፡ እያወጉ ፡ ተጓዙ ።

## መግለጫ ።

ኒኮላይ ፡ ጐጐል ፡ በ «ታራስ ፡ ቡልባ» ፡ የሚገልፀው ፡ ዘመን ፡ በኡክሬይን ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ ከማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ የከፋ ፡ ዘመን ፡ ነበር ። እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ በ ፲፱፻፰ ዓ ፡ ም ፡ በሉብሊን ፡ ዑኒያ ፡ መሠረት ፡ የኡክሬይን ፡ አገር ፡ ያለ ፡ ሕዝቡ ፡ ፈቃድ ፡ ከፖላንድ ፡ ጋር ፡ ተቀላቅሎ ፡ ነበር ። የፖላንድ ፡ መኳንንትም ፡ ይህን ፡ ሰፊና ፡ ለም ፡ አገር ፡ የእጅ ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ባለሃገሩን ፡ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ያለ ፡ ርኅራኄ ፡ በጭቆና ፡ ያስገብሩት ፡ ጀመር ። ሕዝቡን ፡ ጨርሶ ፡ ፖሊሽ ፡ ለማድረግም ፡ በመሞከር ፡ የኡክሬይንን ፡ ቋንቋ ፡ ከልክለው ፤ ልዩ ፡ የሆነውን ፡ የኡክሬይን ፡ ባህል ፡ ጨቁነው ፡ በጠቅላላው ፡ ሃገሩን ፡ በመንፈስም ፡ ሆነ ፡ በኤኮኖሚ ፡ ረገድ ፡ ባሪያ ፡ ለማድረግና ፡ ብሄራዊ ፡ ነፃነቱን ፡ ለመግፈፍ ፡ በብዙ ፡ መንገድ ፡ ይጥሩ ፡ ነበር ። እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ከ ፲፱፻፲፯ ዓ ፡ ም ፡ ጀምሮ ፡ የብሬስት ፡ ዑኒያ ፡ ሲታወጅ ፡ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ከተጫነበት ፡ የኤኮኖሚና ፡ የፖሊቲካ ፡ ጭቆና ፡ በላይ ፡ ተጨማሪ ፡ የሃይማኖት ፡ ጭቆና ፡ ወደቀበት ።የፖላንድ ፡ መኳንንትና ፡ ቀሳውስት ፡ የሕዝቡን ፡ ሃይማኖት ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ካቶሊክነት ፡ እያስለወጡ ፡ በከሃዲነት ፡ እምቢ ፡ ያለውን ፡ ወይም ፡ በኦርቶዶክስነት ፡ የሚፀናውን ፡ ሁሉ ፡ በጭካኔ ፡ ይቀጡት ፡ ጀመር ።



ይህ ፡ ሁሉ ፡ ቢከብደው ፡ ሕዝቡ ፡ የጭቆና ፡ ቀንበሩን ፡ አውልቆ ፡ ለመጣል ፡ ተነሳና ፡ በኡክሬይናውያን ፡ ገባር ፡ ባለሃገሮች ፡ ቀስቃሽነት ፡ ብዙ ፡ ሁከት ፡ እያነሳ ፡ መከተ ። ኡክሬይን ፡ ለነፃነቷ ፡ ባደረገችው ፡ በዚህ ፡ ጦርነት ፡ ጉሉህና ፡ ዓይነተኛ ፡ ተግባር ፡ የፈፀመው ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፡ ሲሆን ፡ ይህም ፡ የኮበለሉ ፡ ገባሮችና ፡ እንዲሁም ፡ ብሔራዊና ፡ ሰብዐዊ ፡ ጭቆና ፡ አንገፍግፏቸው ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ሃብታሙ ፡ ደቡባዊ ፡ ሩሲያ ፡ የመጡ ፡ ነፃነት ፡ ወዳድ ፡ ሰዎች ፡ ያቋቋሙት ፡ ወታደራዊና ፡ ሕዝባዊ ፡ ድርጅት ፡ ነበር ። ዘመን ፡ እያለፈ ፡ ሲሄድ ፡ የዛፖሮዥያን ፡ ኮዛኮች ፡ ለነፃነት ፡ የሚያደርጉት ፡ ውጊያ ፡ ቱርኮቹን ፡ ታታሮችንና ፡ የፖላንድንም ፡ መኳንንት ፡ ፍርሃትና ፡ ስጋት ፡ አሳደረባቸው ። በ «ታራስ ፡ ቡልባ» ፡ ውስጥ ፡ በተገለፀው ፡ ዘመን ፤ ማለት ፡ በሺ ፡ ሰባት ፡ መቶኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፤ የዛፖሮዥያን ፡ ሴች ፤ ያልተለመደ ፡ በሆነው ፡ የአኗኗር ፡ ጠባዩና ፡ በጠንካራው ፡ የጦር ፡ ድርጅቱ ፡ የተነሳ ፤ የኡክሬይን ፡ ሕዝብ ፡ ለነፃነቱና ፡ እንደገና ፡ ከሩሲያ ፡ ለመቀላቀል ፡ ላደረገው ፡ ትግል ፡ ዋና ፡ ግንባር ፡ ሆነ ።

<u>ገጽ ፡ ፶</u>

[1] ሄትማንቺና ፡—በድኔፐር ፡ ምሥራቃዊ ፡ ወደብ ፡ የሚገኘው ፡ በፖላንድ ፡ ንጉሥ ፡ በተሾመ ፡ ሄትማን ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የኡክሬይን ፡ ክፍለ ፡ ሃገር ።

<u>ገጽ ፡ ፶፪</u>

[2] በብረት ፡ ድስት ፡ የተቀቀለው ፡ ሄትማን ፡—በአፈ ፡ ታሪክ ፡ መሠረት ፡ ሄትማን ፡ ናሊቫይኮ ፡ የተባለው ፡ የኮዛኮች ፡ ድርጅት ፡ መሪ ፡ በፖሊሾች ፡ እጅ ፡ ገብቶ ፡ በብረት ፡ ድስት ፡ ተቀቅሎ ፡ መሞቱ ፡ ይነገራል ።

ገጽ ፡ ፻፳፯

[3] ሄትማን ፡ አስትራኒትሳ ፡—ኮዛኮች ፡ በፖሊሽ ፡ ጨቋኞቻቸው ፡ ላይ ፡ ባደረጉት ፡ ተቃውሞ ፡ ከመሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ ሲሆን ፤ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ) በ ፲፱፻፳፱ ዓ ፡ ም ፡ በዋርሶ ፡ ከተማ ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ ተፈጸመበት ።

ገጽ ፡ ፻፳፱

[4] ጉንያ ፡—ጉንያ ፡ ሌወን ፡—(እ ፡ ኤ ፡ አ ፡) በ ፲፱፻፳፱ ዓ ፡ ም ፡ በተደረገው ፡ ዘመቻ ፡ የአስትራኒትሳ ፡ ቀኝ ፡ ክንድ ፡ የነበረ ፡ ኮዛክ ።

## አንባብያን ፡ ሆይ!

የፕሮግሬስ ፡ የመጻሕፍት ፡ ማዘጋጃና ፡ ማሳተሚያ ፡ ቤት ፡ ስለዚች ፡ መጽሐፍ ፡ ትርጉም ፤ ዝግጅትና ፡ እትም ፡ ያላችሁን ፡ አስተያየትና ፡ አሳባችሁን ፡ ብትገልጹለት ፡ በደስታ ፡ ይቀበላል ።
አድራሻው ፤

21, Zubovsky Boulevard,
Moscow, USSR.